# የመጨረሻዋ
# ዘመን
# ቤተ ክርስቲያን


መጋቢ መኮንን ሞገስ



1990 ዓ.ም ታተመ
1998 እ. ኤ. አ.


ለመጋቢ በዓሉ

መልካም የአገልግሎት ዘመን ይሁንልህ

ከመጋቢ መኮንን ሞገስ

21/11/98 CAIRO

**ማሳሰቢያ**

ጸሐፊው ይህን መጽሐፍ ሲፅፍ የተጠቀመው በአዲሱ ትርጉም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን አንዳንድ ጥቅሶች ግን በ1954 ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ነው:: ይህንን ለመለየት ከጥቅሶቹ ጎን የቀድሞ ትርጉም በማለት በአጭሩ (የቀ:ት) ተብሎ ተጽፎ እናገኘዋለን::

# የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን

ይህንን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ መልሶ
ማሳተም ወይም ማባዛት በሕግ የተከለከለ ነው::

# The Last Day Church

Copyright 1998

By
**Mekonnen Moges**

All Rights Reserved

የሽፋን ስዕል
በታምራት አበበ

## *DEDICATION*

*For the Greater Glory of the*
*Lord Jesus Christ*

This book is dedicated to my wife
"Tigist" who has faithfully helped me
in my ministry, and to my daughter "Bemenet"
whom I love very much

## ለክርስቶስ ኢየሱስ ታላቅ ክብር

ይህን መጽሐፍ በጣም ለምወዳት በአገልግሎቴና
በሕይወቴ ታማኝ ረዳት ለሆነችኝ ለባለቤቴ ለትእግስት
እና
በጣም ለምወዳት ልጄ ለበእምነት መኮንን
በራሴና በአንባቢያን ስም አበረክታለሁ ::

ደራሲው የመጀመሪያ ጽሑፉ ስለሆነ ለሚኖረው የቃላት ወይም የዐ/ነገር አቀማመጥ ስህተት ቢኖር በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየኩኝ ዋናው የመጽሐፉ አሳብ ላይ ትኩረት እንድታደርጉ በትህትና እጠይቃለሁ ::

# ምስጋና


ከሁሉ በፊት በከበረው ደሙ አጥቦ ስሜን በሕይወት መዝገብ ላይ ለፃፈው፤ ፀጋውን አትረፍርፎ ለአገልግሎቱ ታማኝ አድርጎ ላቆመኝ ለጌታ ለኢየሱስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ምስጋናና ክብር ለእርሱ እሰጣለሁ ::

ይህን መጽሐፍ ለህትመት ከመላኩ በፊት ውድ ጊዜአቸውን ሰጥተው ጽሁፉን በመገምገም አስተያየትን፥ የአባትነት ምክርን ለሰጡኝ እንዲሁም በፀጋ ላበረታቱኝ ለመጋቢ ሰይፉ ከበደ ከፍ ያለ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ ::

በጌታ መንፈሳዊ አባትና ወንድም ሆኖ ላሳደገኝና በአገልግሎቴም ብዙ ለረዳኝ እንዲሁም ይህንን መጽሐፍ በመገምገም አስተያየቱን ለሰጠኝ ለመንፈሳዊ አባቴ ተክለአብ ዘሩ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ ::

የመጽሐፉን ረቂቅ ሳይሰለችና ደክመኝ ሳይል ደጋግሞ በማንበብና በማስተካከል አሳቦችንም በመስጠት ለዚህች መጽሐፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረገው ለወንድም አሰፋው ፀጋዬ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ ::

የአማርኛ ቃላቶችን በማረም ለረዱኝ ለወንድም አበባየሁ ታከለና ለወንድም ግርማ ወ/ሥላሴ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ ::

አገልግሎቴንና ይህም መጽሐፍ ተጀምሮ እስከሚጨረስ ድረስ በፀሎት ከጎኔ በመቆም በጣም የረዱኝን ለውድ ባለቤቴ ትእግስት ወንድይፍራው፤ ለእህት ደስታ ውድማና ለእህት የሺመቤት ዳምጤ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ ::

ረቂቁን በኮምፒዩተር በመፃፍ ለዚች መጽሐፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረገችው ለእህት ትንቢት ዳኜ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ ::

እንዲሁም ለጽሁፉ የሚረዳኝን የአማርኛ የኮምፒዩተር ፊደሎችን(ሶፍት ዌር) በዲስክ ከአሜሪካ በመላክ ለተባበረኝ ለወንድም ዮናስ ተወልደ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ::

በመጨረሻም በእግዚአብሔር ፍቅር ለምንዋደድ አገልገሎቴን በማክበር እንደ እግዚአብሔር ቃል ለሚታዘዙልኝና በፀሎት ለሚረዱኝ ለቤተ ክርስቲያናችን ሽማግሌዎች (መሪዎች)፤ አገልጋዮችና ምዕመናን በጣም ከፍ ያለ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ ::

# ማውጫ


**አርዕስት** **ገፅ**

መቅድም ........................................ 4

መግቢያ ........................................ 8

ምዕራፍ 1. የእውነተኛ ነገር ጥላዎች........................................ 10

ምዕራፍ 2. ቤተ ክርስቲያን የተጠራችበት የክብር ስፍራ ............ 22

- ለሀብታሞችና ለድኾች የተዘጋጀ ግብዣ........................................ 24
- በአትክልቱ ስፍራ የተሰወረው ታላቅ ሀብት ........................................ 25
  - ሀ. መጋረጃዎቹ ........................................ 26
  - ለ. የዕብነ በረድ ምሰሶዎች ........................................ 27
  - ሐ. የወርቅና የብር ድንክ አልጋዎች........................................ 29
  - መ. የሚፈነጥቅ ቀለማት ያለው መሠረት........................................ 31
- የንጉሡ ልግሥና ........................................ 33
  - ሀ. የወርቅ ዋንጫ ........................................ 33
  - ለ. ገደብ የሌለው በረከት ........................................ 33

ምዕራፍ 3. ከክብር የጎደለችው ቤተ ክርስቲያን........................................ 37

- ለብቻዋ መከበር ፈለገች........................................ 39
- ዘውዷን ለመጫን እምቢ አለች........................................ 40
- የንጉሡ ቁጣ መንደድ ........................................ 43
  - ሀ. ክብርዋ የሆነውን ዓምድ ገፋች ........................................ 43
  - ለ. ሕያው የሆነውን አገልግሎት ገፋች ........................................ 45

ምዕራፍ 4. የተሐድሶ ሥራ በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን መጀመር ........................................ 50

- የተሐድሶ ዘመናት ........................................ 52
- አቋሟ የተስተካከለ ቤተ ክርስቲያን........................................ 55
- የጊዜ ተጠቃሚ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ........................................ 58
- ቅርጿን ለማስተካከል የወሰነች ቤተ ክርስቲያን ........................................ 61
  - ሀ. ቤተ ክርስቲያን በሕንፃ ስትመሰል ........................................ 62
  - ለ. ቤተ ክርስቲያን በአካል ስትመሰል........................................ 63

ምዕራፍ 5. ቤተ ክርስቲያንን ቅርጽ የሚያስይዝዋት አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች........................................ 66

- በአገልግሎት ቅባት የሚገኘውን ዋጋ መቀበል ........................................ 68

ሐዋርያት .................................................... 70
የሐዋርያት ቅባት በሰማርያ ቤተ ክርስቲያን..................... 71
ነቢያት .................................................... 76
ሀ. በእግዚአብሔር የተጠሩ ናቸው ............................ 77
ለ. እግዚአብሔር የሚያዛቸውን የሚናገሩ ናቸው ................. 78
ሐ. የእግዚአብሔርን ቃል በኃይል የሚቀበሉ ናቸው............ 78
ወንጌላውያን.................................................... 81
እረኞች.................................................... 82
ሀ. እግዚአብሔር ለአንድ ማኅበር አንድ እረኛ ይፈልጋል........ 83
ለ. በሁሉ ነገር ብቃትን የሚሰጥ መንፈስ ያለው ነው .............. 85
እረኛ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን መውጣት አለበት.......... 86
ሐ. እረኛ በሊቀ ካህኑና በማኅበሩ መካከል የሚቆም ነው ...... 92
መ. እረኛ ማኅበሩ ይታዘዙለት ዘንድ የሥልጣን ተካፋይ ነው ... 94
ሠ. እረኛ በሊቀ ካህኑ የሚደገፍ ነው ............................ 100
ረ. እረኛ በተግባር አፈጻጸም መላውን ማኅበር ይመራል .......... 102
አስተማሪዎች .................................................... 106
ሀ. ትምህርቱ አዲስ ስለሚሆንባቸው ............................ 109
ለ. ለአዲስ የወይን ጠጅ አዲስ አቁማዳ ያስፈልጋል................ 110
ሐ. የተቀበሉትን መናቅ ............................................ 111
የመንፈስ ቅዱስ የክትትል ሥራ ........................................ 113

ምዕራፍ 6. የንግሥናዋን አክሊል የደፉች ቤተ ክርስቲያን.......... 114

ሀ. የመዋቢያ ዘመን ............................................ 116
ለ. የቤተ መንግሥቱ ነዋሪዎች ...................................... 120
ሐ. አስቴር ማን ናት ?............................................ 122
መ. አንተስ ማን ነህ ?............................................ 125

ምዕራፍ 7. የሃማን በጠላትነት መነሣት.............................. 130

ሀ. በማያምኑ ሰዎች የሚገለጥ የዐማሌቅ አሠራር ................ 133
ለ. በነገሥታት የሚገለጥ የዐማሌቅ አሠራር ........................ 133
ሐ. በጻኑ ሰዎች የሚገለጥ የዐማሌቅ አሠራር ........................ 134
የመንፈስ ቅዱስ የሐዘን ድምጽ............................................ 136
የመንፈስ ቅዱስ የማስጠንቀቂያ ድምጽ ለመጨረሻዋ
ዘመን ቤተ ክርስቲያን ............................................ 138

ምዕራፍ 8.ለመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የወርቁ
በትር መዘርጋት............................................ 140

የወርቁ በትር መዘርጋት ............................................ 142
በግብዣው ቦታ የሰይጣን ራስ መቀጥቀጥ ............................ 145
የመላእክት አገልግሎት በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ..... 147
የብልፅግና ምርኮ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት .................... 152
ሀ. ጣዖትን የሚያመልኩ አገሮች ...................................... 153
ለ. ሥልጣናቸውን የሚጠቀሙ እማኞች ያሉበት አገር ......... 154
ሐ. ሥልጣናቸውን የማይጠቀሙ እማኞች ያሉበት አገር ...... 154

ምዕራፍ 9. የቀለበቱ ማኅተም ለመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን
መመለስ............................................ 160

የቀለበቱ ማኅተም መመለስ ............................................ 162
የአመለካከት ተሐድሶን ማግኘት ........................................ 163
ሀ. የዘንዶው ምንጭ ............................................ 165
ለ. የጉድፍ መጣያ ስፍራ ............................................ 165
ሐ. የንጉሡ ኵሬ (መዋኛ) ............................................ 166
መ. የሸለቆው ቅጽር በር ............................................ 168

ምዕራፍ 10. የቤተ ክርስቲያን በትንሳኤው ኃይል በታላቅ ክብር
መመላለስ............................................ 174

የበቀል ቅባት በቤተ ክርስቲያን መፍሰስ ................................ 176
ሀ. የሳምሶን ምሳሌነት ............................................ 176
ለ. የሙሴ ምሳሌነት ............................................ 178
ሐ. የበቀል ቅባት የሚፈስባቸው ሰዎች ................................ 179
የመንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ቦታውን መያዝ ............................ 180
ሀ. የቤተ ክርስቲያን በትንሳኤው ኃይል መመላለስ ............ 180
ለ. የመንፈስ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን መዘጋጀት ............ 181
ሐ. የእምልክ መታደስ ............................................ 182
የቤተ ክርስቲያን መፈራት ............................................ 182
የብዙ ሰዎች መዳን ............................................ 184
በድል ላይ ድል መጨመር ............................................ 186
የቤተ ክርስቲያን ወደ እምነት አንድነት መምጣት ............ 188
የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ............................................ 190
ሀ. የፑሪም በዓል (መነጠቅ)............................................ 190
ለ. የማትነጠቅ ቤተ ክርስቲያን ........................................ 195
ማጠቃለያ............................................ 196

# መቅድም

መጽሐፈ አስቴርን የፃፈው ሰው ማን እንደሆነ አይታወቅም:: ይሁን እንጂ የሜዶንና የፋርስን ሕግ ጠንቅቆ የሚያውቅ አይሁዳዊ እንደጻፈው ይታመናል:: መጽሐፉ በመርዶክዮስ ወይም በዕዝራ ተጽፎአል የሚልም ግምት አለ:: በመጽሐፉ ውስጥ አንድ ጊዜ እንኳን የእግዚአብሔር ስም አልተጠቀሰም ይሁን እንጂ የአምላክ ተአምራታዊ እጆች አይሁዶችን ሲረዳ÷ ጠላቶቻቸውን ሲደመስስ እንዲሁም ከአዘቅት ውስጥ ከፍ ሲያደርጋቸው ይታያል ::

በመጽሐፉ ውስጥ ጐልተው የሚታዩት ባለ ታሪኮች መርዶክዮስና አስቴር ሲሆኑ ደካማ በሆኑት በእነዚህ አይሁዶች ሕይወት ውስጥ የተከናወነው ሁሉ የሚያንጸባርቀው እግዚአብ ሔርን ነው :: ሁለቱ በተአምር በመንግሥቱ አመራር ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ ራሳቸውን ያገኙት ጾምን በማወጅና ራስን በማዋረድ÷ ወቅት ሲያገኙ ደግሞ ጠላቶቻቸውን እስከ መጨረሻ መስቀላቸው የመጽሐፉን መንፈሳዊ ይዘት ያመለክታል:: መርዶክዮስም ሆነ አስቴር ሰውን የማይፈሩ ጽኑ እምነት ያላቸው ሰዎች ናቸው ::

በመንፈሳዊ ዕድገታቸው በኩልም ቢሆን ቅደም ተከተላቸውን የሚያውቁ ሰዎች ነበሩ:: በተለይም አስቴር ወደ ንጉሡ ለመግባት ስትወስን በሕይወትዋ ቆርጣ ነበር የገባችው:: ጉዳይዋን ወዲያው ለንጉሡ አልተናገረችም ግን አመቺ ጊዜ ለማግኘት ንጉሡን ለእራት ጋበዘችው:: መርዶክዮስም ቢሆን በሞት ፍርድ የሚያስቀጣ ቢሆንም እምቢ አሻፈረኝ ለሃማ አልሰግድም ያለ ቆራጥ ነበር:: የእነዚህን ሁለት ባለታሪኮች እና ሌሎችንም የመጽሐፉን ክፍል ስንመለከት አሁን ላለችው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጥሳ ናቸው ::

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለተኛ ጢሞቴዎስ 3÷16-17 ድረስ "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ

የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል "ይላል :: መጽሐፈ አስቴርን በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ በማጥናት መጋቢ መኮንን ሞገስ ለመጨረሻው ዘመን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ትምህርት አዘል የሆነ "የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን" የሚል መጽሐፉን ደርሶ አቅርቦልናል:: መጋቢ መኮንን ሞገስ በግብጽ አገር ካይሮ ከተማ ውስጥ ያለችው ማራናታ የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን ዋና መጋቢ ነው:: በዚያው ክፍለ ዓለም የተበተኑ ወገኖቻችንን በወንጌል በመድረስ፥ በማሳደግና በአገልግሎት በማሠማራት በእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ ወንድም ነው :: የመጋቢ መኮንን ሞገስን መንፈሳዊ ብስለት መጽሐፉን ጠለቅ ብላችሁ ስታነብቡት ትረዳላችሁ::

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የተባለውን መጽሐፍ አንብቤ የግል አስተያየቴንና እርማትም እንድሰጥ በመጠየቄ በጣም ተደስቻለሁ :: ምክንያቱም እግዚአብሔር በተለያዩ ልጆቹ ውስጥ ያለውን ጸጋ እንዳይ ረድቶኛል:: ደራሲው መጋቢ መኮንን ከጌታ ዘንድ የተቀበለው የቃል መገለጥ በዘመናችንም ላለች ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን የአሳብ ጥልቀት ተመልክቼ ተደንቄአለሁ ::

ቤተ ክርስቲያን ለመክበር ተጠርታለች ወደዚያ ሙላት ደግሞ የሚያደርሳት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው :: በሐዋርያት እጅ የተገለጡት ተአምራትና ድንቅ ቅዱሳን መጻሕፍት ተለይተው ከተጠረዙ በኋላ አሁን አስፈላጊ ስላልሆኑ ቀርተዋል የሚል ትምህርት አለ:: ይህ የስህተት ትምህርት ቤተ ክርስቲያንን ተአምራት ዓልባ ከማድረጉም በላይ ፍልስፍናውን ለአማኞችዋ ታስተምራለች ለዚህ ነው ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በሰይጣን ላይ ኃይል ያጣችው :: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት "የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል ከእነዚህ ደግሞ ራቅ" (2ጢሞ 3÷5) ይለዋል ::

እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ የተሞላች ቤተ ክርሰቲያንን በዓለም ዙሪያ እያንሳሳ ነው:: በተለያየ የአገልግሎት ቅባት የተቀቡ አገልጋዮችን እያስነሳ ተሃድሶ በየአቅጣጫው በመካሄድ ላይ ይገኛል :: ይህ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ወደ ቀድሞ ክብርዋና ኃይልዋ ተመልሳ ትታደሳለች :: ነቢዩ ሐጌ በምዕራፍ 2÷9 ላይ "ከፊተኛው ይልቅ የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል" ይላል:: ንግሥት አስቴር ከንጉሡ በተሰጣት ቅባትና ሽቱ አምራ፥ ደምቃና ተኳኩላ ንግሥት አስጢንን እንደተካቻት በመጨረሻው ዘመን ያለችውንም ቤተ ክርስቲያን ጌታ ሸላልሞ ለራሱ ያቀርባታል :: ይህቺው ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉዋት የተቀቡ ቅሪቶችዋ ወደ ሙላት ያመጡአታል ::

የተወደዳችሁ አንባቢዎች "የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ስታነብቡ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ዓይናችሁን እንዲከፍትላችሁና እንዲባርካችሁ ጸሎቴ ነው:: መጽሐፉ በግል ሕይወታችሁም ሆነ በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ለመጽሐፍ ቅዱስ የቡድን ጥናት በጣም ጠቃሚ ነው:: ይህ የተአምራትና የምርኮ ዘመን ስለሆነ መንፈሳዊ ትጥቃችሁን ታጠቁና ውረሱ :: ቤተ ክርስቲያን ያጣችውን ክብር መልሳ የምታገኘው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው:: መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ ራዕይ 2÷11 ይህን መጽሐፍ በብዙ ጸሎትና ድካም የደረሰውን መጋቢ መኮንን ሞገስን አመሰግናለሁ ::

መጋቢ ሰይፉ ከበደ

መለኮታዊ ኃይል የወንጌል አገልግሎት መሥራች

# መግቢያ

"የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን" በሚል ርዕስ የተፃፈው ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያደርግና ሊሠራ ያሰበውን የራሱን ዕቅድ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በማነፃፀር ነው::

እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ያሰበውን የራሱን አሳብ ወደ ማጠቃለያ ለማድረስ ከመቼውም ዘመን ይልቅ አሁን ባለንበት ዘመን በታላቅ ኃይል በመሥራት ላይ ይገኛል:: ይህም የእግዚአብሔር አሳብ በፍጥረት ሁሉ ላይ ስለፈሰሰ ፍጥረት ሁሉ በማስተዋልም ባለማስተዋልም የሚጠባበቀው የዘመኑን ፍፃሜ ነው::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "የመጨረሻው ዘመን " የሚለው ርዕስ ተደጋግሞ የሚጠቀስና በሁሉም አማኝ ውስጥ የሚስተጋባና ትልቅን ስፍራ የያዘ ነው:: ቢሆንም ቤተ ክርስቲያንን በመምራትና ሕዝቡን በማገልገል ላይ ያሉ አገልጋዮች ሕዝቡም ራሱ "የመጨረሻው ዘመን" መቅረቡን ብቻ አውቀው ይህንንም ድምፅ በማስተጋባት ግራ መጋባትን ነው እንጂ የያዙት እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ምን ዓይነት ዕቅድና ሥራ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳለው፤ አማኞች በምን ዓይነት መልኩ በመጨረሻው ዘመን መመላለስ እንዳለባቸው፤ እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ያለውን እውነተኛ አሳብና ለቤተ ክርስቲያን ያለው የዘላለም ዕቅድ ለብዙዎቹ ገና ያልተፈታላቸው እንቆቅልሽ ነው ::

እንቆቅልሽ የሆነብን እግዚአብሔር ከእኛ ስለሰወረው አይደለም:: ምክንያቱም "ልዑል እግዚአብሔር ምስጢሩን ለአገልጋዮች ለነቢያት አስቀድሞ ሳይገልጥ ምንም ነገር አያደርግም::" (አሞጽ 3÷7) ነገር ግን የተገለጠውን ምስጢር እንደሚገባ ለማወቅ ቤተ ክርስቲያን ካልተነሳች "ሕዝቤ ዕውቀትን ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤"(ሆሴዕ4÷6) ተብሎ እንደተፃፈ ዛሬም ቢሆን ያለብንን የእንቆቅልሽ ጥያቄ ፍቺውን ከእግዚአብሔር ቃል ካላወቅን በስተቀር በብዙ ነገር መጥፋታችን የማይቀር ነው ::

እንግዲህ ከመጽሐፈ አስቴር የተገኘውን የቃሉን መገለጥ እግዚአብሔር ለመጨረሻው ዘመን አማኞችና ቤተ ክርስቲያን ያለውን የዘላለም ዕቅድ በመገለጥ እግዚአብሔር በሰጠኝ ፀጋ መሠረት ለክርስቶስ ኢየሱስ ክብር፤ ለቤተ ክርስቲያን መታነጽና ለአማኞች ጥቅም ይህቺን መጽሐፍ ፅፌአለሁ :: በተረፈ እግዚአብሔር ይህቺን መጽሐፍ ተጠቅሞ በምድራችን ላይ ባሉ አብያተ ክርስቲያናትና በተለያዩ የዓለም ክፍል ባሉ የኢትዮጵያውያን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ ተሐድሶን እንዲያመጣ እፀልያለሁ :: ለእኛም ከቃሉ የሚማርን ልብ እግዚአብሔር ይስጠን :: አሜን !!!

*ከመጋቢ መኮንን ሞገስ*

# ም ዕ ራ ፍ  አ ን ድ

## የእውነተኛ

## ነገር

## ጥላዎች

# የእውነተኛ ነገር ጥላዎች

መጽሐፍ ቅዱሳችን በዘላለሙ አምላክ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተፃፈ ስለሆነ ስህተትና ነቀፋ የሌለበት፤ በእግዚአብሔር የዘላለም አሳብ መሠረት የሰፈረና ለሰው ልጆች ያለውን የዘላለም አሳብ የገለፀበት፤ ዛሬም የሚሠራ፤ ሕይወትና መንፈስ ያለበትን ቃል የያዘ መጽሐፍ ነው:: ቃሉን በፃፈው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ዛሬም ሲተረተር እጅግ አስደናቂ ምስጢር እንደያዘ እንረዳለን::

በመጽሐፈ አስቴር የተገለጹ ድርጊቶች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ታላቅና አስደናቂ ምስጢር የያዙ ናቸው :: ይህም ቤተክርስቲያን ከተጠራችበት ክብር አንስቶ የጥሪዋ ዓላማና ውበት፤ እንዲሁም የጥሪዋ የማጠቃለያ ሥራና ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ምድር እስከምትወሰድበት ጊዜ ድረስ ቁልጭ ባለ መልኩ ተገልጦ እናየዋለን :: እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት በክብርም በዓይነትም በጣም ልዩ የሆነውን በአዲስ ኪዳን ያለውን ዕቅድ የገለጸበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው:: በመሆኑም አማኞች ሁሉ አውቀውት እግዚአብሔር ባዘጋጀልን የዘላለም በረከት ውስጥ እንድንኖር ስለሚረዳን በማስተዋል እንመለከተዋለን::

በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ በሰው እጅ ሳይሆን በጌታ ወደ ተተከለችው ሰማያዊ ቅድስተ ቅዱሳን ደሙን ይዞ ስለገባው ታላቅ ሊቀ ካህን ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከገለፀ በኋላ ስለ ብሉይ ኪዳን የሊቀ ካህናት አገልግሎት ሲገልጽ ግን "እነርሱ የሚያገለግሉት ለሰማያዊ ነገሮች ምሳሌና ጥላ በሆኑት ነገሮች ነው፤...." (ዕብ 8÷5) ይለናል :: በብሉይ ኪዳን የነበሩ አንዳንድ አገልግሎቶች ለእውነተኛው ነገር ጥላ ወይም ምሳሌ እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳችን ይነግረናል :: ሙሴ ድንኳኒቱን በሚሰራበት ጊዜ እግዚአብሔር "በተራራው ላይ እንደተገለጠልህ ዓይነት ሁሉን ነገር በጥንቃቄ አድርግ " (ዕብ 8÷5) ብሎ ያዘዘው እግዚአብሔር እንደ ጥላ ለሚያልፍ ነገር ብቻ አስቦ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ ጥላ ወይም ምሳሌ ስለሆነ ነበር:: ከዚህም የተነሳ በድንኳኑ ውጭና ውስጥ ለምሳሌ የናስ መሠዊያ÷ የመታጠቢያ ሳህን÷ የወርቅ መቅረዝ÷ የኅብስት





ገበታ÷ የዕጣን መሠዊያ÷ መጋረጃውና የኪዳኑ ታቦት የመሳሰሉት ሙሉ ለሙሉ የክርስቶስን ጥላ የሚያሳዩ ናቸው::

ሙሴ በጥንቃቄ ከሠራው ከድንኳኑ ሌላ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደ ምሳሌ ወይም ጥላ አድርገን የምንወስዳቸው ብዙ ነገሮች አሉ :: ጌታ ኢየሱስ ራሱ በምድር በነበረ ጊዜ ስለ ራሱ ከብሉይ ኪዳን በምሳሌ ወይም በእውነተኛው ነገር ጥላ እየጠቀሰ ካስተማራቸው ውስጥ ለምሳሌ

"ሙሴ በበረሓ እባብን ከፍ እድርጎ እንደሰቀለ
እንዲሁም የሰው ልጅ ከፍ ብሎ ሊሰቀል ይገባዋል::"
(ዮሐ 3÷14 ዘኁ 21÷4-9)

" ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና
ሦስት ሌሊት እንዳሳለፈ እንዲሁ የሰው ልጅ በመቃብር
ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ያሳልፋል"
(ማቴ 12÷40 ዮናስ 1÷17)

በመጽሐፍ ደረጃም ብንወስደው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለአዲስ ኪዳን እውነቶች በምሳሌ ወይም በጥላ ያስቀመጠው ብዙ ነገር አለ:: ከነዚህም መጻሕፍት ውስጥ አንዱ መጽሐፈ አስቴር ነው :: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሴት ስሞች ከተጠቀሱት ሁለት መጽሐፍት ውስጥ አንዱ መጽሐፈ አስቴር ሲሆን ሌላኛው መጽሐፈ ሩት ነው:: አስቴር ማለት "ኮከብ" ማለት ነው:: መጽሐፈ አስቴር በፋርስ መንግሥት ጊዜ በእሥራኤል ምርኮኞች ላይ የደረሰውን ስደትና ከዚያም ግሩምና ታላቅ በሆነ መንገድ መዳናቸውን እንዴት እንዳገኙ የሚተርክ ነው:: መጽሐፈ አስቴርን ማን እንደጻፈው ባይታወቅም ነገር ግን የፋርስን ቤተ መንግሥት የአኗኗር ሁኔታና እንዲሁም የቤተ መንግሥቱን ደንቦች በሚገባ የሚያውቅ አይሁዳዊ መሆኑ አያጠራጥርም ::

በመጽሐፈ አስቴር የንጉሥ አርጤክስስ ስም በጣም ብዙ ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን ከጾም በስተቀር ምንም ዓይነት ስለ አይሁዳውያን የሃይማኖት ሥርዓትና ሕግ እንዲሁም ስለ ፀሎት መጽሐፉ ውስጥ የምናየው ምንም ነገር የለም:: በተጨማሪም እንደ መኃልየ መኃልይ መጽሐፍ በመጽሐፈ አስቴርም ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በአንድም ስፍራ የእግዚአብሔር ስም አልተጠቀሰም :: በዚህ ምክንያት በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በመጠኑም

ቢሆን መጽሐፈ አስቴርን እንደ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አድርገው ለመቀበል ያንገራገሩበት ጊዜ ነበር:: ምንም እንኳን በመጽሐፉ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም ባይጠቀስም ነገር ግን እግዚአብሔር ታላቅ የሆነውን የማዳን ሥራውን ለሰዎች እንደሚገባ አድርጎ በተጨባጭ ሁኔታ በትዕይንት የገለጸበት በመሆኑ መጽሐፉ በፍጥነት ተቀባይነትን ማግኘት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር የማዳኑን ሥራ የሚገልጥ ታዋቂና አስደናቂ መጽሐፍም ሆኗል ::

በመጽሐፈ አስቴር ትልቅ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰዎች÷ በነገሮች÷ በጊዜያቶች÷ በታሪክና በሕዝቦች ውስጥ የተከናወነበት ነው:: መጽሐፈ አስቴር ስላለፈው ታሪክ የሚነግረን ብቻ ሳይሆን ዛሬም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ትልቅ መልእክት ያለው መጽሐፍ ነው ስለሆነም የመንፈስ መገለጥ መጽሐፍ ምንም ጥርጥር በሌለበት ሁኔታ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ክርስቶስ በምሳሌ የተቀመጠ እውነት እንደሆነ ሁሉ መጽሐፈ አስቴርም ያለ ምንም ጥርጥር የቤተ ክርስቲያን ጥላ ወይም ምሳሌ ሆኖ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የሰፈረ እንደ ሆነ ይህቺን መጽሐፍ አንብበን ስንጨርስ የምንረዳው ነው ::

ቤተ ክርስቲያን የተጠራችበትን ክብር፣ ከክብር የጎደለችውን ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት የተሐድሶን ሥራ እንደጀመረና የመጨረሻዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን እስከ ፍፃሜዋ ድረስ ከማየታችን በፊት በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ የተጠቀሱትንና አሁን ላለችው ቤተ ክርስቲያን በነገር ጥላ ወይም በምሳሌነት የተቀመጡትን ሰዎች በማነፃፀር እንመለከታለን::

## ንጉሥ አርጤክስስ

በብሉይ ኪዳን ከእሥራኤል ንጉሦች ውስጥ በጣም ታዋቂ ከሆኑት አንዱ ንጉሥ ሰለሞን በብዙዎች ዘንድ የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ ይታመናል ይሰበካልም:: ከዚሁ ጋር አያይዞ ንግሥት ሳባ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ እንደሆነች ይነገራል:: በተለይ የመኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን መጽሐፍ ስናነብ ሙሽራው (ክርስቶስ) እንከን ስለማይገኝላት ስለ ሙሽራይቱ (ቤተ ክርስቲያን) ሲገልጽ ሙሽራይቱ ደግሞ ፍፁም ስለሆነው ስለ ሙሽራው በቅኔ በጣም ግሩምና ድንቅ አገላለጽ ተገልጾ እናየዋለን :: መጽሐፍ ቅዱሳችን ንጉሥ ሰለሞን የክርስቶስ ምሳሌ ነው ብሎ በቀጥታ አይነግረንም ነገር ግን





ጌታ ኢየሱስ ከአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነት ለተረዳ ሰው የመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ በምሳሌነቱ የቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ እንደሆነ ያለምንም ጥርጥር ይቀበለዋል:: ስለሆነም ንጉሥ ሰለሞን የክርስቶስ ምሳሌ እንጂ ክርስቶስ አይደለም ጥላ እንጂ እውነተኛ አዳኝ አልነበረም:: ምክንያቱም ከሰለሞን የሚበልጠው እውነተኛው ክርስቶስ ተገልጧልና:: (ማቴ 12÷42)

እንዲሁም ልክ እንደ ንጉሥ ሰለሞን በመጽሐፈ አስቴር ንጉሥ አርጤክስስ የክርስቶስ ምሳሌ ነው:: ምናልባትም የንጉሥ አርጤክስስ ምሳሌነት ለብዙዎቻችን አዲስ ሊሆንብን ይችላል ነገር ግን ይህቺን መጽሐፍ ወደ ውስጥ እያነበብን ስንገባ ከሌሎች የመጽሐፉ ትዕይንቶች ጋር ቁልጭ ባለ መልኩ የምንረዳው ነው :: በተለይ በመጽሐፉ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም አለመጠቀሱ ፀሎትና የሃይማኖት ሥርዓት አለማየታችን ከንጉሡ በላይ የሆነ ሲፈራና ሲመለክ የሚታይ ምንም ነገር አለመኖሩ ንጉሥ አርጤክስስ በመጽሐፈ አስቴር ላይ ተዋናይ ሆኖ ትዕይንቱን የሠራው ሊመጣ ላለው የእውነተኛ አምላክ የክርስቶስ ምሳሌ መሆኑን ያሳየናል:: ምክንያቱም :-

1. ምንም ዓይነት ወደ እግዚአብሔር የቀረበ ፀሎት አለመኖሩ የሚያመለክተው ንጉሥ አርጤክስስ የክርስቶስ ምሳሌ ስለሆነ አስቴር ልመናዋን (ፀሎቷን) ሁሉ የምታቀርበው ወደ ንጉሡ ነበር:: ስለዚህ አስቴር ከንጉሡ ጋር ተነጋገረች ማለት በምሳሌነቱ ቤተ ክርስቲያን ፀሎቷን ሁሉ ወደ ክርስቶስ አቀረበች ማለት ነው ::

2. አይሁዳውያንን ከጠላቶቻቸው የማዳኑ ኃይልና ትእዛዝ መጀመሪያ የሚወጣው ከንጉሡ አርጤክስስ ነበር :: የማዳኑ ኃይል ግን ለሌሎቹ የሚገለጸው ሚስቱ በሆነችው በአስቴር በኩል እያለፈ ነበር:: እንዲሁም ብዙዎችን የሚያድነው ኃይልና ትእዛዝ ከክርስቶስ የሚወጣ ሲሆን ነገር ግን የክርስቶስ የማዳኑ ኃይል ለሌሎች የሚደርሰው ልክ እንደ ንግሥት አስቴር በቤተ ክርስቲያን በኩል ነው::

እንግዲህ ይህንን በመሳሰሉ ሁኔታ ንጉሥ አርጤክስስ እንዴት የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ ሰፋ ባለ መልኩ በዚች መጽሐፍ ውስጥ እንመለከታለን ::

## ንግሥት አስጢን

ንግሥት አስጢን የንጉሥ አርጤክስስ የመጀመሪያ ሚስቱ ናት:: ከዛም ለንጉሡ አልታዘዝም ብላ እምቢ ያለች ሴት ነች:: ያስማችው እምቢ የሚል ድምጽ ንጉሥ አርጤክስስን በጣም አስቆጥቶት ንግሥት አስጢን የንግሥናዋ ማዕረግ እንዲገፈፍና ሚስቱ ተብላ ሁለተኛ እንዳትቀርብ ውሳኔ የተላለፈባት ሴት ነበረች:: ይህቺ ንግሥት አስጢን በመጽሐፈ አስቴር ላይ በቀጥታ ምሳሌነትዋ ከክብር የጎደለችውን ቤተ ክርስቲያን የምታመለክት ናት:: ምክንያቱም ልክ እንደ ንግሥት አስጢን የመካከለኛዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ አልታዘዝም እምቢ በማለት የራሷን ወግና ሥርዓት ስታንጸባርቅ ከእውነተኛው ወንጌል የራቀች በመሆን ንግሥት አስጢን ከንጉሡ እንደተለየች ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ከክርስቶስ የተለየችበት ብዙ ዘመናት ነበር :: ስለዚህ ንግሥት አስጢን ከንጉሡ ክብር ተለይታ በሥራዋ ሙት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት ::

## ንግሥት አስቴር

ንግሥት አስቴር ለሁለተኛ ጊዜ ተፈልጋ የመጣች የንጉሡ አርጤክስስ ሚስት ናት:: አስቴር ንጉሡን በተለየ መንገድ በውበትዋ የማረከች፥ ደስ ያሰኘች ሴትና ንግሥት አስጢን እምቢ ብላ የጣለችውን የንግሥና ዘውድ የደፋች ናት :: ይህ ብቻ ሳይሆን ጠላትዋን ሃማን እስከ መጨረሻ ተዋግታ ድል የነሳችና ለህዝቧ ፍፁም እረፍትን ያመጣች ማሸነፍን እንጂ መሸነፍን የማታውቅ ሴት ናት :: ከዚህም የተነሳ በነገር ሁሉ ከንግሥት አስጢን በተሻለ ሁኔታ የንጉሡ ሚስት የሆነች ናት :: አስቴር በምሳሌነትዋ በቀጥታ የምታመለክተው የመጨረሻዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ነው ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን በመካከለኛው ዘመን ከክርስቶስ ተለይታ ብዙ የዝምታ ዘመናት ያሳለፈች ቢሆንም ነገር ግን እንደገና የተሐድሶ ዘመን ለቤተ ክርስቲያን በመምጣቱ ንግሥት አስቴር ተፈልጋ እንደመጣች ሁሉ እግዚአብሔር እንደገና የወንጌልን እውነት ይዘው የሚያገለግሉትን ሰዎች ፈልጎ አስነሳ:: ከዚያም በየዘመናቱ የወንጌል እውነቶች እየታደሱ አሁን ቤተ ክርስቲያን ያለችበት ደረጃ ላይ ደርሰናል :: ንግሥት አስቴር የንግሥናዋን ዘውድ ደፍታ ጠላትዋን ሙሉ በሙሉ እንደረገጠች ቤተ ክርስቲያን ከአሁን በኋላ የሚጠብቃት የንግሥናዋን ዘውድ ደፍታ ጠላቶችዋን ሙሉ በሙሉ መርገጥ ነው :: እንዲሁም ንግሥት አስቴር በነገር ሁሉ ከንግሥት አስጢን እንደምትሻል ሁሉ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንዲሁ ከፊተኛው





ዘመን እጅግ የተሻለች ናት ምክንያቱም ከፊተኛው ቤት ክብር ይልቅ የኋለኛው ቤት ክብር እጅግ ይበልጣል (ሐጌ 2÷9) ስለዚህ አስቴር የንግሥናዋን ዘውድ ደፍታ ሙሉ ለሙሉ ጠላቶችዋን የምትረግጠው የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት::

## መርዶክዮስ

ንግሥት አስቴርን ያሳደጋትና ለንጉሡም ሚስት እንድትሆን ወደ ንጉሡ ያቀረባት ነው:: ይህ ማለት የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ የሆነችውን አስቴርን ያሳደጋት እንዲሁም የክርስቶስ ምሳሌ ከሆነው ከንጉሥ አርጤክስስ ጋር አንድ አካል እንድትሆን ወደ ንጉሡ ያቀረባት መርዶክዮስ ነው :: በተመሳሳይ መልኩ ሰዎችን በወንጌል ማርከ ወደ ክርስቶስ የሚያቀርበው መንፈስ ቅዱስ ነው :: እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር አንድ አካል እንዲሆኑ የአካል ጥምቀትን የሚያጠምቅ መንፈስ ቅዱስ ነው :: (1ቆሮ 12÷13) ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት እንደ ጥላ ወይም ምሳሌ ሆኖ ሲያገለግል እንመለከታለን:: ይህ ብቻ አይደለም መርዶክዮስ በጣም የታወቀበት ምክንያት የክርስቶስ ምሳሌ የሆነውን ንጉሥ አርጤክስስን ከሞት በማዳኑ ነው :: በሮሜ መልእክት እንደምንመለከተው ኢየሱስ ክርስቶስን ከሞት ያስነሳው የእግዚአብሔር መንፈስ ( መንፈስ ቅዱስ ) እንደሆነ ይነግረናል :: (ሮሜ 8÷11) እንዲሁም ደግሞ መርዶክዮስ ንጉሥ አርጤክስስን ከሞት አድኖአል "አንተን (ንጉሡን) <u>ከሞት ያዳነ መርዶክዮስን</u> ..."(አስ7÷9) ስለዚህ ንጉሥ አርጤክስስን ከሞት ያዳነው መርዶክዮስ ኢየሱስን ከሞት ያስነሳው የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው::

## ጃንደረቦች

በመጽሐፈ አስቴር ላይ የጃንደረቦችን አገልግሎት ስንመለከት የመጨረሻ ዘመን ምሳሌ የሆነችውን አስቴርን ማገልገልና እርስዋ ለንጉሡ መልካም ሚስት እንድትሆን በነገር ሁሉ መርዳት ነው:: አስቴር በመርዶክዮስ አማካይነት ንጉሡ ወዳለበት ቤተ መንግሥት ስትመጣ እርስዋን ለማስተናገድ መጀመሪያ የተቀበላት ጃንደረባው ነበር :: ልክ እንደዚሁ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በክርስቶስ ሥራ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስንገባ እኛን ለማገልገል ለመጠበቅና በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ለመርዳት በመጀመሪያ የሚያገኙን መላእክት ናቸው:: (ዕብ 1÷14) ስለዚህ

ጃንደረቦቹ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ መላእክት ምሳሌ ናቸው:: ሌላው ጃንደረቦቹ የመላእክት ምሳሌ የሆኑበት አያገቡም አይጋቡም መላእክትም እንዲሁ:: በተጨማሪም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ያሉ ጃንደረቦች የንጉሡን ትእዛዝ ብቻ ነው የሚፈጽሙት በሰዎችና በንጉሡ መካከል ገብተው የሰዎችን ነገር ለንጉሡ አያቀርቡም ነገር ግን የወጣውን የንጉሡን ትእዛዝ ተቀብለው ንጉሡንና ሕዝቡን ያገለግላሉ:: በሌላ አገላለጽ መካከለኛ አይደሉም መካከለኛ ሆኖ በቆመው በክርስቶስ ሥራ አገልግሎታቸውን ይፈጽማሉ ::

## <u>ሃማን</u>

ሃማን የጠላታችን የሰይጣን ምሳሌ መሆኑን ለሁላችንም ግልጽ ነው:: ነገር ግን የሃማን ጥልቅ የሆነውን ምስጢራዊ አሠራር ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው :: ይህንን ምስጢር ካወቅን አሁን ቤተ ክርስቲያንን የሚዋጋትን መንፈስ ጠንቅቀን እናውቀዋለን:: የሃማን ምስጢራዊ የሰይጣን አሠራር በግብጽ ውስጥ በአንድ የመሪዎች መንፈሳዊ ፕሮግራም ላይ ትልቅ የማስተማር ፀጋ ባላቸው በዶ/ር መከዲ በኩል እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ሲያስተምረን ስለ ሃማን ያለኝን እውቀት መንፈስ ቅዱስ በልዩ ልዩ መንገድ ገልጾ አስተማረኝ:: የሃማን ማንነት፣ ሥራና እንዲሁም አመጣጡን በደንብ ለመረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ክፍሎችን ከዚህ በመቀጠል እናያለን::

እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ዕቅድ ለፈጠረው ሕዝብ እንዳለው ሁሉ ሰይጣንም የራሱ ዕቅድ አለው:: የእግዚአብሔር ዕቅድ የሰይጣንን ራስ ቀጥቅጦ ለሕዝቡ ደህንነትን ማውረስ ሲሆን የሰይጣን ዕቅድ ደግሞ የእግዚአብሔርን ዕቅድ (ሥራ) እውነት በሚመስል ውሸት ማበላሸት ነው :: እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን የሰጣቸውን ዕቅድ ሰይጣን በውሸት ካበላሸው በኋላ እግዚአብሔር እንደገና አዳምና ሔዋን የጣሉትን ዕቅድ ለማንሳት ተስፋን ሰጠ ተስፋውም :-

> " በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነት እንዲኖር
> አደርጋለሁ :: የእርስዋ ዘርና የአንተ ዘር ዘወትር ጠላቶች
> እንደሆኑ ይኖራሉ የእርስዋ ዘር የአንተን ራስ ይቀጠቅጣል
> አንተም የእርስዋን ዘር ተረከዝ ትነክሳለህ" (ዘፍ 3፥15)





ይህም ተስፋ ከሴቲቱ የሚወለድ ማለትም ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ እየተሸጋገረ ሥጋን ለብሶ ከድንግል ስለሚወለደው የሰይጣንን ራስ ስለሚቀጠቅጠው ስለ ክርስቶስ የተሰጠ ተስፋ ነበር ::

የእግዚአብሔር ዕቅድ የእባቡን (የሰይጣንን) ራስ መቀጥቀጥ ነው:: እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እውን ለማድረግ ሥጋ የለበሰ ሰው ይፈልጋል:: እንዲሁ ሰይጣን የራሱን ዕቅድ ማለትም የእግዚአብሔር ዕቅድ በዚህ ምድር እንዳይገለጽ የሚዋጋበትን ሥጋን የለበሰ ሰው ይፈልጋል:: የእግዚአብሔር ዕቅድ (ተስፋ) ባለበት ቦታ ሁሉ ሰይጣን ያንን ተስፋ ለማበላሸት የሚጠቀምበት የራሱ ትውልድ አለው:: በዘፍጥረት ምዕራፍ 4፥1-8 እግዚአብሔር ዕቅዱንና ተስፋውን የሚፈጽምበት የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጠው ከእርሱ እንዲመጣ አቤልን መረጠ:: በተመሳሳይ ጊዜ የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚያበላሽና ከምድረ ገጽ የሚያጠፋ የሰይጣን አሠራር በቃየን ተገለፀ ወንድሙንም ገደለ :: የእግዚአብሔርን ዕቅድ አበላሸ ስለዚህ በዘፍጥረት ሦስት ላይ እባቡ እንደተረገመ ሁሉ ቃየንም ተረገመ::

> "የተረገምህ ሁን ወንድምህን በገደልከው ጊዜ አፍዋን
> ከፍታ ደሙን በጠጣችው ምድር ላይ ተቅበዝበዝ"
> (ዘፍ 4፥11)

እንደገና ተስፋውንና ዕቅዱን ይዞ እንዲነሳ እግዚአብሔር አብርሃምን መረጠ:: አብርሃም ከእርሱ በሚወለደው በዘሩ የምድር ሰዎች ሁሉ እንደሚድኑ ተስፋን ተቀበለ:: ያም ዘር ክርስቶስ ነበረ:: (ገላ 3፥14) ነገር ግን ይስሐቅ ከመምጣቱ በፊት የክርስቶስን ዘር ሊያጠፋ በአጋር በኩል የሰይጣንን አሳብ የያዘ እስማኤል ተወለደ:: (ዘፍ16፥11-12) እስማኤል ጠርነትን፣ ማጥፋትን፣ ማበላሸትን፣ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማሳደድ የሚወድ ነበር:: እግዚአብሔር አብርሃምን ተስፋውን የሚያበላሽ ከተስፋው ልጅ ጋር አብሮ መቀመጥ አይችልምና አጋርን ከነልጅዋ አባርር አለው :: (ገላ 4፥28-31) አብርሃም እስማኤልን አባረረ:: ባያባርር ኖሮ ተስፋውን ያበላሽና ይደመስስ ነበር ::

የተወለደው ይስሐቅ የእግዚአብሔር ዕቅድ (ተስፋ) ማስፈፀሚያ ዘሩ ነበር:: ስለዚህ ሚስቱ ርብቃ መንታ ልጆችን ፀንሳ ሳለ ገና በማህፀን ሳሉ

እርስ በርሳቸው ይገፋፉ ነበር:: ይህም ነገር ርብቃን አስጨንቋት በፀለየች ጊዜ እግዚአብሔር :-

> “ በማሕፀንሽ ያሉት ሁለት ሕዝቦች ናቸው :: እርስ በርሳቸው የማይስማሙ ሁለት ወገኖች ትወልጃለሽ :: አንዱም ከሌላው የበረታ ይሆናል ታላቁም ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል ” ( ዘፍ 25÷23)

የእግዚአብሔር ቃል ስለነዚህ ሁለት ወገኖች (ሕዝቦች) ሲነግረን ያዕቆብ በቤት ውስጥ መዋል የሚወድ ጭምት ነበር:: ኤሳው ግን በዱር መዋል የሚወድ አዳኝ (ጦረኛ) ነበር ይለናል:: ኤሳው የእግዚአብሔርን ዕቅድ ይዞ በተነሣው በያዕቆብ ላይ በጠላትነት ተነሳ:: ወንድሙንም ሊገድለው ፈለገ:: ምንጊዜም የእግዚአብሔርን ዕቅድ÷ አሳብ (ተስፋ) ባለበት ስፍራ የክርስቶስን ነገር ለማበላሸት ከምድር ላይ ለማጥፋት ክርስቶስ የሚባል ስሙም ዘሩም እንዳይኖር ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የመጣ የክርስቶስና የአካሉ የቤተ ክርስቲያን ጠላት አለ:: ቃየል፣ እስማኤል፣ ኤሳው የሥጋዊ ክርስቲያን ምሳሌዎች ብቻ አይደሉም :: ነገር ግን የክርስቶስና የአካሉ የቤተ ክርስቲያንን መምጣት የሚቃወም የፀረ ክርስቶስ መንፈስ ምሳሌዎች ናቸው::

ከዚህ በኋላ ያለውን አሳብ በደንብ አድርገን እንመልከት:: የእግዚአብሔርን ዕቅድ የያዘውን ያዕቆብን ሊያጠፋ የተነሣው ኤሳው ሒታዊያንን አገባ::(ዘፍ 26÷34) ይህ ብቻ አይደለም ተስፋ የተቀበለውን ይስሐቅን ሊያጠፋ ከተነሳው ከእስማኤል ልጅ ጋር ተጋባ:: (ዘፍ 28÷9) ከሒታዊያን ሴቶች የዓዳ ከምትባለው ሚስቱ የመጀመሪያ ልጁን ኤልፋዝን ወለደ :: ኤልፋዝም የጭን ገረድ ከሆነችው ከቲምናዕ <u>ዐማሌቅን</u> ወለደ :: ስለዚህ ከኤሳው ዘር ኤልፋዝ ተገኘ :: ከኤልፋዝ ዘር ደግሞ የነገድ አለቆች ነበሩ :: ከነዚህም ውስጥ ቴማን÷ አማር÷ ጸፎ÷ ቀናዝ÷ ቆራሕ÷ ገዐታምና <u>ዐማሌቅ</u> ነበሩ::(ዘፍ 36÷12-16)

ከእነዚህ ነገድ ውስጥ የክርስቶስን ሥራ ለማበላሸትና ለመደምሰስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በምድረ በዳ ለማጥፋት በቃየን፣ በእስማኤልና በኤሳው የነበረው አሳብ <u>በዐማሌቅ</u> ላይ አረፈ:: ከዚህም በኋላ ዐማሌቅ የእግዚአብሔር ሕዝብ ዋነኛ ጠላት ሆኖ ተገኘ:: ሌሎች ነገዶች ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የሚዋጉበት የተለያየ ምክንያት የነበራቸው





ሲሆን ዐማሌቅ ግን የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጠውን ክርስቶስ የሚመጣበትን ዘር ለማበላሸት÷ ለማጥፋትና በዚህ ምድር ላይ መታሰቢያ እንዳይኖረው በተለየ መንገድ የሚዋጋ መንፈስ ነበር ::

የእግዚአብሔር ሕዝብ ከግብጽ ከባርነት ቤት ሲወጡ ዐማሌቅ ተዋጋቸው:: የዐማሌቅ አመጣጡ እስራኤላውያንን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ነበር:: እግዚአብሔርም በእርሱ ዕቅድ ላይ የወጣ መንፈስ ስለሆነ ዐማሌቅን መታሰቢያ እስከማይኖረው ድረስ እደመስሰዋለሁ አለ:: ሙሴም ተነስቶ “ እግዚአብሔር ዐማሌቃውያንን ለዘላለም ይዋጋቸዋል” አለ:: (ዘፀ17÷8-16) የዐማሌቅ መንፈስ በግልጽና በስውር ቤተ ክርስቲያንን ስለሚዋጋ እስከ ዛሬ እግዚአብሔር ዐማሌቃውያንን ይዋጋል:: እግዚእብሔር ሙሴን እንደገና ዐማሌቅን ፈጽሞ ማጥፋት እንዳለበት ትእዛዝ ሰጠው::

> “ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችሁ ምድሪቱን አውርሶአችሁ በዙሪያችሁ ከሚኖሩ ጠላቶቻችሁ ሁሉ በሚያሳርፋችሁ ጊዜ በምድር ላይ ማንም የሚያስታውሳቸው እስኪጠፉ ድረስ ዐማሌቃውያንን ሁሉ ይደምስሱ ይህን ከቶ አትርሱ ” (ዘዳ 25÷19)

እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ በማስጠንቀቂያ ቃል <u>“ከቶ አትርሱ”</u> ብሎታል:: ምክንያቱም ዐማሌቅ ካልተደመሰሰ የእግዚአብሔርንዕቅድ ለመደምሰስ ይነሳልና ነው :: በሳኦል ዘመነ መንግሥትም እግዚእብሔር ዐማሌቅን ለመቅጣት በወሰነ ጊዜ በነቢዩ ሳሙኤል በኩል ለሳኦል ትእዛዝ ሰጠው ::

> “እግዚአብሔር ዐማሌቃውያንን ለመቅጣት ወስኖአል:: እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡበት ጊዜ የእነዚህ የዐማሌቃውያን የቀድሞ አባቶቻቸው ተቃውመዋቸው ነበር:: ሂደህ በዐማሌቃውያን ላይ አደጋ በመጣል ያላቸውን ሁሉ ደምስስ ከነሱ ምንም ነገር አታስቀር ወንዶችን፣ ሴቶችን፣ ልጆችንና ህፃናትን፣ ከብቶችን፣ በጎችን፣ ግመሎችንና አህዮችን ሁሉ ግደል::” (1ሳሙ 15÷2-3)

እግዚአብሔር ዐማሌቃውያን መታሰቢያ እንዳይኖራቸው ከምድረ ገጽ እንዲጠፉ ይፈልጋል :: ደግሞም ዐማሌቅን ለዘላለም ለመዋጋት ወስኖአል::

ሳኦል ግን እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ አልፈፀመም :: ዐማሌቃውያንን ከምድረ ገጽ አላጠፋም ነበር::

> "የዐማሌቅ ንጉሥ የነበረው አጋግ በሕይወት ማርኮ ሕዝቡን ሁሉ ፈጀ :: ነገር ግን ሳኦልና ሠራዊቱ የአጋግን ሕይወት አተረፉ :: እንዲሁም ምርጥ ምርጥ የሆኑትን በጎችና የቀንድ ከብቶች፤ የሰቡ ሠንጋዎችና ጠቦቶችን ከዚህም ጋር መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ አላጠፉም :: እነርሱም ያጠፉት የማይረባውንና የማይጠቅመውን ነገር ብቻ ነበር::" (1ሳሙ15÷8-9)

ሳኦል የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያበላሸውን የክርስቶስን መንፈስ የሚቃወመውን ዋናውን የዐማሌቅን ንጉሥ አጋግንና በዐማሌቅ መንፈስ የተያዙ ያልተቀደሱ የቀንድ ከብቶች ፤ የሰቡ ሠንጋዎችና በጎችን ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ወደ ተቀደሰ ምድር አስገባ:: እንዲያውም ከብቶቹን ለእግዚእብሔር መስዋእት አድርጎ ሊያቀርባቸው ወደደ:: በዚህ ምክንያት እግዚእብሔር ሳኦልን በማንገሡ ተጸጽቶ ከንጉሥነት ክብር ሻረው:: እግዚአብሔር በዐማሌቅ መንፈስ ላይ ከፍተኛ የሆነ አቋም አለው:: ምክንያቱም ዐማሌቅ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ሊያደርጋቸው ባለው ዕቅድ ላይ የሚወጣና ለማጥፋት የሚነሣ ስለሆነ እግዚአብሔር ደግሞ ዐማሌቃውያንን ወደ ተቀደሰ ሰፍራ በሚያመጡ እንደ ሳኦል ባሉ ላይ ወዲያው ነው የውሳኔ ቃሉን የሚያሰማው :: ሳሙኤልም ሳኦል ወደ ተቀደሰ ስፍራ ያስገባውን ንጉሥ አጋግን አምጡልኝ አለ :: ነቢዩ ሳሙኤልም ለአጋግ እንዲህ አለው " የአንተ ሰይፍ ብዙዎች እናቶችን ልጅ አልባ እንዳደረገቻቸው፤ የአንተም እናት ልጅ አልባ ሆና ትቀራለች" አለው:: ከዚህ በኋላ በጌልገላ በሚገኘው በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት አጋግን ቆራርጦ ጣለው (1ሳሙ 15÷33)

እዚህ ላይ የምንመለከተው ትልቅ የሆነውን የዐማሌቅን አሠራር ነው:: ንጉሥ አጋግ እርሱ ራሱ ዐማሌቅ ነበር:: የክርስቶስን ሥራ የእግዚአብሔርን ዕቅድ በሚያበላሽ መንፈስ የተያዘ ነበር የእርሱም ሰይፍ ብዙ እናቶችን ልጅ አልባ ያደረገ ነው:: ብዙ እናቶች ልጆቻቸውን በማሳደግ ላይ ሳሉ ንጉሥ አጋግ እየመጣ ልጆቻቸውን ከእነርሱ ይነጥቃል:: ሥራውም ማጥፋትና ማበላሸት ነውና:: አማሌቁ ሃማን የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ የሆኑትን ያውም ልጆች ያፈሩትን በሰይፍ ያጠፋ እንደነበር ሁሉ ዛሬም ቤተ ክርስቲያንን





የሚዋጋበት አሠራሩ ሁሉ ተመሳሳይ ነው ይኸውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ያፈሩትን ፍሬና ያላቸውን ፀጋ የሚያስጥል÷ የሚነጥቅ÷ የሚገድልና የሚያጠፋ ነው ::

እንግዲህ ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ሳኦል ዘመነ መንግሥት ዐማሌቅ ምሳሌነቱ ሊገለጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ በመቃወም÷ በማፈራረስና በማበላሸት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከምድረ ገፅ ለማጥፋት የሚነሳውን የሰይጣን አሠራር የሚወክል ነው :: እንዲሁም በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚወጣው የዚህ መንፈስ ምሳሌ የሆነው ሃማን ሳሙኤል የገደለው የንጉሥ አጋግ ዝርያ ነበር :: ንጉሥ አጋግም ዐማሌቅ ነበር :: ሃማን የአጋግ ዝርያ ስለሆነ ዐማሌቅ ነው :: "..የሃማን አባት ሃማዳታ ተብሎ የሚጠራው የአጋግ ዝርያ ነበር " (አስ 3÷1 እና 10) ይላል:: ስለዚህ በመጽሐፈ አስቴር ጥናታችን ሃማን እንዴት የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማጥፋት እንደተነሣና በመጨረሻም እግዚአብሔር ለዘላለም ስለሚዋጋው በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የእግርዋ መረገጫ በመሆን መታሰቢያ እስከማይኖረው ድረስ ከምድረ ገፅ እንደጠፋ እንመለከታለን::

# ም ዕ ራ ፍ ሁ ለ ት

## ቤተ ክርስቲያን
## የተጠራችበት
## የክብር ስፍራ

“ ከዚህ በኋላ ንጉሥ አርጤክስስ በመናገሻ ከተማ በሆነችው በሱሳ በሚኖሩ ሁሉ ለሀብታሞችም ለድኾችም እንደገና ሌላ ግብዣ አደረገ በቤተ መንግሥቱ የአትክልት ቦታ የተደረገው ያ ግብዣ አንድ ሳምንት ሙሉ ቆየ :: በዚያም የነበረው አደባባይ ከነጭ ጥጥ በፍታ በተሠሩ ሰማያዊ ቀለም ባላቸው መጋረጃዎች የተጌጠ ነበር:: መጋረጃዎቹም ከሐምራዊ በፍታ በተሠሩና የብር ቀለበት በተበጀላቸው ገመዶች በዕብነ በረድ ምሰሶዎች ላይ ተንጠልጥለው ነበር :: ከወርቅና ከብር የተሠሩ ድንክ አልጋዎችም ነጭና ቀይ ቢጫና ሰማያዊ ቀለማትን በሚፈነጥቅ የዕብነ በረድ ወለል ላይ ተደርድረው ነበር አንዱ ከሌላው ጋር በማይመሳሰል በልዩ ልዩ የወርቅ ዋንጫ መጠጥ ይታደል ነበር :: ንጉሡም የቤተ መንግሥቱ የወይን ጠጅ በልግስና እንዲሰጥ አደረገ :: ለመጠጡም ብዛት ገደብ አልነበረውም ንጉሡም ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን ያህል መጠጣት ይችል ዘንድ ለቤተ መንግሥቱ አገልጋዮች ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር::” (አስ 1÷5-8)

ከዚህ በላይ ባለው የመጽሐፈ አስቴር የንባብ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትና ልናያቸው የሚገባንን ቤተ ክርስቲያን የተጠራችበትን ክብር የሚገልጹ ጠቃሚ እውነቶችን አንድ በአንድ እንመለከታለን ::

# ለሀብታሞችና ለድኾች የተዘጋጀ ግብዣ

በዘመናችን የሚደረጉ ግብዣዎች ብዙ ዓይነት ባህሪዎች አላቸው:: ብዙዎቹ ጋባዦች በግብዣቸው ላይ የሚጠሩት ይጠቅመናል የሚሉትን እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል:: በተለይ በዚህ ዘመን የአሳብ መበላለጥ ጎልቶ በሚታይበት ድብቅ የዘረኝነትና የቀለም ጥላቻ በሚካሄድበት ሰዎችም የጎሪጥ በሚተያዩበት ዘመን የግብዣ ጥሪዎችም ይህንን ስልፍ ተከትለው በመሄድ ብዙ ልዩነት ያደርጋሉ :: ብዙ ነገር የተሟላላቸው ናቸው የሚባሉት የዘመናችን ሀብታሞች÷ ነገሥታት እንዲሁም መንግሥታት ግብዣዎቻቸው የቱንም ያህል የተሳካለት ቢሆንም የተሟላ አይደለም





የንጉሥ አርጤክስስ ግብዣ ግን ከዚህ የተለየ ነበር :: ምሳሌነቱም በሉቃስ ወንጌል እንደተጠቀሰው የራት ግብዣ አዘጋጅቶ ጥሪ ከጠራው ሰው ጋር ይመሳሰላል::

“ኢየሱስ ግን እንዲህ አለው አንድ ሰው ትልቅ የራት ግብዣ አዘጋጅቶ ብዙ ሰዎችን ጠራ” (ሉቃ 14÷16)

እንዲሁም “ መንግሥተ ሰማይ ለልጁ ሠርግ ያዘጋጀ ንጉሥ ትመስላለች::” (ማቴ 22÷2) (የቀ.ት)

መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ 1÷5 ላይ ንጉሡ ታላቅ ግብዣ አዘጋጀ:: የንጉሡን ግብዣ ለድኾችም ለሀብታሞችም የተዘጋጀ ነበር :: ይህም ጌታ የተናገረው የመንግሥተ ሰማያት ግብዣ ምሳሌ ነው:: በዚህ ግብዣ ላይ ሰው ሁሉ ድኸው÷ ሀብታሙ÷ የተማረውም÷ ያልተማረውም÷ ከቋንቋና ከዘር የተጠራበት ነበር ::

ምክንያቱም የግብዣውን ሁሉን አቀፋዊነት በማስመልከት ሐዋርያው ጳውሎስ ለቲቶ በቲቶ 2÷11 ላይ “ ስዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ፀጋ ተገልጦአል” ብሎት እንደነበር መመልከት ይቻላል :: ስለዚህ የንጉሥ አርጤክስስ ግብዣ ሰዎች ሁሉ የተጠሩበት የመንግሥተ ሰማይ ግብዣ ምሳሌ ነው::

# በአትክልቱ ቦታ የተሰወረው ታላቅ ሀብት

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምድር ላይ በተመላለሰበት ጊዜ ለተከታዮቹም ሊያስተውሉት በሚችሉ በአካባቢያቸው ባሉ ነገሮች ምሳሌ እየተጠቀመ ያስተምራቸው ነበር :: በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ መንግሥተ ሰማያትን በእርሻ ውስጥ ከተሰወረ ሀብት ጋር አወዳድሮ ያስተማረው ትምህርት ከብዙዎቹ መካከል አንዱ ነው ::

“ ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ መንግሥተ ሰማይ በእርሻ ውስጥ የተሸሸገውን ሀብት ትመስላለች አንድ ሰው ይህን ሀብት ባገኘ ጊዜ መልሶ ደበቀው ከደስታውም ብዛት የተነሣ

ሄደና ያለውን ሁሉ ሸጦ ያንን እርሻ ገዛ እንደገናም ኢየሱስ እንዲህ አለ መንግሥተ ሰማይ ጥሩ ዕንቁ ለመግዛት የሚፈልግ ነጋዴን ትመስላለች ነጋዴውም እጅግ ክቡር የሆነ ዕንቁ ባገኘ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያንን ዕንቁ ገዛ"

(ማቴ13÷44-45)

እንዲሁም ንጉሥ አርጤክስስ በአትክልቱ ስፍራ ያደረገው ታላቅ ግብዣ ብዙ ሀብትና ክብር ያለበት ስፍራ ጌታም እንዳለው ያለንን ሁሉ የሚያሸጥ የተሰወረ ሀብት በንጉሡ በአርጤክስስ ግብዣ ላይ በአትክልቱ ስፍራ ነበር :: ከነዚህ ሀብቶች መካከል የመጀመሪያው መጋረጃዎቹ ሲሆኑ እነዚህንም ከዚህ በመቀጠል እንመለከታቸዋለን:-

## ሀ) መጋረጃዎቹ

" በዚያም የነበረው አደባባይ ከነጭ ጥጥ በፍታ በተሠሩ ሰማያዊ ቀለም ባላቸው መጋረጃዎች የተጌጠ ነበር::"
(አስ 1÷6)

በንጉሥ አርጤክስስ የክብር ግብዣ ላይ ከሚገኙት ታላላቅ ሀብት መካከል የመጀመሪያዎቹ በነጭ÷ በሰማያዊና በሐምራዊ ቀለማት ያሸበረቁ መጋረጃዎች ነበሩ :: መጽሐፍ ቅዱሳችን ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ ነው ይለናል በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ለሰዎች የፈፀማቸው ድርጊቶችና የሰጣቸው መንፈሳዊ በረከቶች በብሉይ ኪዳን በምሳሌ መልክ የተቀመጡ ናቸው:: ይህንን ከተረዳን መጋረጃዎቹ የሚያመለክቱት ክርስቶስ ሥጋን ለብሶ መምጣትና ስለእኛ በመስቀል ላይ መሞቱ የሥጋው መቆረስ የደሙ መፍሰስ ወደ እግዚአብሔር ሰማያዊ ክብር የሚያደርሰንን የመስቀሉን ሥራ የዕብራውያን ፀሀፊ መጋረጃ ብሎ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል :-

"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን..."

(ዕብ10÷19-20)(የቀ.ት)





በንጉሥ አርጤክስስ ግብዣ ላይ የነበሩ መጋረጃዎች በነጭ÷በሰማያዊና በሐምራዊ ቀለሞች ያሸበረቁ ሲሆኑ ነጭ ቀለም ምሳሌነቱ ክርስቶስ ጽድቃችን መሆኑን የሚገልጽ ነው :: ሰማያዊው ደግሞ በክርስቶስ የሚገኝ የሰማያዊ አገር ዜግነት የሰማያዊ በረከት ተካፋዮች መሆናችንን የሚያረጋግጥ ነው:: በክርስቶስ የሚገኘው ጽድቅና በረከት ለሰው ልጆች ግልጽ ሆኖ እንዲታይና በዚህም ጽድቅና ሰማያዊ በረከት ሰዎች እንዲያልፉ እንደ መጋረጃ ሆኖ የተንጠለጠለው ሐምራዊ ቀለም ባላቸው ገመዶች ነበር :: ሐምራዊ ማለት ደም የሚመስል ቀይ ማለት ሲሆን በምሳሌነቱ በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስን ደም ያመለክታል :: እዚህ ላይ የምንመለከተው ትልቅ ነገር በክርስቶስ አማካኝነት የተገኘው ጽድቅና ሰማያዊ በረከት ከላይ ወደ ታች ለሰው ልጆች የተንጠለጠለው በክርስቶስ ደም አማካኝነት መሆኑን ነው :: መጋረጃዎቹ እርስ በርሳቸው እንደተያያዙ የክርስቶስ ደሙ÷ ጽድቅና ሰማያዊ በረከቱ ሁሉም በአንድ ላይ የተያያዙ ናቸው:: ያለ ደሙ ጽድቅንና ሰማያዊ በረከትን መውረስ አይቻልም ::

ስለዚህ ማንም ሰው ወደ ንጉሡ ግብዣ ሲመጣ በመጀመሪያ የሚያገኘው የተሰወረ ትልቅ ሀብት ኃጢአተኝነትና ዓለማዊ ምኞትን የሚያስክድ ከኲነኔና ከመርገም ነፃ በሚያወጣ አቻና ወደር በማይገኝለት በጌታችን በኢየሱስ ደም ታጥቦ መንፃት ነው :: (ቲቶ2÷11-14) እንዲሁም የተገባን ሆነን ነጭ ልብስ ለብሰን ከጌታ ጋር ለዘላለም ሊያኖረን የሚያስችለንን የክርስቶስን ጽድቅ መልበስ :: (ሮሜ3÷22-25) በተጨማሪም በክርስቶስ የተገኘውን ሰማያዊ በረከት ተካፋዮች መሆን ነው ::(ኤፌ1÷3 ፤ 2÷7) ማንም ሰው እነዚህን መጋረጃዎች ሳያልፍ በንጉሡ የማዕድ ግብዣ ላይ መቀመጥ አይችልም:: (ማቴ22÷11-13) እንግዲህ መጋረጃዎቹ በጌታችን በኢየሱስ ደም በእርሱ ጽድቅ የሰማያዊ አገር ዜጎች የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች እንድንሆን የሚያበቁን የደሙን መፍሰስ የሥጋውን መቆረስ የሚያመለክቱ የመስቀሉን ምስጢር የያዙ ናቸው ::

## ለ) የዕብነ በረድ ምሰሶዎች (ዓምድ)

" ....መጋረጃዎቹም በሐምራዊ በፍታ በተሠሩ የብር ቀለበት በተበጀላቸው ገመዶች በዕብነ በረድ ምሰሶዎች ላይ ተንጠልጥለው ነበር ..." (አስ1÷6 )

በዚህ ጥቅስ ላይ እንደምንረዳው መጋረጃዎቹ የተንጠለጠሉት በዓምዱ ላይ ነበር:: መጋረጃውን ማለትም ደሙን÷ ጽድቁንና ሰማያዊ በረከቱን ለሰው ልጆች እንዲታይ ከፍ አድርጎ የያዘው ዓምዱ ነው :: ይህ ዓምድ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው :: ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ ስለመንፈስ ቅዱስ ሲገልጽላቸው " እርሱ በመጣ ጊዜ ስለ ኃጢአት÷ ስለ ፍርድና ስለ ጽድቅ ሰዎችን ያስረዳል" :: እንዲሁም "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ...እኔን ያከብረኛል ":: (ዮሐ16÷8-14) ስለዚህ ዓምዱ መጋረጃውን ከፍ አድርጎ በማንጠልጠል የክርስቶስን ደም÷ ጽድቅና በእርሱም የሚገኘውን ሰማያዊ በረከት በማሳየት በዚህ ምድር ላይ ክርስቶስን በማክበር ለሰው ልጆች የመስቀሉን ሥራ መግለጥና ማሳየት ነው::

ሌላው ይህ ዓምድ ቤተ ክርስቲያንን የሚመራ ዓምድ ነው :: ማንኛውም ሰው ግብዣውን አክብሮ ከመጣ እጅግ ውብና ድንቅ በሆነ በመጋረጃው በኩል በማለፍ ያለ እንዳች ዋጋ እንዲያው በፀጋው መዳን ያገኛል :: (ኤፌ2÷8) ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በመጋረጃው በኩል ለማለፍ ብቻ የተጠራች ሳትሆን መጋረጃውን ከያዘው ከዓምዱ ፊት ለፊት ልትቀመጥ የተጠራች ናት:: እስራኤላውያን የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ወይም ጥላ ናቸው :: እነርሱን በምድረበዳ ቀን በደመና ዓምድ ሌሊት በእሳት ዓምድ የመራቸው ዛሬም ቤተ ክርስቲያን በተጠራችበት የክብር ሥፍራ አለ :: ይህ ዓምድ እንዲሁ ዝም ብሎ ለዕይታ ብቻ የቆመ ሳይሆን ሕያው ሆነው መጋረጃውን አልፈው የገቡትን ሰዎች ለመምራት ፊት ለፊታቸው የቆመ ዓምድ ነው ::

ዓምዱ ቀን በደመና ማድረግ የሚገባንን የሚነግረንና በሌሊት የጠላት አሠራር በበዛበት እንኳ በእሳት እየተገለጠ ሕዝቡን የሚመራ ዓምድ ነው ::

> "ከሱኮትም ተጓዙ በምድረ በዳውም ዳር በኤታም ሰፈሩ በቀንና በሌሊትም ይሄዱ ዘንድ መንገድ ሊያሳያቸው ቀን በደመና ዓምድ ሊያበራላቸው ሌሊት በእሳት ዓምድ እግዚአብሔር በፊታቸው ሄደ:: " (ዘፀ 13÷20-22)(የቀ.ት)

የደመና ወይም የእሳቱ ዓምድ ሲነሳ የእስራኤልም ሕዝብ አብሮ ይነሳ ነበር :: ዓምዱ አንድ ቀንም ቢሆን አንድ ወርም ካልተንቀሳቀሰ እነርሱም አይንቀሳቀሱም ነበር :: ምክንያቱም የሚመራቸው ዓምድ ከፊት





ለፊታቸው ያለውን ነገር ሁሉ የሚያውቅ ነበርና :: ይህ ዓምድ የቤተ ክርስቲያን ክብርዋና ጌጥዋ ነው :: ቤተ ክርስቲያን ክብር አላት ጌጠኛም እንድትሆን ተጠርታለች:: በተጨማሪም የገሃነም ደጆች የማይቋቋሙዋት ጠንካራም ነች :: እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ክብሯ ጌጧና ጥንካሬዋ ከፊት ለፊት የቆመው ዓምድ ነው :: መጋረጃውን ካለፍን በኋላ በዓምዱ ፊት ለፊት ስንቀመጥ ከዓምዱ በሚወጣው እሳታማዊ ነፀብራቅ ቤተ ክርስቲያን ከክብር ወደ ክብር የምትለወጥ ናት እንጂ የዚያን ይሻር የነበረውን መጨረሻ ትኩር ብለው የእስራኤል ልጆች እንዳይመለከቱት በፊቱ መጋረጃ እንዳደረገው እንደ ሙሴ አይደለንም:: የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ጌታ በመረቀላት በአዲስና በሕያው ጎዳና ምህረቱንና ማለቂያ የሌለውን የጌታን ክብር ትኩር ብላ የምትመለከት ናት ::

> "ጌታ ግን መንፈስ ነው የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ እኛ ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያንን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን::" (2ቆሮ 3÷17-18 ) (የቀ.ት)

በግብዣው ላይ የቆመው ዓምድ ከሚያንፀባርቀው ክብር የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ዕድፈት÷ የፊት መጨማደድና ነውር የሌለባት ክብርትና ጌጠኛ እንድትሆን ያደርጋታል:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በተጠራችበት የግብዣ ስፍራ ያለው ሌላው ትልቅ ሀብት ቀን በደመና ሌሊት በእሳት ዓምድ የሚመራ÷ በእሳት የሚናገር÷ በእሳት የሚያሻግር እንዲሁም ክብርዋ÷ ጌጥዋ÷ ጥንካሬዋ የሚሆናት አመፅንም ከመካከልዋ የሚያስወግድ እሳታማዊ ዓምድ ነው ::

## *ሐ) የወርቅና የብር ድንክ አልጋዎች*

> " .... ከወርቅና ከብር የተሠሩ ድንክ አልጋዎችም ነጭ÷ቀይ÷ቢጫና ሰማያዊ ቀለማትን በሚፈነጥቅ የዕብነ በረድ ወለል ላይ ተደርድረው ነበር::"(አስ1÷6)

ቤተ ክርስቲያን እንድታርፈበት የተዘጋጀላት የክብር አልጋ ከእንጨት ወይም ከገመድ የተሠራ አይደለም :: ቤተ ክርስቲያን ከወርቅና ከብር በተሠራ አልጋ እንድታርፍ ተጋብዛለች :: በጥንት ጊዜ በእስራኤል ድኾች

ከነልብሳቸው መሬት ላይ ይተኙ ነበር:: ሀብታሞች ደግሞ ከእንጨት÷ ከስሌን እንዲሁም ከተለያየ ቆዳ በተሠሩ አልጋዎች ይተኙ ነበር :: የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ከወጡ በኋላ ምድሪቱን በመውረር ላይ እያሉ ካስደነቃቸው ነገር አንዱ የብረት አልጋ ያለው ንጉሥ ማግኘታቸው ነበር :: (ዘዳ3÷11)

ነገር ግን ወደ ንጉሡ ግብዣ የተጠሩ ድኾችም ሀብታሞችም ነበሩ:: በዘመናቸው ሁሉ በወርቅ አልጋ ላይ ተኝተው አያውቁም ንጉሡ ወደ ግብዣው ሲጠራቸው ግን በወርቅና በብር አልጋ ላይ ሊያሳርፋቸው ነበር:: በተመሳሳይ መልኩ ለቤተ ክርስቲያን ዕረፍትን ሊሰጥ የተገለጠው ጌታ ጥሪውን በማቴዎስ ወንጌል እንዲህ እያለ ይገልፃል :-

> "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ:: (ማቴ 11÷28-29) (የቀ.ት)

ድንኩን የወርቅ አልጋ ለቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀላት ጌታ እራሱ ነው:: ነገር ግን በመኃ.መኃ1÷12 ላይ " ንጉሡ በድንኩ አልጋው ላይ ዐረፍ ብሎ ሳለ የሽቶዬ መዓዛ ቤቱን ሁሉ ሞላው " እዚህ ላይ የምንመለከተው ድንኩ አልጋ የንጉሡ ማረፊያም እንደሆነ ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳችን ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሴት (ሚስት) ክርስቶስን (ባል) አድርጎ ይመስለዋል :: ከዚህ የተነሣ ቤተ ክርስቲያን በድንኩ የወርቅ አልጋ ላይ ብቻዋን ልታርፍ ሳይሆን የተጠራችው ካሳረፋት ጌታ ጋር ጊዜ የምትወስድበት የእርሱን ማንነት የምትረዳበት ከእርሱ ጋር በመዋል እርሱን የምትመስልበት የክብር አልጋ ነው :: እዚህ ላይ ትልቅ የምንረዳው ነገር ቢኖር ንጉሡ በወርቅ ድንክ አልጋ ላይ ከእርስዋ ጋር ሲያርፍ ነው ከእርስዋ የሚወጣው መዓዛ ቤቱን የሚሞላው :: በሌላ አገላለጽ ቤተ ክርስቲያን ብቻዋን ያለ ንጉሡ የሽቶዋ መዓዛ ቤቱን አይሞላም ::

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሽቶአቸው መዓዛ የማይወጣው ከወርቁ አልጋ ርቀው በራሳቸው አልጋ ላይ ብቻቸውን ስላረፉ ነው :: ከንጉሡ ጋር ጊዜዋን የማታሳልፍ ቤተ ክርስቲያን የእርሱን እሳብ የማትረዳ÷ ራእይ የሌላት÷ የክርስቶስን መዓዛ የማትሸት÷ ከማረፍ ይልቅ የተኛችና ያንቀላፋች ድምፁንም የማትሰማ ነች:: ቤተ ክርስቲያን በወርቁ





አልጋ ላይ ስታንቀላፋ የምታስማው ድምፅ በቃኝ÷ ጠግቤአለሁ÷ ሀብታምም ሆኛለሁ÷የሚጎድለኝ ምንም የለም÷ ያለኝም ይበቃኛል የሚል ነው :: ነገር ግን ግብዣው የተዘጋጀላት በወርቁ አልጋ ላይ ከንጉሡ ጋር አርፋ ሰማያዊውን ራእይ እየተቀበለች ክርስቶስን በመምሰል የጌታን ክብር እንድታንፀባርቅና ሰማያዊውን ምስጢር እንድትገልጥ እንጂ ብቻዋን በአልጋው ላይ በመቀመጥ ምንም የሌላት ምስኪን እንድትሆን አልተጠራችም ::

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ያገኘችው ሌላው ሀብት ከንጉሡ ጋር በአንድነት የምታርፍበት የወርቁ አልጋ ባለቤት መሆን ነው ::

## *መ) የሚፈነጥቅ ቀለማት ያሉት መሠረት*

> "...ከወርቅና ከብር የተሠሩ ድንክ አልጋዎችም ነጭና ቀይ÷ ቢጫና ሰማያዊ ቀለማት በሚፈነጥቅ የዕብነ በረድ ወለል ላይ ተደርድረው ነበር::" ( እስ1÷6)

በዚህ ክፍል ላይ ቤተ ክርስቲያን በወርቁ አልጋ ላይ ያረፈችው ልዩ ልዩ ቀለማትን በሚፈነጥቅ ዕብነ በረድ ወለል ላይ ነበር ወይም አልጋዎቹን የተሸከመው ልዩ ልዩ ቀለማትን የሚፈነጥቅ የዕብነ በረድ መሠረት ነበር :: ይህንን ክፍል ከዮሐንስ ራእይ 1÷12-20 ጋር ስናስተያየው :-

1ኛ. መሠረቱ የወርቁን አልጋ እንደተሸከመ እንዲሁም በራእይ መጽሐፍ ላይ እንደተገለፀው የወርቁን መቅረዝ የተሸከመው ክርስቶስ ነው :: መሸከሙን የምናውቀው በቁጥር ሃያ ላይ "በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብት "ና" የሰባቱ የወርቅ መቅረዝ ምስጢር ይህ ነው::" "ና" የሚለው አያያዥ ቃል ሁለቱንም እንደያዛቸው ይገልፅልናል ::

2ኛ. አልጋውን የተሸከመው የዕብነ በረድ ወለል(መሠረቱ) የተለያየ ቀለማትን እንደሚፈነጥቅ ሁሉ እንዲሁም በራእይ 1÷14 ላይ ክርስቶስ በተሸከማቸው የወርቅ መቅረዞች ላይ ከራስ ፀጉሩ እስከ እግሩ ድረስ የተለያዩ ቀለማት ያሳቸው የሚያንፀባርቅ አምላካዊ ገፅታውን እናያለን:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሠረትዋ ክርስቶስ ነው::ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል ሲገልፀው "ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" (1ቆሮ 3÷11) እንግዲህ በዚህ

መሠረት ላይ ጌታም ባዘጋጀልን የወርቅ አልጋ ላይ እንደሚገባ ማረፍ አለብን ካረፍን ደግሞ:-

ሀ . የጌታን ማንነት እናውቃለን "ዕረፉ እኔም አምላክ እንደሆንሁ ዕወቁ" የሚለው ቃል ተፈፅሞ እናያለን :: (መዝ46÷10)(የቀ.ት)

ለ . ከሥጋና ከደም ሳይሆን እንደ ጴጥሮስ ከላይ ከሰማይ የሆነ ሰማያዊ መገለጥን የቤተ ክርስቲያን መሠረት ከሆነው ከክርስቶስ ከሚፈነጥቀው ነፀብራቅ እንሞላለን :: መገለጦች በመጡልን ቁጥር ደግሞ የገሃነም ደጆች አይቋቋሙንም :: ከዚህ የተነሣ አገልግሎታችንም እንደዛው ይሆናል :: በወርቅ አልጋ ላይ ካረፍን የወርቅ÷ በብር አልጋ ላይ ካረፍን የብር አገልግሎት ይኖረናል ::

> " ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ሆነ በብርም÷ በክቡረ ድንጋይም÷ በእንጨትም÷ በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል::"(1ቆሮ 3÷12)(የቀ.ት)

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን እንድታገለግል ብቻ ሳይሆን የተጠራችው በተመሠረተው መሠረት ላይ በወርቅ÷ በብር÷ በክቡረ ድንጋይ ወይም በሣርና በእንጨት መገንባትዋን ለይታ ማወቅ አለባት :: ምክንያቱም በመቅረዞቹ መካከል የሚመላለሰው ዐይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል በሆነው በጌታ ፊት የሁሉ ሥራ ይፈተናልና :: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደምታገለግል እራስዋን መጠየቅ ይኖርባታል ::

ስለዚህ የክቡረውን አገልግሎት ለማገልገል በወርቁ አልጋ ላይ የግድ ማረፍ ይኖርብናል ካላረፍን ግን የምናገለግለው አገልግሎት ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው የሳርና የአገዳ አገልግሎት ይሆናል:: ይህም የቤተ ክርስቲያን መሠረት ከሆነው ከጌታ በሚመጣ ህያው መገለጥ ሳይሆን በስመ አገልጋይ ብቻ የሆነ አገልግሎት ነው የሚሆነው:: ከዙፋኑ ያልመጣ ማንኛውም መልዕክት ኃይል የሌለው የማይገነባ ተረት ነው :: ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የተጠራችበት ክብር በወርቅና በብር አልጋ ላይ እንድታርፍና ከመሠረቱ በሚወጣው ነፀብራቅ ሕያው አገልግሎት እንድታገለግል ነው::





# የንጉሡ ልግስና

## ሀ ) የወርቅ ዋንጫ

> አንዱ ከሌላው ጋር በማይመሳሰል በልዩ ልዩ የወርቅ ዋንጫ መጠጥ ይታደል ነበር... " (አስ1÷7)

ሰዎች ለሚያዘጋጁት በየትኛውም ደረጃ ለሚደረግ ግብዣ ታዳሚው የሚስተናገድበት የአገልግሎት ዕቃ እንደ ጋባዡ አቅምና ፍላጎት አስቀድሞ ይዘጋጃል :: ስለዚህም በንጉሡ ግብዣ የተዘጋጀው የመጠጫ ዕቃ የወርቅ ዋንጫ ነበር :: ይህም የወርቅ ዋንጫ አንዱ ከአንዱ ጋር የማይመሳሰል ነበር:: ነገር ግን ሁሉም ወርቅ ነበር :: የተጠራው ሁሉ ድኻው÷ ሀብታሙ÷ የተማረው÷ ያልተማረው÷ ነጭና ጥቁሩም ሁሉም በወርቅ መጠጫ ይጠጣ ነበር :: ምክንያቱም "እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላምና " ዋንጫው የተለያየ ቅርጽ እንዳለው የተለያየ አገልግሎት ቢኖርም በንጉሡ ግብዣ ላይ የንጉሡ የበረከት ሙላት ወደ እኛ የሚተላለፈው በወርቅ ዋንጫ ብቻ ነው ::

እንደዚሁም ቤተ ክርስቲያን ከንጉሡ ወይን ጠጅ ልትጠጣ ብትጠራም መጠጣት ያለባት ንጉሡ ራሱ ባዘጋጃላት በወርቅ ዋንጫ ብቻ ነው :: አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ግን የንጉሡን የወርቅ ዋንጫ ጥለው በራሳቸው ጣሳ (አመለካከት÷ እውቀት÷ ጥበብና ማስተዋል ...ወዘተ) የንጉሡን በረከት ለመቀበል ይፈልጋሉ :: ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ሰማያዊ በረከት (የወይን ጠጅ) ለመጠጣት በራስ ማስተዋል ሳይደገፉ ንጉሡ የሚያስተላልፍበትን የእራሱን መንገድ ወርቁን መፈለግ አለብን::

## ለ) ገደብ የሌለው በረከት

> "... ንጉሡም የቤተ መንግሥቱ የወይን ጠጅ በልግሥና እንዲሰጥ አደረገ ለመጠጡም ብዛት ገደብ አልነበረውም ..."
> (አስ 1÷7-8)

እንግዲህ ሁሉም በግብዣው ላይ የወርቅ ዋንጫ ይዟል ፤ እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላም ፤ ለሁሉም መጠጫ ሰጥቶአል ፤ የወይን ጠጁም በልግሥና እንዲሰጥ ተፈቅዶአል ፤ ለመጠጡም ብዛት ገደብ አልነበረውም ፤ የእግዚአብሔር በረከት በሕይወታችን ቁጥር ስፍር የለውም ተሰፍሮም የሚሰጥ አይደለም ይህን በማስመልከት በመጽሐፍ ቅዱሳችን በተለያየ ቦታ እንዲህ ይላል:-

> " እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ኑ ገንዘብ የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም ኑ ያለ ገንዘብ ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ:: " (ኢሳ 55÷1)(የቀ.ት) "... ንጉሡም ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን ያህል መጠጣት ይችል ዘንድ ለቤተ መንግሥቱ አገልጋዮች ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር ::" (አስ 1÷8)

በግብዣው ላይ ግዴታ የለም ማንኛውም ሰው ለመጠጣት ፈቃደኛ ከሆነ መጠጣት ይችላል፤ ከጠገበም ማቆም ይችላል ነገር ግን ሰው እስከፈለገው ድረስ ነውና ገደብ የለውም :: እግዚአብሔር ከመዐዱ በግድ አያጎርስንም እጃችንን ሰንዘረን መብላትና መጠጣት የእኛ ድርሻ ነው :: " እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና":: (ዮሐ 3÷34)

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን የተጠራችበት የክብር ስፍራ አላት :: በዚህም የክብር ስፍራ እጅግ ውብና ውድ የሆነ የተሰወረ ሀብት እንዳለና ቤተ ክርስቲያን የዚህ ሀብት ወራሽ እንድትሆን የተጠራች እንደሆነች አንድ በአንድ ተመልክተናል :: እነዚህ አሳቦች ለሚቀጥለው ትምህርታችን በጣም ጠቃሚ ስለሆኑ የምዕራፍ ሁለት አሳቦችን እንደያዝን ወደሚቀጥለው እንሄዳለን::

# ም ዕ ራ ፍ   ሦ ስ ት

## ከክብር
## የጎደለችው
## ቤተ ክርስቲያን

# ይህ በዚህ እንዳለ

ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ አገላለጽ የክርስቶስ ሚስት ተብላ እንደምትጠራ መጽሐፍ ቅዱሳችን ይነግረናል:: እንዲሁም ንጉሥ አርጤክስስና ንግሥት አስጢንም የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናቸው :: ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሚስት ተብላ ልትጠራ የምትችለው ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ባዘጋጀላት የመስቀሉ ሥራ ካለፈች በኋላ ነው:: እንዲሁም ንግሥት አስጢን የንጉሥ ሚስት ስለሆነች ንጉሡ ባዘጋጀው የግብዣ ቦታ ያለፈች ነበረች:: ማለትም በመጋረጃው÷ በዓምዱ÷ በድንክ አልጋው÷ በሚፈነጥቅ የዕብነ በረድ መሠረት÷ በንጉሡ የወርቅ ዋንጫ÷ በልግሥናውና ገደብ በሌለው በረከት ውስጥ ያለፈች ነበረች :: ከዚህ የተነሣ ንግሥት አስጢን እጅግ ውብ ነበረች:: ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ሥራ ላይ በበዓለ ኀምሳ ቀን በምድር ላይ በመንፈስ ቅዱስ ከተመሠረተች በኋላ በሚያስደንቅና ታላቅ በሆነ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያዳናትን ጌታ ክብሩን በመግለጥና በማሳየት የተሰጣትን የወንጌል አደራ በሚገባ ተወጥታለች :: ከዚያም ቤተ ክርስቲያን ቀስ በቀስ ዓለማዊ ምኞትንና አሠራርን ወደ ውስጥዋ በማስገባት በተለይ በ1000 ዓ.ም ገደማ ፍፁም ከወንጌል እውነት ወጥታ በጨለማ ትመላለስ እንደነበር ከታሪክ መረዳት ይቻላል ::

እንዲሁም እጅግ ውብ የነበረችው ንግሥት አስጢን እንዴት ንጉሡ ካዘጋጀላት የክብር ግብዣ እንደተንሸራተተችና ከወንጌል እውነት እርቃ ከክብር የጎደለች እንደሆነች፤ የዚህም አስደናቂ የሆነውን ምስጢር የያዘውን የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ካዘጋጀላት ክብር ወይም ሙላት እንደጎደለች በማነፃፀር እንመለከታለን ::

> "<u>ይህ በዚህ እንዳለ</u> ንግሥት አስጢን ደግሞ በበኵልዋ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ለሴት ወይዛዝርት ግብዣ አድርጋ ነበር :: ግብዣው በተጀመረ በሰባተኛው ቀን ንጉሡ አርጤክስስ በወይን ጠጅ ረክቶ ደስ ባለው ጊዜ ...."(አስ1÷9-10)





ከላይ ባለው ጥቅስ መጀመሪያ ላይ <u>"ይህ በዚህ እንዳለ"</u> የሚለው ቃል ከቁጥር ዘጠኝ በላይና ከቁጥር ዘጠኝ በታች ያለውን አሳብ ያገናኘ ነው::

<u>"ይህ በዚህ እንዳለ"</u> ሲል ቤተ ክርስቲያን የተጠራችበት ክብር÷ መጋረጃው÷ የደመናውና የእሳት ዓምዱ÷ የወርቅና የብሩ አልጋ÷ የወርቁም ዋንጫና የንጉሡ ልግስና እንዳለ ማለቱ ነው :: ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ሰባዎቹ ደቀመዛሙርት ለአገልግሎት ልኮ ተመልሰውም በእነርሱ መካከል ምን እንደተሠራ ነገሩት :: ይህን በሰማ ጊዜ ሥልጣን እንደተቀበሉ ስማቸው በሰማያት እንደተፃፈ አይቶ "በዚህ ሰዓት በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት አደረገና... " የሚል ቃል እናገኛለን :: (ሉቃ10÷21) በተመሳሳይ ሁኔታ <u>ይህ በዚህ እንዳለ</u> ግብዣው በተጀመረ በሰባተኛው ቀን ንጉሥ አርጤክስስ የቤተ ክርስቲያን ክብርና የተደረገላትን ልግሥና በመመልከት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በሆነው በወይን ጠጅ ሐሤት ባደረገ ጊዜ ንግሥት አስጢን ልብሰ መንግሥትዋን ለብሳ ዘውዷን ጭና ባጠገቡ እንድትቀመጥ ፈለገ ::

ንጉሡ ይህን ያደረገው ንግሥት አስጢን እጅግ የተዋበች ስለነበረች ለባለ ሥልጣኖችና ለእንግዶች እንድትታይ ፈልጎ ነበር :: እርስዋ ግን ወደ ንጉሡ <u>ለመቅረብ እምቢ አለች</u>:: እምቢ ያለችበት ምክንያት ለብቻዋ መክበር ስለፈለገች ነበር ::

# ለብቻዋ ለመክበር ፈለገች

> " ይህ በዚህ እንዳለ ንግሥት አስጢን ደግሞ <u>በበኵልዋ</u> በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ለሴት ወይዛዝርት ግብዣ አድርጋ ነበር::"
> (አስ 1÷9)

በዚህ ጥቅስ ላይ <u>"በበኵልዋ"</u> የሚል ቃል እናገኛለን :: ይህ ማለት የንጉሡ የክብር ግብዣ እያለ ንግሥት አስጢን ደግሞ <u>በበኵልዋ</u> በራስዋ ፈቃድ ለብቻዋ ንጉሥ አርጤክስስ በሌለበት ስፍራ እራስዋን ለማክበር በበኵልዋ ግብዣን አዘጋጀች :: የንጉሡንም ግብዣ ናቀች ባሏ ክብርዋ እንደሆነ ዘነጋች፤ በንጉሡ ክብር ሳይሆን በራስዋ ኃይልና ብርታት መመካት ጀመረች፤ ሰው ያደረጋትን የንጉሡን ምህረትና ቸርነት ረሳች፤

በንጉሡ የወርቅ ዋንጫ ሳይሆን በራስዋ ጣሳ (ማስተዋል፥ ጥበብና እውቀት) ግብዣን አዘጋጀች፤ እንደ ሎዶቅያም "ሀብታም ነኝ ባለጠጋም ሆኛለሁ አንድስ እንኳን አያስፈልገኝም ያለኝ ይበቃኛል"የምትል ሆነች:: ነገር ግን ያለ ክርስቶስ ክብር ስለሌለ ደኻ፥ የተራቆተች፥ምስኪን፥ዕውር፥ ጎስቋላ መሆንዋን የረሳች ነበረች::

በመጽሐፍ ቅዱስ የተገፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፈዋልና ዛሬም ቢሆን እንደ ንግሥት አስጢን በአምላካቸው ተደግፈው ሳይሆን በራሳቸውና ባላቸው ነገር በመመካት ከንጉሡ ክብር እየተንሸራተቱ ያሉ ሎዶቅያዊ ሕይወት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ናቸው ::

ንግሥት አስጢን <u>"በበኰልዋ"</u> ግብዣን ያዘጋጀችው ለሴት ወይዛዝርት ነበር:: ለሴት ወይዛዝርት ግብዣን ያደረገችበት ምክንያት በሴት ወይዛዝርት ዘንድ ሙገሳን፥ ክብርና ዝናን ፈልጋ ነበር :: የንጉሡን ዕቅድ ከማድረግና ከመከበር ይልቅ የወይዛዝርትን ሙገሳ የምትፈልግ የአስጢን ዓይነት አመለካከት ወይም ፍልስፍና ያላት ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ከመስመር የወጣች አንድም የምታውቀው የሴላት ፍፃሜዋም እጅግ አሳዛኝ ነው ::

ሌላው <u>"በበኰልዋ"</u> ግብዣን ያደረገችው የንጉሡን ክብር ሳይሆን የራስዋን ክብር፥ አመለካከትና ሥርዓት በሴት ወይዛዝርት መካከል ለማንፀባረቅ ፈልጋ ነበረ የንጉሡን የክብር ጥሪ እምቢ ያለችው :: ልክ እንደ ንግሥት አስጢን በተመሳሳይ ሁኔታ በመካከለኛው ዘመን ከወንጌል እውነት ወጥታ ከክብር የጎደለችው ቤተ ክርስቲያን ንጉሡን ፊት ለፊት እያየች በእውነትና በመንፈስ ማምለክንና ማገልገልን ትታ በወግና በሃይማኖት ቀንበር ብቻ የምትመላለስ ቤተ ክርስቲያን ሆነች:: ከንጉሡ በምታገኘው ፀጋ ሳይሆን በዚህ ዓለም ጥበብና ማስተዋል ማገልገልን ፈለገች ::

በዘመናችን አገላለጽ ብንገልፀው ከወግና ከሥርዓት ዩኒቨርስቲ ተመርቃ የወጣች፤ ከአሥር ደቂቃ በላይ መስበክ የማትችል፤ የስብከት አቋቋምና የማይከራፎን አያያዝ ሥርአት ያላት፤ ለሰዎች ጆሮ እንዲስማማ የስብከቱ 3/4 ተረትና ቀልድ መሆን እንዳለበት የምታምን፤ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን እንዳይቀሩ ጠንክር ያለ ትምህርት መስጠት የማትችል ...ወዘተ ከንጉሡ ርቃ <u>"በበኰልዋ"</u> ግብዣን ባዘጋጀችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ቦታ ያዘ :: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ያልተለማመደችውን ዓለማዊ ምኞትና ጥበብ





ንግሥት አስጢን ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስገባች ከዚህ የተነሣ ስም ብቻ ያላት ነገር ግን የሞተች ሆነች :: (ራእ 3፥1)

# ዘውዷን ለመጫን እምቢ አለች

የንግሥት አስጢን ጥሪና እምቢታ ከዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ጥሪና እምቢታ ጋር ተመሳሳይ ነው :: የንጉሡ ፍላጎት ቤተ ክርስቲያን በተዘጋጀላት ክብር ውስጥ ብቻ እንድትሆን ሳይሆን ከዚህ በበለጠ ክብርና ውበት ደምቃ ከጎኑ እንድትቀመጥ ከፍ ከፍም ብላ እንድትታይ ንግሥተ አልባሳትዋንና ዘውዷን ጭና በጣም አሸብርቃና ደምቃ ወደ ሙላቱ እንድትደርስ ፈልጎ ነበር:: ይህንንም ያደረገበት ምክንያት በጣም ውብ ስለነበረች ነው::

> " ...ንጉሡ ይህንን ያደረገበት ምክንያት ንግሥት
> አስጢን እጅግ የተዋበች ስለነበረች ባለሟሎች ለሆኑት ባለ
> ሥልጣኖችና ለአንግዶቹ ሁሉ እንድትታይ ፈልጎ ነበር:: "
> (አስ1፥11)

ንግሥት አስጢን ገና የእምቢታ ድምፅ ከማሰማትዋ በፊት በንጉሡ ዘንድ እጅግ የተዋበች ነበረች:: ነገር ግን ውበትዋ ከራስዋ የመነጨ ሳይሆን በንጉሡ ግብዣ ላይ ካለው ዓምድ እንዲሁም የተለያዩ ቀለማት ካለው ከመሠረቱም ከሚፈነጥቅ ውበት የተነሣ <u>እጅግ የተዋበች</u> ነበረች::

የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን በመካከለኛው ዘመን ከእውነት መንገድ ከመውጣትዋ በፊት እጅግ የተዋበች ነበረች ለዚህ እውነት ከመጽሐፍ ቅዱሳችን የሐዋርያት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ማየት ይቻላል:: ቤተ ክርስቲያን እጅግ የተዋበች ነበረች ስንል ምን ማለታችን ነው? መልሱ ክርስቶስን በሙላት የምታሳይና በስማያዊው ፀጋ የተሞላች፤ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የደመቀች፤ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን በሰጠው የአገልግሎት ስጦታዎች ማለትም በሐዋርያትና በነቢያት፥ በወንጌል ሰባኪዎች፥ በእረኛና በአስተማሪዎች ያሸበረቀች ከዚህ ስጦታ የተነሣ የክርስቶስን ክብር ሙሉ በሙሉ የምታንፀባርቅ፥ የምትገልጥና የምታሳይ እጅግ የተዋበች ነበረች ማለታችን ነው ::

ስለዚህ ንግሥት አስጢን የእምቢታ ድምፅ ከማሰማትዋ በፊት በብዙ ክብር ያሸበረቀች እጅግ የተዋበች አብያተ ክርስቲያናት ነበረች:: ነገር ግን የንጉሡ ፍላጎት በዚህ ብቻ የሚያበቃ አልነበረም ንግሥት አስጢን ዘውዷን ደፍታ ከፍ ከፍ ብላ እንድትታይና እንዲሁም ከጎኑ በማስቀመጥ የማጠቃለያ ሥራን መሥራት ፈልጎ ነበር :: ሆኖም ንግሥት አስጢን ውበትዋን ከየትና ከማን እንዳገኘችው በመዘንጋት የውበትዋ ምንጭ በሆነው በባልዋ ላይ እጅግ በመኩራራት ባቀረበላት የዘውድ መጫን ጥያቄ መሠረት <u>ዘውዷን ለመጫን እምቢ አለች</u> ::

ንግሥት አስጢን ዘውዷን ጭና ልብሰ ንግሥትነትዋን ለብሳ አምራና ደምቃ ከፍ ከፍም ብላ የንግሥናዋና የዘውዷ ውበት በአለቆችና በባለሥልጣናት ፊት እንዲታይ ንጉሡ ፈልጎ ነበር :: እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ መቀመጥ ውበትዋ ተገልጦ እንድትታይ ነው:: ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ "…. ወሰን የሌለውን የክርስቶስን ባለፀግነት ለአረማዊያን እንዳበስር ይህ ፀጋ ተሰጠኝ እንዲሁም ባለፉት ዘመናት የሁሉ ነገር ፈጣሪ በሆነው በእግዚአብሔር ተሰውሮ ስለነበረው ምስጢር÷ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን መሆኑን ለሁሉ እንድገልጥ ጸጋ ተሰጠኝ::"(ኤፌ3÷8-9) ሐዋርያው ጳውሎስ እንደገለፀው ጸጋ የተቀበለው የተሰወረውን ምስጢር (ህብት) ወይም ቤተክርስቲያን የተጠራችበትን ክብርና ታላቅነት ለሁሉ በመግለጥ እንዲያሳይ ነው:: በተመሳሳይ መልኩ ንግሥት አስጢን የተዋበችና ፀጋን የተቀበለችው በከበረውና በተሰወረው ህብት ውስጥ ያለችው ያንን እርስዋ ያለችበትን ክብር ለሌሎች እንድታሳይ ወይም እንድትገልጥ ነበር :: ሐዋርያው ጳውሎስ በቁጥር አሥር ላይ በተጨማሪ "ይህም የሆነው በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት በሰማይ ያሉት አለቆችና ባለሥልጣኖች የእግዚአብሔርን ጥበብ በየመልኩ እንዲያውቁ ነው" ይላል :: (ኤፌ3÷10)

በተመሳሳይ መልኩ ቤተ ክርስቲያን ጥሪዋ በልዩ ልዩ ውበትዋ በየመልኩ ለአለቅነትና ለሥልጣናት በሰማያዊም ስፍራ ላሉ የክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊቶች በታላቅ ኃይልዋ ትገለጽና ትታወቅ ዘንድ ከፍ ከፍ ብላም ትታይ ዘንድ ነው::

እንዲሁም የንጉሡ ግርማ የንጉሡ ውበት የንጉሡ ታላቅነት በልዩ ልዩ መልኩ በንግሥት አስጢን አማካይነት ይገለጽ ዘንድ ዘውድዋን ጭና ንግሥት አልባሳትዋን ለብሳ በከፍታ ሥፍራ እንድትቀመጥ እንደ ንግሥትም ለአለቆችና ለባለሥልጣኖች እንድድትታይ ንጉሡ ጥሪ





ቢያቀርብላትም እርስዋ ግን ንጉሡን ለመታዘዝ÷ ለማሳየትና ለማስከበር እምቢ አለች :: እምቢ በማለትዋ የንጉሡ ቁጣ ነደደ ::

ባለንበትም ዘመን ክርስቶስ ሊያከብራቸውና ሊያደምቃቸው እየፈለገ ልክ እንደ ንግሥት አስጢን እምቢ የሚሉ አብያተ ክርስቲያናት ጥቂት አይደሉም::

# የንጉሡ ቁጣ መንደድ

" …ይህም ሁኔታ ንጉሡን እጅግ አስቆጣው " (አስ 1÷12)

ንግሥት አስጢን ለንጉሡ የዘውድ መጫን ጥያቄ እምቢ የሚለውን ቃል ስትመልስ ብዙ ያበላሸቻቸው ነገሮች ቢኖሩም በተለየ መንገድ የንጉሡ ቁጣ በእርስዋ ላይ እንዲነድ ካደረጉት ነገሮች ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን::

## ሀ) ክብርዋ የሆነውን ዓምድ ገፋች

ንግሥት አስጢን የንጉሡ ሚስት ስለነበረች ቀደም ብለን እንዳየነው ከመጋረጃው ጀምሮ እስከ ወርቅ ዋንጫ ባለበት በቤተ መንግሥቱ በንጉሡ ግብዣ ላይ የምትኖር ነበረች:: ከነዚህም ውስጥ ዓምዱና የተለያዩ ቀለማትን የሚፈነጥቅ መሠረት ባለበት ስፍራም ነበር የምትኖረው:: ከዓምዱ በሚወጣው ብርሃን ንግሥትአስጢን ያጌጠች÷ የተዋበችና ክብር ያላት ነበረች:: ነገር ግን ንግሥት አስጢን የውበትዋን ምንጭ ዘንግታ ለንጉሡ ጥሪ እምቢ ስትል በንጉሡ አማካይነት የተገኘውን እጅግ ያስዋባትን÷ ዓላማውንም ሊገልፅባት ያሰበውን፤ የሚመራትን ዓምድ፤ ከፊት ለፊትዋ የቆመውን ከእርሱም ክብር ተካፋይ የሆነችበትን ዓምድ አልፈልግም እምቢ ማለትዋ ነበር ::

እስራኤላውያን ከግብጽ ከባርነት ቤት በድንቅና በተአምራት እየመራ ያወጣቸውን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊያስገባቸው በምድረ በዳ የመራቸውን ይህንን የእሳት ዓምድ ቁጭ ብለው አሙት :: እርሱንም ለመከተል እምቢ አሉ፤ ያለ እርሱም በምድረ በዳ ወድቆ መቅረት እንዳለ ዘነጉ፤ ዓምዱ ባለበት ቦታ መኖራቸውን ዘንግተው በዓምዱ ፊት እራሳቸውን አረከሱ :: የበረከት

ሙላት ወደ አለበት ወደ ንጉሡ ዙፋን መውጣት ሳይሆን ወደ ግብፅ መውረድን ተመኙ ከዚህ የተነሣ የእግዚአብሔርን መንፈስ (ዓምዱን) አስመረሩት:: እርሱም መልሶ ተዋጋቸው ጠላትም ሆነባቸው:: (ኢሳ 63÷10) (የቀ.ት) የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ የሆኑት ንግሥት አስጢንና እስራኤላውያን ዓምዱ ባለበት ስፍራ ይኖሩ እንደነበር ሁሉ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ዓምዱ ባለበት ስፍራ ከዓምዱ ጋር አብራ የምትኖር ናት :: ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ ለጢሞቴዎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ከገለፀለት በኋላ የትና ከማን ጋር እንደሚኖር በደንብ እንዲያውቅ እንዲህ በማለት ገልጾለታል :-

> " ብዘገይ ግን በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ <u>ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት</u> የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው:: " (1ጢሞ 3÷15)(የቀ.ት)

ጢሞቴዎስ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ የሚኖር ነበር :: ምክንያቱም እንዲህ ብሎታልና "በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት እንዴት መኖር እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ...."እግዚአብሔር በሚያድርበት ቤት ውስጥ ጢሞቴዎስ አብሮ ያድር ነበር :: ቤቱም እግዚአብሔር የሚያድርበት <u>የእውነት ዓምድና መሠረት</u> ያለበት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው::

አንዳንድ ክርስቲያን አገልጋዮችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር አብረው የሚያድሩ አይመስላቸውም:: ከዚህ የተነሣ እንዴት መኖር እንዳለባቸውና እንዴት ቤተ ክርስቲያንን መምራት እንዳለባቸው ዘንግተዋል:: የእውነት ዓምድና መሠረት ባለበት በእግዚአብሔር ቤት መኖራቸውን የረሱ ብዙዎች ናቸው :: ከመርሳታቸው የተነሣ እንደ ንግሥት አስጢን ዓምዱ ባለበት ስፍራ በራሳቸው አሳብና ምኞት የሚመላለሱ ምእመናን ያለ ቅድስና እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ አገልጋዮችና ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ናቸው ::

" የነብርን ጅራት አለመያዝ ከያዙም አለመልቀቅ " የሚባል አባባል አለ :: የነብርን ጅራት አንዴ ከያዝን በኋላ ብንለቀው ውጤቱ ለማናችንም ግልፅ ነው :: እንዲሁም የሰዎችና የእግዚአብሔር ማደሪያ በሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዓምዱም ባለበት ቦታ አለመቀመጥ ከተቀመጡም ደግሞ





ዓምዱን እንደሚገባ መከተል አለበለዚያ ዓምዱ መልሶ ጠላት እንደሚሆንብን ማወቅ አለብን ::

እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን በሕያው እግዚአብሔር ቤት ውስጥ ነው ያለነው ካልን ቤቱም ቤተ ክርስቲያን እንጂ መቀለጃ÷ ማላገጫ÷ የወንበዴዎች ዋሻ÷ የግልን ጥቅም ለማግኘት የራሳችንን መዋቅር የምንዘረጋበት አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን የእውነት ዓምድና መሠረት ያለበት የሕያው የእግዚአብሔር ቤት ነው :: በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንደፈለግን እየቀለድን ያለን ብንኖር ዓምዱ እየታገሰን እንጂ እግዚአብሔር በቤቱ በሕያውነቱ ሳይኖር ቀርቶ ስላይደለ መጠንቀቅ አለብን ::

ስለዚህ ያለንበት ዘመን ከመቼውም ይልቅ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ቤተ ክርስቲያንን በልዩ ክብር ሊያከብራት÷ ሊያነግሣት÷ ከፍ ከፍም አርጎ ሊያሳያት የተነሣበት ዘመን ነው :: ለዚህም ጥሪ ድምፁን በተለያየ መልኩ እያሰማ ያለበት ዘመን ነው :: ነገር ግን ለዚህ ድምፅ (ጥሪ) እምቢ የምንል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች÷ አገልጋዮችና ምእመናን ካለን እንደ ንግሥት አስጢንና እንደ እስራኤላውያን የቤተ ክርስቲያን ክብርዋ÷ ጌጥዋና ውበትዋ የሆነውን ዓምድ አልፈልግም አልታዘዝም እምቢ በማለት እየገፋነው ነው :: ከገፋነው ደግሞ የሚጠብቀን ዕድል እግዚአብሔር ከእኛና ከአገልግሎታችን ዞር ማለት ብቻ ነው :: " ይሰጠንም ዘንድ ሕይወት ያላቸው ቃላት ተቀበለ ለእርሱም አባቶቻችን ሊታዘዙለት አልወደዱም ነገር ግን <u>ገፉት</u> በልባቸው ወደ ግብጽ ተመለሱ ....<u>እግዚአብሔር ግን ዘወር አለ</u> " (ሐ.ሥ 7÷38-42)(የቀ.ት)

## ለ) ሕያው የሆነውን አገልግሎት ገፋች

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ አይደለም:: ከክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ የሚመነጭ ነገር ግን ሥጋን በለበሰ ሰው ለሌሎች የሚተላለፍ ነው:: እንዲሁም ንግሥት አስጢን የአገልግሎትዋ ምንጭ ከየት እንደሆነ በመዘንጋት እምቢ ስትል በወርቁ አልጋ ላይ ሆርፋ የምታገኘውን ከመሠረቱ (ከክርስቶስ) የሚፈነጥቀውን ሕያው የሆነውን አገልግሎት ነበር የገፋችው :: ስለዚህ አስቀድመን እንዳየነው ከንጉሡ

ሳይሆን ከሥጋና ከደም የመነጨ አገልግሎት በሴት ወይዛዝርት መሀከል ጀመረች::

የእግዚአብሔር ቃል ከጌታ የተቀበልነውን አገልግሎት እንደ ምናምንቴ በመቁጠር ብናገለግል ተጠያቂ እንደምንሆን በብዙ ቦታ ይነግረናል :: ንግሥት አስጢን የአገልግሎት አደራዋንና ያስዋባትን የአገልግሎት ስጦታዎች ገፋች፤ የተሰጣትን የወንጌል አደራ መፈጸም አልቻለችም፤ የንጉሡን ጥሪ በመናቅ እምቢ አለች ::

በዘመናችን ብዙ አገልጋዮች የአገልግሎት ስጦታና የመንፈስ ቅዱስን የጸጋ ስጦታ ይቀበላሉ :: ነገር ግን መገንዘብ ያለብን ዋናው ነገር መቀበሉ ላይ ሳይሆን አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ መፈፀም ላይ ነው :: ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልሞናና በቆላስያስ መልእክቱ ላይ ለአክሪጳ ስለ አገልግሎቱ አፈጻጸም ግልጽ በሆነ መንገድ ገልጾለት ነበር::

"... ከእኛ ጋር አብሮ ወታደር ለሆነው አክሪጳ... "
(ፊልሞ÷2)(የቀ.ት)

አክሪጳ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር የሚያገለግል አገልጋይ ብቻ ሳይሆን የክርስቶስም መልካም ወታደር ተብሏል:: ወታደር ከተባለ ደግሞ የወንጌል አደራ ለመፈፀም ስለ ክርስቶስ ሲል የሚደርስበትን መከራ መቀበል የሚችል የጦር አዛዡን ደስ የሚያሰኝ ዓለማዊ በሆነ ነገር ራሱን የማያጠላልፍ ነው:: (2ጢሞ2÷3-4) ስለዚህ አክሪጳ የክርስቶስ መልካም ወታደርና አገልጋይ ነበር:: ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስያስ በጻፈው መልእክቱ ላይ ለአክሪጳ እንዲህ ብሎታል:-

"ለአክሪጳ ከጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት
እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ በሉልኝ ::" (ቆላ 4÷17)

እዚህ ላይ ሦስት ነገሮችን እናያለን ምንም እንኳን ሐዋርያው ጳውሎስ አክሪጳን የጌታ በጎ ወታደር መሆኑን በፊልሞና መልእክቱ ቢመሰክርም በቆላስያስ መልእክቱ ግን ቸል እንዳይል :-

1ኛ. አገልግሎቱ ከሰው ወይም ከእራሱ አመለካከት፤ ከሥጋና ከደም የመነጨ እንዳይደለ <u>"ከጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት"</u> በማለት አገልግሎቱን ከጌታ እንደተቀበለ ያሳስበዋል::





2ኛ. አገልግሎቱ ሕያው እንደሆነና ከምድር አልፎ እስከ ፍርድ ቀን ከዚያም አልፎ እስከ ላይኛው ቤታችን ድረስ የሚሄድ ሽልማት ያለው ዘላለማዊ ነገር እንደሆነ መጀመር ብቻ ሳይሆን መጨረስ (መፈፀም) ያለበት ሕያው አገልግሎት ስለሆነ <u>"እንድትፈፅመው"</u> ይለዋል::

3ኛ. አገልግሎት የዋዛ እንዳልሆነ ከጌታ የተቀበለውንና ወታደር ተብሎ እንዲጠራ ያደረገውን አገልግሎት አልፈልግም ቢለው እንደ ንግሥት አስጢን ቢገፋው ቅጣት እንዳለው በማስጠንቀቂያ ቃል <u>"ተጠንቀቅ በሉልኝ"</u> ይለዋል::

ንግሥት አስጢን ግን ሕያው የሆነውን አገልግሎት ለመፈፀም አልቻለችም አልፈልግም እምቢም አለች:: እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን አገልግሎቱን አልፈልግም ስትል ለአገልግሎቱ ብቁ ያደረጋትን ከመሠረቱ ማለትም ከክርስቶስ ለሚፈነጥቀው ለሰማያዊ ምስጢር÷ ለሰማያዊ ተልዕኮ÷ ለሰማያዊ ትዕዛዝ እምቢ አልታዘዝም ማለትዋ ነበር:: ሐዋርያው ጳውሎስ በንጉሥ አግሪጳ ፊት ቀርቦ ጌታ እንዴት እንደተገናኘውና ስለተሰጠውም አገልግሎት እንዲሁም ጌታ በእርሱ ሕይወት ምን እየሠራ እንዳለ ከገለፀ በኋላ "...ንጉሥ አግሪጳ ሆይ ስለዚህ <u>ከሰማይ የታየኝን ራእይ እምቢ አላልኩም</u>" (ሐ.ሥ 26÷19)(የቀ.ት) ጳውሎስ ከሰማይ ለተገለፀለት ምስጢር÷ ሰማያዊ ተልዕኮ÷ ትእዛዝ <u>እምቢ</u> ሊል አልፈለገም:: ምክንያቱም አልታዘዝም ቢል የሚጠብቀውን ነገር ጌታ እንዲህ በማለት አስቀድሞ ነግሮታል "...የመውጊያውን ብረት <u>ብትቃወም</u> ለአንተ ይብስብሃል...":(ሐ.ሥ26÷14) (በቀ.ት) እዚህ ላይ <u>"ብትቃወም"</u> የሚለው ቃል <u>እምቢ</u> ብትል ማለቱ ነው:: ስለዚህ ከአገልግሎት አደራ ጋር ሁል ጊዜ ማስጠንቀቂያም አለ :: ንግሥት አስጢን ይህንን የማስጠንቀቂያ ቃል የረሳች ነበረች:: ንግሥት አስጢን ከዓምዱ÷ ከመሠረቱና ከወርቁ አልጋ ጋር እንዲሁም ከሰማይ ለተገለጠላት ሰማያዊ ምስጢር አልስማማም÷ አልታዘዝም እምቢ በማለትዋ የተነሣ የንጉሡ ቁጣ በእርስዋ ላይ ነደደ:: ዓምዱም ተመልሶ ጠላት ሆነባት የመውጊያውንም ብረት ስትቃወም መልሶ ወጋት የንጉሡም የመጨረሻ የውሳኔ ድምፅ በንግሥት አስጢን ላይ ወጣ ይህም የአስጢን የንግሥነት ማዕረግ ከእርስዋ ለተሻለ ለሌላ ሴት እንዲሰጥ ተወሰነ::

# የአስጢን የንግሥነት ማዕረግ ከእርስዋ ለተሻለ ለሌላ ሴት እንዲሰጥ ተወሰነ

" ንጉሥ ሆይ! እንግዲህ መልካም ፈቃድህ ቢሆን ንግሥት አስጢን ከእንግዲህ ወዲህ ወደ አንተ ፊት መቅረብ ከቶ እንዳይፈቀድላት የሚገልጥ ውሳኔህን በዐዋጅ አስተላልፍ ይህም ውሳኔ ከቶ የማይለወጥ ሆኖ ለዘላለም ይጸና ዘንድ በፋሪስና በሜዶን ሕግ ውስጥ እንዲመዘገብ ትእዛዝ አስተላልፍ <u>የአስጢንንም የንግሥነት ማዕረግ ከእርስዋ ለተሻለች ለሌላ ሴት ስጥ</u>::" (አስቴ 1÷19)

ስለዚህ ንግሥት አስጢን የእውነት ዓምድና መሠረት ባለበት የእግዚአብሔር ማደሪያ በሆነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሆንዋን በመዘንጋት÷ በራስዋ አመለካከት በሴት ወይዛዝርት ለመክበርና ለመሞገስ በመፈለግ ለንጉሡ የዘውድ መጫን ጥያቄ እምቢ÷ አልፈልግም÷ አልታዘዝም በማለትዋ ልክ የመካከለኛዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከወንጌል እውነት ፍፁም ወጥታ ከክርስቶስ ተለይታ የሞተች እንደነበረች ንግሥት አስጢንም እምቢ በማለትዋ የንግሥነት ክብርዋ ተገፈፈ:: ከንጉሡ የተለየች ሙት ሆነች:: ንግሥት አስጢን ዘውዷን ለመጫን እምቢ ስትል ንጉሡ የእርሱን ክብር የምታንፀባርቅ ሌላ ሴት ስለሚያስፈልገው የአስጢንን የንግሥነት ማዕረግ ከእርስዋ <u>"ለተሻለ"</u> ለሌላ ሴት እንዲሰጥ ተወሰነ ::

<u>"የተሻለ"</u> የሚለው ቃል በጣም አስፈላጊ ነው:: <u>የተሻለ</u> ማለት ለምሳሌ ከመገናኛዎች ውስጥ ስልክን ብንወስድ ከዚህ ቀደም ከነበረው የስልክ መገናኛ አሁን ያለው የስልክ መገናኛ እጅግ <u>የተሻለ</u> ነው:: ከዚህ ቀደም የነበረው የስልክ መገናኛ ማገናኘት ያገናኛል ድምፅንም ያስተላልፍ ነበር:: ነገር ግን እንደ አሁኑ ዘመን የተሻለ አልነበረም:: አሁን ያሉት የስልክ መገናኛዎች በፊት ከነበሩት የስልክ መገናኛዎች የተሻሉና ላቅ ያሉ ናቸው:: በመጀመሪያ ከነበሩ የስልክ መገናኛዎች አንዱ በማዞሪያ የሚደወልባቸው ነበሩ:: ከዚያ የተሻሉ በመምጣታቸው አሁን በየትኛውም ስፍራ ይዘናቸው መጓዝ የምንችል ተንቀሳቃሽ የስልክ መገናኛዎች ተሠርተዋል:: ከዚህም አልፎ አሁን ዓለማችን የኢንተር ኔት የስልክ መገናኛዎች ላይ ደርሳለች:: የኢንተር ኔት የስልክ መገናኛዎች ከመጀመሪያው ስልክ ጋር ስናወዳድራቸው ልዩነታቸው ቃል እስከምናጣለት ድረስ በዓይነትም÷ በክብርም÷ በሞገስም በሁሉም ነገር የተሻሉ ናቸው::





የእግዚአብሔር ቃል ስለመጀመሪያውና ስለመጨረሻዋ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ክብር ሲነግረን " ከፊተኛው ቤት ክብር ይልቅ የኋለኛው ቤት ክብር እጅግ ይበልጣል (የተሻለ) ነው" (ሐጌ 2÷9) ስለዚህ ከንግሥት አስጢን እጅግ <u>የተሻለች</u> ሌላ ሴት አለች ንግሥት አስጢን ክብርዋን የጣለችው ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነች:: ነገር ግን በክብርም÷ በሞገስም÷ በዓይነትም ከንግሥት አስጢን <u>የተሻለች</u> የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን አለች:: አንዳንድ ሰዎች ያሉበት የኢንተር ኔት የመገናኛ ዘመን እንደሆነ አያውቁም ምኞታቸውና ራእያቸው ዛሬም በማዞሪያ ስልክ መጠቀም ነው:: የበፊተኛው ቤት ክብር ስንል የብሉይ ኪዳን የፊደልና የሕግ አገልግሎት ማለታችን አይደለም የምገልፀው ስለ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ነው:: የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ የተመሠረተችና በታላቅ ክብር የተመላለሰች ነበረች:: ከዚያም በመካከለኛው ዘመን ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት ሆኖ ቤተ ክርስቲያን በባህልና በሃይማኖት ቀንበር ተይዛ ከክብር የጎደለችውን የመካከለኛዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን አጠቃሎ ማለት ነው:: ነገር ግን ከአሁን በኃላ የምናያት የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ክብርዋ÷ ሞገስዋ÷ ቅባትዋ፣ አገልግሎትዋ እንደ ኢንተር ኔት ቴክኖሎጂ እጅግ የተሻለ ነው:: በመሆኑም አንባቢያን ሊያስተውሉት የሚገባ ነገር ቢኖር ከመንፈሳዊ ማዞሪያ የስልክ መገናኛ አገልግሎት ወጥተው ወደ መንፈሳዊ ኢንተር ኔት የተሻለ አገልግሎት መድረስ እንደሚችሉ ነው::

ስለዚህ በሚቀጥለው ምዕራፍ ለንጉሡ የመጣችውን በነገር ሁሉ ከንግሥት አስጢን የተሻለችውን የንግሥነት ዘውዷን ለመድፋት ወደ ንጉሡ የቀረበችውን የተሻለችውን ሴት ሁኔታ እንመለከታለን::

# ም ዕ ራ ፍ  አ ራ ት

## የተሐድሶ ሥራ
## በመጨረሻዋ ዘመን
## ቤተ ክርስቲያን መጀመር

# የተሐድሶ ዘመን

> “ዘግየት ብሎ የንጉሡ ቁጣ ከበረደ በኋላ እንኳ÷ ንግሥት አስጢን ስላደረገችው ነገርና በእርስዋም ላይ ስለተላለፈው ዐዋጅ ማሰላሰሉን ቀጠለ:: ስለዚህ የንጉሡ የቅርብ አማካሪዎች ከዚህ የሚከተለውን አሳብ አቀረቡለት ውብ የሆኑ ወጣት ልጃገረዶች ለአንተ ይፈለጉልህ፤ በንጉሠ ነገሥትህ ግዛት በየአገሩ ባለ ሥልጣኖችን በመሾም ውብ የሆኑትን ልጃገረዶች እየመረጡ መናገሻ ከተማ በሆነችው በሱሳ ውስጥ ለአንተ የተመረጡ ሴቶች መኖሪያ ወደ ሆነው ቤት እንዲያመጡዋቸው ይደረግ፤ የዚህም ቤት ኃላፊ ባደረከው በጃንደረባው በሄጋይ ቁጥጥር ሥር ይጠበቁ፤ የቊንጅናም ክብካቤ ይደረግላቸው:: ከእነርሱም መካከል በይበልጥ የምትወዳትን መርጠህ በአስጢን እግር ተተክታ ንግሥት እንድትሆን አድርግ::” (አስ2÷1-4)

ከላይ ባለው ጥቅስ መጀመሪያ ላይ “ዘግየት ብሎ” የሚል ቃል እናገኛለን ይህ ማለት በንግሥት አስጢንና በንግሥት አስቴር መካከል የሦስት ዓመት ልዩነት ነበር:: ንጉሥ አርጤክስስ ለእርሱ የምትሆነውን የተሻለችዋ ሴት እስክትገኝለት ድረስ የሦስት ዓመት የዝምታ ጊዜ አሳልፎአል ወይም ሦስት ዓመት “ዘግየት ብሎ ” ነበር::

እንግዲህ ይህ “ዘግየት ብሎ” የሚለው ቃል የአስጢን የንግሥናዋ ማዕረግ ከተገፈፈበት ጀምሮ ሌላ የተሻለች ሴት ለንጉሡ እስከተገኘችበት ድረስ የጊዜ ገደብ እንዳለ የሚያመለክት ቃል ነው :: ይህ ቃል በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ተፈጽሞ እናገኘዋለን :: ጌታ ኢየሱስ መጥቶ ለእስራኤላውያን እስከታየበት ጊዜ እስራኤላውያን የአራት መቶ ዓመታት የዝምታ ጊዜ አሳልፈው ነበር:: እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ከወንጌል እውነት ከወጣች በኋላ ማርቲን ሉተር የመጀመሪያውን የደህንነት ተሐድሶ እስከ ጀመረበት ጊዜ ድረስ ቤተ ክርስቲያን የ 500 ዓመታት የዝምታ ጊዜ ወይንም የጨለማ ዘመን እንዳሳለፈች ይነገራል:: በዚህ ጊዜ





ብዙ የጠላት አሠራር ወደ ሞተችው ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ቦታ ያዘ:: ሙት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ያስተናገደችው የጠላት አሠራር ውጤት እስከ አሁን ድረስ በመታደስ ላይ ነው:: ገና ሙሉ ለሙሉ ቤተ ክርስቲያን መታደስን አላገኘችም ሙሉ ለሙሉ የቤተ ክርስቲያን መታደስ ሲፈፀም የዛን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ይመጣል:: ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ ላይ:-

> “ እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና”ያለው:: (ሐ.ሥ 3÷21)(የቀ.ት)

ጌታ ኢየሱስ ያለና የነበረ የሁሉም ነገር መጀመሪያ ነው:: በምድራዊው የአገልግሎት ጊዜው ሥጋን ለብሶ እንደተገለጠ ከዚያም ሥራውን ከፈፀመ በኋላ ለሰዎች ስጦታን ሰጥቶ ወደ ሰማይ እንደ ዐረገና በአባቱም ቀኝ እንደተቀመጠ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: ነገር ግን ጴጥሮስ ሲናገር ክርስቶስ ወደ ሰማይ የወጣው ሰማይም የተቀበለው ሁሉ ነገር እስከሚታደስበት ዘመን ነው ይለናል:: ስለዚህ ጴጥሮስ በትንቢት መንፈስ ሊመጣ ያለውን ስለ ቤተ ክርስቲያን የመታደስ ዘመን ነው የተናገረው:: ከዚህ የትንቢት ቃል የተነሣ ያለንበት ይህ ዘመን ሁሉ ነገር የሚታደስበት ዘመን ነው::

በሐዋርያት ሥራ ላይ ያለው ጴጥሮስ የተጠቀመበት ቃል ”ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት” የሚለው ትክክለኛ አገላለጽ አንድ የነበረን ነገር ነገር ግን በአንድ አጋጣሚ የተበላሸን ያንን የተበላሸን ነገር እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ማደስ÷ መሥራትና መገንባት የሚለውን ቃል ትርጉም ይሰጠናል::

እግዚአብሔር ሁሉንም በሚያውቀው እውቀቱ የመካከለኛውን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ያውቃት ስለነበር በጴጥሮስ አፍ ከዚያን ዘመን በኋላ “ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ” በማለት ገለፀው እዚህ ላይ “ነገር ሁሉ” የሚል ቃል አለ “ሁሉ” በሚለው ቃል መሠረት ሁሉም ነገር እንደሚታደስና ሳይታደስ የሚቀር ነገር እንደሌለ ያመለክታል:: በሌላ አገላለጽ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገር ሁሉ ሳይታደስ ጌታ ኢየሱስ አይመጣም:: ጌታ ኢየሱስ መምጣቱ ስለማይቀር ደግሞ ሁሉ ነገር ይታደሳል:: ከዚህ የተነሣ ቤተ ክርስቲያን በመካከለኛው ዘመን ከወንጌል እውነት ሙሉ በሙሉ ወጥታ ሃይማኖታዊ መልክ ብቻ ይዛ ለብዙ ዘመን ከኖረች በኋላ በ1500 ዓ.ም

ማርቲን ሉተር ታላቁን ተሐድሶ በመባል የሚታወቀውን መዳን የሚገኘው በእምነት እንደሆነ በመግለጥ የመጀመሪያ የደህንነት ተሐድሶ ተጀመረ:: ከዚያም በየዘመናቱ ተሐድሶን ያገኙትን የእግዚአብሔር ቃል እውነቶችን ከዚህ በታች እንመለከታቸዋለን::

## ተሐድሶ የተገኘባቸው አማካኝ ዓ.ም (እ.ኤ.አ) እና መታደስን ያገኙ የቃሉ እውነቶች

በ 1500 --------- ሰው የሚፀድቀው በእምነት እንደሆነ

በ 1600 --------- የውኃ ጥምቀት

በ 1700 --------- የቅድስና ኑሮና ሕይወት

በ 1880 -------- በእምነት የሚገኝ መለኮታዊ ፈውስን መቀበል

በ 1900 -------- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በሌላ ቋንቋ መናገር

በ 1940 --------- እጆችን መጫንና ለግል የሚሆኑ የትንቢት ቃሎች መምጣት

በ 1950 --------- እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ በነፃነት ማምለክ

በ 1960 --------- ከተለያዩ የሰይጣን ቀንበርና እሥራት ነፃ መውጣት

በ 1970 --------- ደቀ መዛሙርትነትና የቤተ ክርስቲያን በቁጥር ማደግ

በ 1970 --------- የእምነት መልእክቶችና የቃሉ እውነት በትክክል ማስተማር እንዲሁም ሰዎች ከድኽነትና ከጉስቁልና ተላቀው





በብልፅግና እንዲኖሩ የሚያስችለውን የቃሉን እውነት ማግኘት

በ 1980 --------- የሐዋርያትና የነቢያት ቅባት መነሣትና ይህንንም ቅባት ተጠቃሚ የሚሆኑ ሰዎች መነሣት

በ 1990 --------- የነቢያትና የሐዋርያት ቅባት እየተስፋፋ መሄድ

# አቋሚ የተስተካከለ ቤተ ክርስቲያን

ቀደም ብለን እንዳየነው ከዝምታ ጊዜ በኋላ በመጀመሪያ እግዚአብሔር የደህንነት ተሐድሶ አደረገ:: በአስቴር 2÷2 ላይ “ ውብ የሆኑ ልጃገረዶች ይፈለጉልህ ” የሚል ቃል እናገኛለን:: ስለዚህም ተፈልገው ብዙ ልጃገረዶች ወደ ሱሳ ከተማ መጡ፤ ልጃገረዶቹ ተፈልገው መጡ እንጂ ፈልገው አልመጡም ነበር:: እግዚአብሔር ተሐድሶ ሲያስነሳ በምህረቱና በፍቅሩ እንደገና የሰው ልጆችን መፈለግ ጀመረ:: ወደ ሱሳ ከመጡት ከብዙ ልጃገረዶች መካከል አንድዋ አስቴር ነበረች:: አስቴርም ከሌሎች ልጃገረዶች ልዩ የሚያደርጋት ሌሎቹ ልጃገረዶች ራሳቸውን በራሳቸው ያቀረቡ ሲሆን አስቴር ግን ለንጉሡ የቀረበችው በመርዶክዮስ ምሪት ነበር:: የእግዚአብሔር ቃል በአንዱ መንፈስ በክርስቶስ ሥራ ወደ እግዚአብሔር ቀርባችኋል ይላል:: ቤተ ክርስቲያንንም ወደ ንጉሡ የሚያቀርባት ወስዶም በክርስቶስ አካል የሚያጠምቃት መንፈስ ቅዱስ ነው:: (1ቆሮ 12÷13)

አስቴር ወላጆቿ (እናት÷ አባት) የሞቱባት ምንም የምትተማመንበት ያልነበራት ልጃገረድ ነበረች:: ከዚያም ጊዜ ጀምሮ መርዶክዮስ ሊያሳድጋት ወስዳት ሊያሳድጋት ሲወስዳት ምንም የምትመካበት ትምክህት ያልነበራት ነገር ግን በሚያሳድጋት በመርዶክዮስ ብቻ የምትመካ ነበረች:: ስለዚህም መርዶክዮስ ወደ ራሱ አሳብ በማስገባት በልዩ ክብካቤ አሳደጋት:: (አስ 2÷2)

ዛሬም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕብረት በማድረግ ለልዩ ዓላማው እንዲለያት የምትፈልግ ቤተ ክርስቲያን የምትመካበት ምንም ነገር የሌላት ትምክህትዋን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የጣለች መሆን አለባት:: ከዚህም የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አስቴር ሲገልጽልን :-

"...እርስዋም ቁመናዋ የተስተካከለ እጅግ ውብ ልጃገረድ ነበረች::" (አስ 2÷7)

በዚሁ የንባብ ክፍል ላይ "ቁመናዋ የተስተካከለ" የሚል ሀረግ እናገኛለን:: ንግሥት አስጢን ወደ ንጉሡ መቅረብ እምቢ ካለች ወዲህ ብዙ የዝምታ ዓመታት ነበሩ:: በዚህ ጊዜ ንጉሡ ብቻውን ነበር:: ከጎኑም ንግሥተ አልባሳትዋንና ዘውዷን ጭና የምትቀመጥ ንግሥት አልነበረችውም:: አሁን ግን የተሐድሶ ዘመን ሲጀመር ንጉሡ የሚፈልጋት ቁመናዋ የተስተካከለን ሴት ነው:: ቁመና የሚለው ቃል አቋምን የሚያመለክት ነው :: አስቴር የተስተካከለ አቋም ያላት ነበረች:: ቤተ ክርስቲያን የተስተካከለ አቋም እንዳይኖራት ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ ያልተስተካከለ አመራር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲኖር ነው:: እንደ አስቴር በመንፈስ ቅዱስ ከመመራት÷ ከመደገፍና የጠራንን ጌታ ከማየት ይልቅ እንደ አስጢን የራሳችንን ጥቅምና ክብር እንዲሁም የተቀመጥንበትን ወንበር ማየት ስንጀምር አቋማችን እየተበላሸ ይሔዳል:: አቋም የሌላት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሌሎችን ማቆም አትችልም ከዚህም የተነሣ ምእመኑ የተፍረከረኩ ይሆናሉ:: አቋም የሌላት ቤተ ክርስቲያን በማዕበል የምትንገላታን ጀልባ ትመስላለች:: አስቴር ግን ላመነችበት ነገር ወደ ኋላ የማትል ብዙ ልጃገረዶች እንኳን ወደ ሱሳ ከእርስዋ ጋር ለንጉሡ ቢቀርቡም ሌሎቹ አቋማቸውን አላስተካከሉም ብላ አመለካከትዋን የማትለውጥ እንደ ንግሥት አስጢን በሴት ወይዛዝርት መካከል መወደስን የማትወድ÷ ንጉሡ ብቻ እንዲከብርባት የምትፈልግ÷ ጌታዋን ያለማስተዋል በመሮጥ ሳይሆን ጥልቅ በሆነ መረዳትና ማስተዋል ማገልገል የምትፈልግ አቋም ያላት የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነች::

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ማን ናት ብለን ስናስብ በመጨረሻው ዘመን የሚኖሩ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ የሚል አመለካከት ሊያድርብን ይችላል:: ነገር ግን የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ተብላ የምትጠራው በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን ሥራና





የእግዚአብሔርን የዘመኑን አሳብ የተረዳች በተረዳችውም የእግዚአብሔር አሳብ መሠረት ዋጋን ከፍላ የምትጓዝ÷ አቋም ያላትና ወደ ሙላቱ የምትገሰግስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ያቺ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ተብላ ትጠራለች:: እንዲሁ አቋሟን ሳታስተካክል የንግሥት አስጢንን አመለካከት ይዛ የምትጓዝ ቤተ ክርስቲያን የንግስት አስጢን ዓይነት አመለካከት ርዝራዥ ያላት ቤተ ክርስቲያን ተብላ ትጠራለች እንጂ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ተብላ አትጠራም:: የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን መሪዎችዋና አገልጋዮችዋ ባላቸው እውነተኛና ግልፅ አቋም ሰዎችን ይማርካሉ እንጂ በወሬና በቅስቀሳ ሰዎችን ለመማረክ አይሞክሩም:: የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን አቋሟን ግልጽ አድርጋ በመናገር እንዲከተልዋት ታደርጋለች እንጂ አቋሟን ባለመግለጥ የሚከተልዋትን ግራ አታጋባም::

ስለዚህ ጌታን መከተል በአቋም ቤተ ክርስቲያንን መምራት ደግሞ በታላቅ አቋም መሆን አለበት:: አስቴርም አቋም ያላት ስለነበረች በጃንደረባው በሄጋይ ፊት ሞገስ አገኘች::

"አስቴርም ሄጋይን ደስ አሰኘችው በፊቱም ሞገስ አገኘች..." (አስ 2÷9)

አቋም ያላት ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን በቅዱሳን መላእክት ፊት ምስክርነት ስለምታገኝ ግርማና ክብር አላት:: እንዲሁም በሰይጣንና በመንግሥቱ ላይ የአስፈሪነት ግርማና ሞገስን የምታገኝ ቤተ ክርስቲያን አቋም ያላት ናት:: በአስቴር ምዕራፍ 2÷15 ላይም "ባያት ሁሉ ዘንድ ሞገስን ያገኘች ነበረች " የሚል ቃል እናገኛለን ሞገስ ሊያስገኝላት የቻለው ዋናው ነገር አቋሟ ነበር::አቋም ያላት ቤተ ክርስቲያን እንደ ንፍታሌም በሞገስ የጠገበች ናት በሞገስ ከጠገበች ደግሞ የእግዚአብሔርን በረከት ትሞላለች የተሰፋ ቃሉንም ትወርሳለች:: (ዘዳ 33÷23)

ስለዚህም እንደ አስቴር እያንዳንዳችን አቋም ኖሮን ሞገስን እንድናገኝና ቤተ ክርስቲያናችንና አገልግሎታችን በፊቱ እንዲከብር ጌታ ይፈልጋል::እንግዲህ እግዚአብሔር ከመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ አቋምን ይፈልጋል::

# የጊዜ ተጠቃሚ የሆነች ቤተ ክርስቲያን

"፡፡ጊዜም ሳይባክን ወዲያውኑ ጥሩ ምግብ እንዲሰጣትና የሰውነትዋ ቅርጽ በመታሸት እንዲስተካከል በማድረግ በቁንጅና ክብካቤ እንድትጠበቅ ወሰነ... " (አስ 2÷9)

በዚህ ጥቅስ መጀመሪያ ላይ "ጊዜ ሳይባክን" የሚለውን ቃል እናያለን:: በንግሥት አስቴር የምትመሰለው ቤተ ክርስቲያን አቋም ስላላት ጊዜዋን በከንቱ ነገር ላይ ማባከን አትፈልግም ንጉሡም የእርስዋ ጊዜ እንዲባክን አልፈለገም:: በንግሥት አስጢን የምትመሰለው ቤተ ክርስቲያን ግን አቋሟን ያበላሸችና እምቢ ያለች ስለነበረች ቤተ ክርስቲያን ማግኘት የሚገባትን በረከት በጊዜው እንዳታገኝ ጊዜ አባክናለች:: አሁን ግን አስቴር አቋሟን አስተካክላ ብቅ ስትል በከንቱ ያለፈውን ጊዜ ለመበቀል ንጉሡ ጊዜ መፍጀት አልፈለገም::

ከዚህም የተነሣ በጃንደረባው በሄጋይ አማካኝነት ጊዜ ሳይባክን ጥሩ ጥሩ ምግብ እንዲሰጣት ተወሰነ:: እዚህ ላይ ምግብ የእግዚአብሔር ቃል ምሳሌ ነው:: ስለዚህም ጊዜ ሳይባክን አቋም ላላት ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ጥሩ የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ እንዲፈስላት ንጉሡ ወሰነ:: ከውሳኔው የተነሣ አስደናቂ የሆነ የቃሉ መገለጥ አቋም ባላት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሁንም እየፈሰሰ ነው:: በዚህም አያበቃም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚመጣው የቃሉ ምስጢር ገና ተጀመረ እንጂ አላበቃም:: ነገር ግን አንድ መገንዘብ ያለብን ነገር ንጉሡ አቋም ካላት ቤተ ክርስቲያን ጋር ጊዜው እንዳይባክን ወስኖአል:: የሰው አመለካከት ሥርዓትና ወግ የንጉሡን ውሳኔ ሊሽረው ስለማይችል ያለን አማራጭ ጌታ ጊዜው ሳይባክን ቀብቶ በሚሰጠን አገልጋዮች በኩል የሚመጣውን የቃሉን እውነት ተቀብሎ መታዘዝ ብቻ ነው::

አቋም ያላት ቤተ ክርስቲያን ከንጉሡ ጋር ጊዜዋን የምታጠፋ ንጉሡም በጊዜው የሚሰጣትን የቃሉን እውነት የምትመገብና ሌሎችንም የምትመግብ ናት:: አስጢን ግን የባሏን የንጉሡን የክብር ግብዣ መመገብ ሲገባት በክብር ስፍራ ተቀምጣ መመገብ እምቢ እንዳለች ሁሉ ዛሬም ጌታ





ያዘጋጀውን የክብር ግብዣ ለመመገብ የማትዘጋጅ ቤተ ክርስቲያን ሌሎችን መመገብ ፈጽሞ አትችልም::

የእግዚአብሔር ቃል ፍቺ ወደ አገልጋዮች የሚፈሰው አገልጋዮች አቋም ሲኖራቸው ነው:: አቋም ከሌላቸው የሚቀበሉትን የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሌሎች ማስተላለፍ አይችሉም:: ለምን ቢባል ፈሪሳዊያንና የምኩራብ አለቆችን ስለሚፈሩ አቋም ወደ ሌላቸው አገልጋዮች የቃሉ መገለጥ አይመጣም:: ለውጥ ከፈለግን አቋም እንዲኖረን ያስፈልጋል እግዚአብሔር ቃሉን ገልጦላቸው ተሐድሶን ያመጡ ሰዎች አቋም ያላቸው ነበሩ::

ስለሆነም በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጊዜ አይባክንም እግዚአብሔርም አስደናቂ የሆነውን የቃሉን ምስጢር እየገለጠ ይመግባታል:: በኤፌሶን 5÷30 "ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል ይንከባከበውማል" ተብሎ እንደተጻፈው ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የሚመግባት በኤፌሶን 5÷26 ላይ እንደተገለፀው እንደ ውኃ አጥቦ በሚያነጻው ቃሉ ነው:: ይህም ጌታ ከመምጣቱ በፊት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀደስና የፊት መጨማደድና ነውር የሌለባት ሆና እንድትገኝ ነው:: የጌታ መምጫ ደግሞ ስለተቃረበ ጊዜ ሳይባክን ጌታ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የምትዘጋጅበትን ጥሩ ጥሩ ምግብ እየመገባት ነው:: ጥሩ ምግብ የምትመገበውን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ሲገልጽልን :-

" ሙሽራይቱ

ውዴ ከሌሎች ጕልማሶች ጋር ሲነጻጸር በዱር ዛፎች መካከል አምሮ እንደሚታይ የፖም ዛፍ ነው፤ እኔም እጅግ ደስ ብሎኝ በጥላው ሥር ዐረፍሁ፤ ጣፋጭ ፍሬውንም በመመገብ ተደሰትሁ ወደ ምግብ አዳራሹ አስገባኝ፤ ፍቅሩንም እንደ ሰንደቅ ዓላማ በእኔ ላይ ከፍ ከፍ አደረገ:: እኔ በፍቅሩ ተይዤ ስለታመምሁ፤ ዘቢብ እየመገባችሁ አበረታቱኝ ፤ በፖም ፍሬም አስደስቱኝ"( መኃ.መኃ 2÷3-5)

በዚህ ክፍል ላይ "ሙሽራይቱ " (ቤተ ክርስቲያን) በብዙ ኃያላን መካከል ወደር በማይገኝለት በክርስቶስ ጥላ ሥር ቁጭ ብላ ጣፋጭ የሆነውን የፖም ፍሬ ትበላ ነበር:: እንዲሁም ወደ ምግብ አዳራሹ ገብታ ወይን

ትመገብ ነበር:: በመኃ.መኃ7÷8-9 ላይ ደግሞ "ሙሽራው" (ክርስቶስ ኢየሱስ) ወደ ምግብ አዳራሹ ገብታ ስለተመገበችው ቤተ ክርስቲያን (ስለ ሙሽራይቱ) ሲመሰክርላት:-

> "…. የእስትንፋስሽ መዓዛ እንደ ፖም ፍሬ ሽታ ነው
> የአፍሽም መዓዛ እንደ መልካም ወይን ጠጅ ነው::" ይላታል
> (መኃ.መኃ 7÷8-9 )

እንግዲህ በዚህ ባለንበት ዘመን የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ጊዜዋን ሳታባክን ወደ ንጉሡ የምግብ አዳራሽ የገባች በወርቁ አልጋ ላይ ዐርፋ ጣፋጭ የሆነውን የቃሉን መገለጥ እየተመገበች የእስትንፋስዋን መልካም መዓዛ የምታሸትት ጉባኤዋን በወይን ጠጅና በፖም መዓዛ የምታውድ ሙሽራው እስኪመሰክርላት ድረስ የተለወጠች በእግዚአብሔር ቃል የተሞላች ነች::

*"ትጉህ ገበሬ በቂ ምግብ ይኖረዋል ጊዜን በከንቱ የሚያባክኑ ሰዎች ግን ሁል ጊዜ እንደ ደኸዩ ይኖራሉ::" (ምሳ28÷19)*





# ቅርጿን ለማስተካከል የወሰነች ቤተክርስቲያን

> "…ጊዜም ሳይባክን ወዲያውኑ ጥሩ ምግብ እንዲሰጣትና የሰውነትዋ ቅርጽ በመታሸት እንዲስተካከል በማድረግ በቁንጅና ክብካቤ እንድትጠበቅ ወሰነ፤… " ( አስ 2÷9)

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ጥሩ ምግብ እየተመገበች በቃኝ እንድትል ሳይሆን ወደ ሌላ ክብር እንድትገባ የሰውነትዋ ቅርጽ በመታሸት እንዲስተካከል በልዩ ክብካቤ እንድትያዝ ተወሰነ::

ንግሥት አስቴር እንደተመለከትነው ጥሩ የሆነ አቋም ያላት እውነተኛ የሆነውን የቃሉን መገለጥ የምትመገብ ነበረች:: ቅርጽ ግን ይጎላት ነበር:: ንጉሡ ወደ ሙላቱ ይዞአት መሄድ የሚፈልገው ጥሩ ምግብ የምትመገበውን እንዲሁም የሰውነትዋ ቅርጽ በመታሸት የተስተካከለላትን በአስቴር የምትመሰለው ቤተ ክርስቲያንን ነው:: ስለዚህ አቋም ያላትንና ጥሩ ምግብ የምትመገበውን አስቴርን ቅርጽ እንዲኖራት ንጉሡ ወሰነ:: አስቴር ጥሩ አቋም ያላት ብትሆንም ሰውነትዋ ቅርጽ ስለሌለው የሰውነትዋ ክፍሎች ውበቱ በቀላሉ ሰዎችን አይማርክም ነበር::

ንግሥት አስጢን እጅግ የተዋበች ስለነበረች ንጉሥ አርጤክስስ ለአለቆችና ለባለሥልጣናት ሊያሳያት ፈልጎ እርስዋ ግን እምቢ በማለትዋ ከንጉሡ ክብር የጎደለች ሆነች:: አስቴር ደግሞ በርግጥ አቋም አላት ሞገስንም አግኝታለች ነገር ግን ወደ ንጉሡ ሙላት ገብታ ለአለቆችና ለባለሥልጣናት ፊት ለፊት ከፍ ከፍ ብላ እንድትታይ እጅግ የተዋበች መሆን አለባት:: እጅግ የተዋበች ለመሆን ደግሞ የጎደላት ቅርጽ ብቻ ነበር:: ስለዚህም በመታሸት ቅርጽ ወደምትይዝበት ወደ መታሻ ክፍል ገባች:: አስቴር ቅርጽ ይጎድላታል ስንል ምን ማለታችን ነው ? ምንስ መንፈሳዊ ትርጉም አለው ? የሚለውን ለመመልከት ከዚህ የሚቀጥለውን አሳብ አስተውለን እንመልከት::

መጽሐፍ ቅዱሳችን ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ይዘት እንዳላት በብዙ ቦታ በተለያየ ምሳሌያዊ አገላለጽ ተገልጾ እናየዋለን :: ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱን እንመለከታለን :-

## ሀ) ቤተ ክርስቲያን በሕንጻ ስትመሰል

> "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል የማእዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል በእርሱም እናንተም ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ::"
>
> (ኤፌ 2÷20- 22) (የቀ.ት)

በዚህ ክፍል ላይ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ እንደታነጽንና የማእዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ እንደሆነ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበሉ አማኞች ሁሉ የተጠረቡ ድንጋዮች ሆነው በተመሠረተው መሠረትና በማእዘኑ ድንጋይ ላይ እንደሚጋጠሙና ጥሩ ቤት ለመሆን ዕለት ዕለት እየተገነባን እንደምንሄድ ይነግረናል:: ሕንጻው በተገነባ ቁጥር ቅርጽ እየያዘ ይሄዳል በር÷ መስኮትና ጣራ ይኖረዋል:: በር÷ መስኮትና ጣራ የሌለው ሕንጻ በደንብ ያልተገነባና ያላለቀ ቤት÷ ምንም ውበት የሌለው÷ የማይማርክ÷ ቅርጽ የሌለው÷ በቂ አገልግሎትም መስጠት የማይችል ነው:: ንግሥት አስጢን ደግሞ የዚህ ሕንጻ ምሳሌ ነበረች:: እምቢ ባለች ጊዜ ግን የማእዘኑ ድንጋይ ጠላት ሆነባት:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው :-

> " ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማእዘን ራስ ሆነ ተብሎ የተጻፈው ምንን ያመለክታል ? በዚያ ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ ይሰበራል ድንጋዩ በላዩ ላይ የሚወድቅበት ሰው ግን ይጨፈለቃል":: (ሉቃ20÷17-18)

በዚህ ክፍል ላይ "ድንጋዩ በላዩ ላይ የሚወድቅበት ሰው ግን ይጨፈለቃል" ሲል ከማእዘኑ ድንጋይ ጋር እንደሚገባ ካልተጓዝን የማእዘኑ ድንጋይ እኛ ላይ ወድቆ ይጨፈልቀናል ማለቱ ነው:: በንግሥት አስጢን የምትመሰለዋ ቤተ ክርስቲያን እምቢ ከሰማይ ለመጣው ራእይና ሰማያዊ ተልዕኮ አልታዘዝም ባለች ጊዜ የማእዘኑ ድንጋይ ወድቆባት ተጨፈለቀች::





ቤቱም ቅርጽ ኖሮት ቤት ሊያሰኘው የቻለውን በሩን÷ መስኮቱን÷ ጣራውንና በቤቱ ውስጥ የተቀመጡ ዕቃዎችን ሁሉ አጣች:: ይህ ማለት ቤተ ክርስቲያን ከወንጌል እውነት ስትወጣ ቤተ ክርስቲያንን ቅርጽ እንዲኖራት የሚያደርጉትን ክርስቶስ ኢየሱስ ለአካሉ የሰጣትን በኤፌሶን መልእክት 4÷11 ላይ የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን ውበትዋ የሆኑትን አምስቱን ታላላቅ የመንግሥቱን ውብ ስጦታዎችና ሌሎችንም ስጦታዎች ጨምራ አጣች:: ከዚህ የተነሣ ንግሥት አስጢን (የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን) ቅርጽ የጎደላት÷ የማትማርክ ከንጉሡ በጣም የራቀች ሆነች:: አስቴር ግን ንግሥት አስጢን የጣለችውን የቤተ ክርስቲያን ቅርጽ እንደገና ለማግኘት ቅርጽ ወደምትይዝበት መታሻ ክፍል ገባች::

## ለ) ቤተ ክርስቲያን በአካል ስትመሰል

በአንደኛ ቆሮንቶስ 12÷12-30 ላይ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ከየቦታው ተሰብስበው አንድ አካል የሆኑበት የሁሉም ራስ ደግሞ ክርስቶስ እንደሆነ ይነግረናል:: እያንዳንዱ አካል የራሱ የሆነ የሥራ ድርሻ አለው:: እጅ የራሱ ሥራ አለው÷ ዐይንም የራሱ የሆነ ሥራ አለው÷ ሁሉም ግን ከአእምሮ በሚወጣው ትእዛዝ ይንቀሳቀሳሉ ስለዚህ ክርስቶስ :-

— በመጀመሪያ አካሉን ጠራ:: (1ቆሮ 12÷12 )

— ሁለተኛ በየስፍራው ቦታን እንዲይዙ አደረገ::(1ቆሮ12÷15)

— ሦስተኛ በአካሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች የተለያየ አገልግሎት እንዲይዙ አደረገ:: (1ቆሮ 12÷28)

እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ በኤፌሶን ምዕራፍ 4÷4 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ "አንድ አካል አለ" ይለናል ያም አካል ክርስቶስ ራስ የሆነበት ነው:: በቁጥር ሰባት ላይም በአካሉ ውስጥ "ክርስቶስ ለመስጠት በወሰነው መጠን ለያንዳንዳችን ጸጋ ሰጥቶናል" ይላል:: በቁጥር ዐሥራ አንድ ላይ የሰጠውን ስጦታ ሲያስቀምጠው "እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት÷ አንዳንዶቹ ነቢያት÷ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች÷ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች÷ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ" በማለት ያጠቃልለዋል::

እንግዲህ ክርስቶስ ጎልተው የሚታዩ ስጦታዎችን ለአካሉ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል:: በመካከለኛው ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እውነት አልታዘዝም ስትል ያጣችው እጅግ ያስዋባትን የአገልግሎት ስጦታን ጨምሮ ነበር:: እምቢ ስትልም በአካሉ ውስጥ ያሉትን ሐዋርያቶችን፥ ነቢያቶችን፥ ወንጌል ሰባኪዎችን፥ እረኞችን፥ አስተማሪዎችን ሁሉ አጣች:: ቤተ ክርስቲያን ካለነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች ቁመና ያላት አካል ብቻ ነገር ግን ቅርጽ የጎደላት የማትማርክ ትሆናለች:: በሌላ አገላለጽ ክርስቶስ ኢየሱስ አካል የሚሆኑ ብዙ ሰዎች ሰበሰበ ሁሉንም ቦታ ቦታ አስያዛቸው አንድም አካል ሆኑ አካሉም ቅርጽ እንዲኖረውና የሚማርክ እንዲሆን አምስቱን የመንግሥቱን ታላላቅ የአገልግሎት ስጦታዎችን አስቀመጠ::

ቀደም ብለን እንዳየነው ከንግሥት አስጢን ውድቀት በኋላ እግዚአብሔር እንደገና ተሐድሶን ሲያደርግ በመጀመሪያ የደህንነትን ተሐድሶ ከዚያ በኋላ ቤተ ክርስቲያን አቋም ያላት እንድትሆንና ጥሩ ጥሩ ምግብ እንድትመገብ ተደረገ:: ቅርጽ ስላልነበራት ግን <u>በመታሸት ቅርጽ እንድትይዝ</u> የተሐድሶ ሥራ በአስቴር ምዕራፍ 2፥9 ላይ መጀመሩን ተመልክተናል::

ስለዚህ አስቴር አቋም ያላት የእግዚአብሔርን የቃሉን መገለጥ የምትመገብ እንደውም ባያት ሁሉ ፊት ሞገስን ያገኘች ነበረች:: ነገር ግን አስቴር ቅርጽ እንዲኖራት ወደ መታሻ ክፍል ገባች ማለት ንግሥት አስጢን የጣለችውን የቤተ ክርስቲያን ውበትና ቅርጽ የሆኑትን የአገልግሎት ስጦታዎች ለመቀበል ቅርጽ እንደሌላት አምና አስቴር በዘይትና በከርቤ በጣፋጭም ሽቶ በመታሸት ቅርጽ ወደምትይዝበት ክፍል እራስዋን አስገባች:: ይህንንም በደንብ ለመረዳት ቤተ ክርስቲያንን ቅርጽ ስለሚያስይዝዋት የአምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች በመጠኑ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን::

# ም ዕ ራ ፍ  አ ም ስ ት

## ቤተ ክርስቲያንን ቅርጽ የሚያስይዝዋት አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች

# በአገልግሎት ቅባት የሚገኘውን ዋጋ መቀበል

በኤፌሶን 4÷11 ላይ እንደምንመለከተው ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ስጦታን ሰጥቷል::“ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ::”(ኤፌ 4÷8) ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ በእነዚህ የአምስቱ የአገልግሎት ቅባት በሙላት አገልግሏል :: ቅባት የሚተላለፍ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳችን በብዙ ቦታ ይነግረናል:: ለምሳሌ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲረዱት ለሽማግሌዎቹ በሙሴ ላይ ከነበረው መንፈስ (ቅባት) አካፈላቸው::(ዘኁ11÷17,25)ኢያሱ ሙሴን ተከትሎ እንዲያገለግል ሙሴ እጁን ጫነበት የጥበብን መንፈስ ተቀበለ:: (ዘዳ 34÷9) ኤልያስ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ በመጎናፀፊያው ላይ ያለውን ቅባት ለኤልሳዕ አስተላለፈ:: (2ነገ 2÷12-14) እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ በእርሱ ላይ ያለውን ቅባት አንድ ሰው ሊሸከመው ስለማይችል በአምስት ቦታዎች በመከፋፈል ሐዋርያት÷ ነቢያት÷ ወንጌላውያን÷ እረኞችና አስተማሪዎች ብሎ ቅባቱን እከፋፍሎ ለቤተ ክርስቲያን ስጦታን ሰጠ::

ይህም ስጦታ በቤተ ክርስቲያን የሚሠራው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ የእግዚአብሔርንም ልጅ በማወቅና በማመን ወደሚገኝ አንድነት ደርሳ ክርስቶስ ፍፁምና ሙሉ እንደሆነ ቤተ ክርስቲያንም ሙሉ ሰው እንድትሆን ነው:: (ኤፌ 4÷13)

እነዚህ አምስቱ የክርስቶስ የመንግሥቱ ታላላቅ ስጦታዎች ናቸው:: ያለነዚህ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያን ወደ ፍፁምነት አትገባም፣ ሙሉ ሰውም አትሆንም:: በኤፌሶን 4÷7 ላይ “ክርስቶስ ለመስጠት በወሰነው <u>መጠን</u> ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል” የሚል ቃል እናገኛለን:: ይህ <u>“መጠን”</u> የሚለው ቃል ሁሉም የየራሳቸው የሆነ ከጌታ የተቀበሉት የቅባት መጠንና የተለያዩ የአገልግሎት ድርጊቶች (ተግባር) እንዳላቸው ያሳያል:: ሌላው ነገር እነዚህ አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች ጌታ ኢየሱስ በሰዎች ውስጥ ነው ያስቀመጠው:: ጌታ ኢየሱስ ባገለገለበት ስፍራና አገልግሎቱን በተቀበሉበት ስፍራ በውስጡ ያለው ቅባት እየፈሰሰ ሌሎችን ይነካ ነበር::ጌታ ሰባዎቹን ደቀ መዛሙርት ሥልጣንና ከእርሱም ኃይል (ቅባት)





ካካፈላቸው በኋላ ወንጌልን እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ተአምራትንም እንዲያደርጉ ላካቸው:: (ሉቃ10÷1-2) ሲልካቸውም አገልግሎት የሚተላለፍ ከጌታ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ቁልፍ የሆነ ምስጢር እንዲህ በማለት ገለፀላቸው :-

“ እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል እናንተን የማይቀበል እኔን አይቀበልም እኔን የማይቀበልም የላከኝን አይቀበልም::“ (ሉቃ 10÷16)

እዚህ ላይ ልናስተውል የሚገባን ነገር ኢየሱስን ቀብቶ የላከው እግዚአብሔር አብ ነው:: ኢየሱስን የማይቀበል ሁሉ የላከውን አብን አልቀበልም ማለቱ ነው:: እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ የራሱን ቅባት በአምስት ቦታ ከፋፍሎ ቀብቶ የላካቸውን ሰዎች አንሰማም ብንል ጌታን አለመስማት ነው:: አንቀበልም ብንል ደግሞ የስጦታውን ምንጭ (ሰጪ)ጌታን አንቀበልም ማለታችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: እንዲሁም በሌላ ስፍራ ጌታ ሲገልጽ:-

“ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል::” (ማቴ10÷41)

ይህንን ጥቅስ ስናይ ነቢይን የሚቀበል <u>የነቢዩን</u> ዋጋ ያገኛል አይደለም የሚለው:: ነገር ግን <u>የነቢይን</u> ዋጋ ያገኛል ነው የሚለው:: ይህ ማለት አንድን ነቢይ ነቢይ የሚያስብለው የነቢይነትን ቅባት ከጌታ ስለተቀበለ ነው:: ያለበለዚያ ግን ነቢይ ተብሎ ሊጠራ አይችልም:: ነቢይን የሚቀበል በነቢዩ ውስጥ ያለውን እጅግ የከበረ ዋጋ ያለውን ቅባት ተጠቃሚ ይሆናል ማለት ነው:: ስለዚህ ነቢይን የሚቀበል ነቢይ ሆኖ በተጠራው ሰው ውስጥ ያለውን ኢየሱስ ያስቀመጠውን ዋጋ ያለውን የነቢይን የቅባቱን ድርጊት ተቀባይ ወይም ተጠቃሚ ይሆናል:: <u>“ዋጋ”</u> የሚለው ቃል ውድ÷ የከበረ÷ ጥቅም ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው::

አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ነቢይ ሆኖ የተጠራውን ሰው ይቀበላሉ ነገር ግን ነቢዩ በተሰጠው ቅባት የሚያስተላልፈውን ዋጋ ያለውን መልእክቱን ግን አይቀበሉም:: እንዲሁም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እረኞች አላቸው፣ እረኞችም አሉን ብለው ይናገራሉ ነገር ግን በእረኛው ውስጥ እግዚአብሔር ያስቀመጠውን ዋናውን የእረኛውን የቅባቱን ድርጊት

አይቀበሉም:: ነገር ግን ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል ሲል ነቢይ የሚለው ስም ስላለው ሳይሆን ነቢይ ስለሆነ ከእግዚአብሔር የከበረውን መልእክት ያመጣልናል፣ በቅባቱ እንጠቀማለን፣ ብላ የምትቀበል ቤተ ክርስቲያን የነቢይን የቅባቱን ድርጊት ዋጋ ያለውን የከበረውን ነገር ታገኛለች እንጂ ሰዎችን ተቀብላ የአገልግሎት ቅባታቸውን ድርጊት ካልተቀበለች ዋጋ የለውም::

ስለዚህ ወንጌላዊን ብቻ የምትቀበል ቤተ ክርስቲያን የወንጌላዊውን ቅባት ብቻ ተጠቃሚ ትሆናለች:: አስተማሪን የምትቀበል የአስተማሪውን ቅባት ብቻ ተጠቃሚ ትሆናለች:: እንዲሁም እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ ወንጌላውያን፥ እረኞችና አስተማሪዎች እንዲኖሩ ይፈልጋል ያለነሱ የቅባት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን ልትይዝ የሚገባትን ቅርጽ አትይዝም::

# የአምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች አስፈላጊነት

በዚህ ርዕስ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ቦታዎችን በማየት አምስቱ ታላላቅ የክርስቶስ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን እንዴት አስፈላጊ እንደሆኑ ዛሬም የአገልግሎት ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ ሰጪና ጠቃሚ እንደሆኑ እንመለከታለን::

## ሐዋርያት

ሐዋርያትና ነቢያት ተመሳሳይ አገልግሎት አላቸው:: ይህም እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ እንድትመሠረት አድርጓል ወይም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ በሐዋርያትና በነቢያት የተጀመረ ነው:: እነዚህ ሁለቱ አገልግሎቶች ባለንበት ዘመን ለቤተ ክርስቲያን በጣም ጠቃሚዎች ናቸው:: ምክንያቱም እነርሱ የመሠረቱትን ሕንጻ እነርሱ መጨረስ አለባቸው:: ካለ ሐዋርያትና ካለ ነቢያት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፍፁም ሙላት አትገባም::





የሐዋርያትና የነቢያት ቅባት ልክ እንደዘሩባቤል ቅባት ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ስለ ዘሩባቤል ሲናገር :-

> "የዘሩባቤል እጆች ይህንን ቤት መሠረቱ የእርሱም እጆች ይፈጽሙታል" (ዘካ 4፥9)(የቀ.ት)

የቤተ መቅደሱ ሥራ በዘሩባቤል ተጀምሮ በዘሩባቤል እንደ ተፈፀመ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሥራ በሐዋርያትና በነቢያት ቅባት የተመሠረተ ሲሆን በእነርሱም ቅባት የመቅደሱ ሥራ ይፈጸማል:: ሐዋርያት ነገሮችን የመጀመር ቅባት፥ የመፈጸም ቅባት፥ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በትክክል የመገንባት ቅባት፥ የሰይጣንን ክበባ በጣጥሶ የሚያልፍ የጦርነት ቅባትና እንዲሁም ከመንጋው ነውርን እየመነጠረ የሚያወጣ ቅባት አላቸው:: ይህም አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን ቅርጿን እንዳትለቅ ትልቅ ቦታ አለው:: ስለዚህም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ስምንት ላይ ካለው ክፍል ወስደን ቤተ ክርስቲያን እንዴት በሐዋርያት ቅባት ቅርጽ እንደምትይዝ እንመለከታለን::

## የሐዋርያት ቅባት በሰማርያ ቤተ ክርስቲያን

በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት አማኞች ወደ ተለያዩ አገር ሲበተኑ ወንጌላዊ ፊሊጶስ ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው ሕዝቡም የፊሊጶስን ቃል ሰሙ:: በሌላ አገላለጽ ሕዝቡ በፊሊጶስ ውስጥ ያለውን የወንጌላዊ ቅባት ተቀበሉ:: ብዙ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ፣ ብዙ ተአምራት በፊሊጶስ አገልግሎት ተደረገ ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፣ እርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮሁ ከሰዎች ላይ እየለቀቁ ወጡ:: ይህ ሁሉ ሲሆን በሰማርያ አንድ ሲሞን የሚባል ታላቅ ጠንቋይ ነበር፣ በሚያደርገውም የጥንቆላ ሥራ የሰማርያን ሰዎች ታላላቆችንና ታናናሾችን ያሳተ፣ የእግዚአብሔር ኃይል ይኼ ነው ብለው ሰዎች ያደምጡት የነበረ ከብዙ ዘመን ጀምሮ በጥንቆላ ሥራ የታወቀ ነበር:: ሲሞን በፊሊጶስ አገልግሎት ጌታ ኢየሱስን አምኖ ተቀበለ እንዲሁም ተጠመቀ ከዚህም አልፎ ከፊሊጶስ ጋር ይተባበር ነበር::(ሐ.ሥ8፥4-13)

እዚህ ላይ ፊሊጶስ የተቀባ ወንጌላዊ ነበር:: በድንቅና በተአምራት ወንጌልን ይሰብክ ነበር፣ ጠንቋዩ ሲሞንን እንኳ ሳይቀር በወንጌላዊ ቅባት ወደ ጌታ አምጥቷል:: ነገር ግን በሰማርያ ከተማ ከዚህ በላይ መሄድ

አልቻለም ነበር:: ምክንያቱም በኤፌሶን 4÷7 ላይ እንደምናየው ለወንጌላዊ የተሰጠው የቅባት መጠን ስላለው ቅባቱም ወንጌልን ከመስበክ ሰዎችን ወደ ጌታ ከማምጣትና በድንቅና በተአምራት ስጦታ ሥጋዊ ከሆነ በሽታ ሰዎችን ከመፈወስ አላለፈም ነበር::

ነገር ግን በዚሁ በምዕራፍ 8÷14 ላይ " በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላቸውን በሰሙ ጊዜ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ ሰማርያ ላኩላቸው " ይላል:: እዚህ ላይ ለምንድነው የላኩላቸው? ሰማርያ እንደሆነ በድንቅና በተአምራት ተሞልታለች !! ሰዎችም የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላቸውንና ጠንቋዩ ሲሞን እንኳ ሳይቀር ጌታን እንደተቀበለ ያውቃሉ:: ታዲያ ለምን ተላኩ? መልሱ አንድ ነው ይህም የወንጌላዊን ቅባት እንደተቀበሉ የሐዋርያትንም ቅባት እንዲቀበሉ ነው::

ጴጥሮስና ዮሐንስ በሰማርያ በደረሱ ጊዜ የሰማርያ አማኞች መንፈስ ቅዱስ አልተቀበሉም ነበር:: በሐዋርያትም እጅ መጫን የሰማርያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ:: በሐዋርያት እጅ መጫን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በልሳን መፀለይ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም መንፈሳዊ ስጦታ እንደተቀበሉ ከሌሎች የሐዋርያት አገልግሎት መመልከት ይቻላል:: ለምሳሌ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች " በእምነት እንድትፀኑ የሚያደርጋችሁን መንፈሳዊ ስጦታ ላካፍላችሁ ስለምፈልግ ላያችሁ እመኛለሁ" ( ሮሜ 1÷11) "<u>ላካፍላችሁ</u>" ማለቱ ኢየሱስ ካካፈለው የሐዋርያ ቅባት እርሱም ከዚህ ቅባት ለሌሎች ላካፍል ማለቱ ነበር:: እዚህ ላይ ልናስተውል የሚገባን አማኞች ሐዋርያት እጅ ስለጫኑባቸው ሐዋርያ ይሆናሉ ማለት አይደለም:: ነገር ግን በሐዋርያት ቅባት በኩል በሚያልፈው የእግዚአብሔር ኃይል ተካፋይና ተጠቃሚ ይሆናሉ ማለት ነው:: ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 19÷5 ላይ እጁን ጭኖ ለኤፌሶን አማኞች ሲፀልይላቸው መንፈስ ቅዱስ ተቀበሉ÷ ትንቢትን ተናገሩ÷ የትንቢትንም ስጦታ ተቀበሉ:: እንዲሁም ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በሐዋርያ ቅባት ፀልዮለት መንፈሳዊን ስጦታ ተቀብሏል:: (2ጢሞ 1÷6) ስለዚህ ሐዋርያቶች ለሰማርያ አማኞች የጸጋ ስጦታ አካፍለዋቸው እንደነበር መገመት ይቻላል ይህም ብቻ አይደለም :-

<u>በሐዋርያት ላይ ያለ ቅባት ቤተ ክርስቲያንን የሚበረብርና ቅርጽ የሚያስይዝ ቅባት ነው::</u> በመጀመሪያ ሲሞን ጠንቋይ ነበር ነገር ግን በጌታ ኢየሱስ አምኘአለሁ የሚል ሰው ነበር፤ከዚያም ሲሞን ሞቱን





በሚመስል ሞት ትንሳኤውን በሚመስል ትንሳኤን በመካፈል የተጠመቀ ሰው ነበር፤ ሌላው በጣም የሚገርመው ሲሞን ከፊሊጶስ ጋር <u>ይተባበር</u> ነበር:: "<u>ይተባበር</u>" ነበር ሲል አብሮ ይወጣና ይገባ÷ በአገልግሎቱም ከወንጌላዊ ፊሊጶስ ጋር አብሮ እስከ ማገልገል ደርሶ ነበር ማለቱ ነው:: ወንጌላዊ ፊሊጶስ የሲሞንን መዳን÷ መጠመቅና አብሮ ማገልገልን እንጂ እውነተኛ ማንነቱንና የልቡን አሳብ አልተረዳም ነበር::

ነገር ግን ሐዋርያት ወደ ሰማርያ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ የሲሞን እውነተኛ ማንነቱ ተገለጠ ለሰዎች ታየ ይፋም ወጣ ይኸውም :-

1. የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለማግኘት ፈለገ (ሐ.ሥ8÷20)

2. ልቡ በእግዚአብሔር ፊት ቅን አልነበረም (ሐ.ሥ 8÷21)

3. በመራራ ቅንዓት የተሞላና የኃጢአት እስረኛ ነበር (ሐ.ሥ 8÷23)

ሐዋርያት ባሉበት ስፍራ የምእመንና የአገልጋዮች እውነተኛ ማንነት ይገለጣል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ሲያገለግል ምንም ነገር ሳይናገር በእርሱ ላይ ካለው ቅባት የተነሣ "ከአማኞች ብዙዎቹ ክፉ ሥራቸውን በግልጽ እየተናዘዙ ይመጡ ነበር"ይላል(ሐ.ሥ19÷18)እዚህ ላይ ስንመለከት ያላመኑ ሰዎች አልነበሩም ክፉ ሥራቸውን እየተናዘዙ የሚመጡ የነበሩት:: በክፉ ሥራ የተያዙት አማኞችና በጌታ ኢየሱስ የዳኑ ነበሩ እንዲሁም ባለንበት ዘመን የምእመንና የአገልጋዮች እውነተኛ ማንነት እንዲታወቅ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ቅባት መበርበር አለባት::

የእግዚአብሔር ቃል በገላትያ 5÷20 "ጣዖትን ማምለክ" የሥጋ ሥራ እንደሆነ ይነግረናል እንዲሁም አማኞች ጣዖትን ከማምለክ መጠንቀቅ እንዳለባቸው:-

"ልጆች ሆይ ራሳችሁን ከጣዖታት ጠብቁ::"(1ዮሐ5÷21) (የቀ.ት)

"እንግዲህ ወዳጆቼ ሆይ! ጣዖትን ከማምለክ ራቁ::"(1ቆሮ10÷14)

እዚህ ላይ መመልከት ያለብን ጣዖት አምላኪዎች እንዳይሆኑ የተነገረው ጌታ ኢየሱስን አምነው ደህንነት ላገኙ አማኞች ነው:: ጣዖት ማለት የተቀረፀ ምስል ብቻ አይደለም:: ማንኛውም ነገር እኛን ገዝቶ የያዘን

የምንበረከክለትና የምንሰግድለት ከሆነ ያ ነገር ጣዖታችን ነው:: ጌታ ኢየሱስ ለሁለት ጌቶች ማለትም ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም አለ:: (ሉቃ 16÷13) ጌታ በዚህ ክፍል ላይ ሲገልጽ እግዚአብሔር አንድ ጌታ ገንዘብ ደግሞ ሌላ ጌታ እንደሆነ አድርጎ ይነግረናል:: ገንዘብ ከተገዛንለት ከእግዚአብሔር ሊለይ የሚችል ጌታ ወይም ጣዖት ነው:: ሰዎች ከእግዚአብሔር ነገር ይልቅ ለገንዘብ ቅድሚያ የሚሰጡ ከሆነ ጣዖትን እያመለኩ ነው፤ ጣዖት ደግሞ ከሰይጣን ነው:: ሲሞን የእግዚአብሔርን ጸጋ በቁጥጥሩ ሥር ሊያደርግ የፈለገው በገንዘብ ኃይል ነበር:: ሲሞን ይህንን ሲል ከእግዚአብሔር ኃይል ይልቅ የገንዘብ ኃይል ይበልጣል ማለቱ ነበር:: ምክንያቱም አንድ ነገር በሌላ ነገር መገዛት ከቻለ ገዥው ከተገዥው እንደሚበልጥ ተገዥው ደግሞ ከገዥው እንደሚያንስ የታወቀ ነው:: ሲሞን ገንዘብን ከእግዚአብሔር ኃይል አስበልጦ በማየቱ ለእርሱ ገንዘብ ጣዖቱ ነበር ስለዚህ ሲሞን የእግዚአብሔርን ኃይል በገንዘብ ለመግዛት መፈለጉ በጣዖቱ ኃይል የእግዚአብሔርን መንፈስ በቁጥጥሬ ሥር አደርገዋለሁ ማለቱ ነበር:: ስለዚህ ገንዘብ ጣዖት እንዳይሆንብን በጣም መጠንቀቅ አለብን::

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንደ ሲሞን የእግዚአብሔርን ጸጋ በገንዘባቸው በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ይፈልጋሉ:: የተቀቡ አገልጋዮችን በገንዘብ ኃይል መቆጣጠር ማለት የጸጋ ስጦታን በገንዘብ መቆጣጠር ማለት ነው:: ለምሳሌ አንድ የቤተ ክርስቲያን እረኛ ከቤተ ክርስቲያን ስለሚከፈለው ብቻ በእረኝነት ቅባቱ በትክክል ከጌታ በተሰጠው ሥልጣን በሙሉ የአገልግሎት ድርሻው እንዳያገለግል የሚቆጣጠሩ አሉ:: ሲሞን ይህን በማድረጉ የመጣለት የመንፈስ ቅዱስ ደምጽ ከባድና አስፈሪ ነበር ይህም “ገንዘብህ ከአንተ ጋር ይጥፋ” የሚል ነው:: ደግሞም ይህንን እያወቁ ጥቅምና ክብራቸውን እየተመለከቱ ከጌታ የተቀበሉትን የአገልግሎት ሥልጣን በትክክል የማያስተላልፉ እረኞችና አገልጋዮች የጌታ ባሪያዎች ሳይሆኑ የሰዎችና የገንዘብ ባሪያዎች ስለሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂዎች ሊያደርጋቸው ይችላል:: ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችዋን በደንብ መያዝ ቢኖርባትም አንዳንድ አገልጋዮች ገንዘብ የአገልግሎታቸው ኃይል ይመስል ከቤተ ክርስቲያን የግድ ገንዘብ ካልተከፈላቸው ወይም የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆነው ካልሠሩ ጸጋቸውን ይዘው የሚቀመጡ አሉ:: እንደነዚህ ዓይነት አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ዓላማ ይልቅ ገንዘብን በማስቀደማቸውና የሲሞንም ዓይነት





አመለካከት ስላላቸው ቶሎ ብለው በጌታ ፊት በንስሐ እራሳቸውን ካላቀረቡ የያዙት ጸጋ ከእነርሱ ጋር ብዙ ጊዜ ላይቆይ ይችላል ::

እንደ ሲሞን የእግዚአብሔርን ዕቅድ በገንዘብ ኃይል በቁጥጥር ሥር ለማድረግ የምትፈልግ ቤተ ክርስቲያን ወይም የገንዘብ ጥቅም ስለሚገኝበት ብቻ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን አሳብ የማያስተላልፉ አገልጋዮች ወይም ገንዘብ ካላገኙበት አገልግሎታቸውን እንደሚገባ የማያገለግሉ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በተቀደሰ ስፍራ ቁጭ ብለው ጣዖትን የሚያመልኩና ለሁለት ጌቶች የሚገዙ ይሆናሉ ::

እንዲሁም ልባቸው በቅንነት ሳይሞላ በመራራ ቅንዓት ተሞልተውና የኃጢአት እሥረኛ ሆነው እውነተኛ የአገልግሎት ጥሪ ሳይኖራቸው እንደ ሲሞን ከሌሎች እውነተኛ አገልጋዮች ጋር እየተባበሩ ያሉ ብዙ አስመሳይ አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ቦታን የያዙበት ዘመን ነው:: እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በወንጌላዊ ቅባት÷ በእረኛና በአስተማሪ ቅባት ብዙም አይገኙም:: የቅባቱ መጠን እንደ ሐዋርያትና ነቢያት ስለማይሆን በቤተ ክርስቲያን ተመሳስሎ የገባውን ጥልቅና ረቂቅ የሆነ ሰዎች የታሰሩበትን የሰይጣንን ሥራ አይገልጡትም:: ነገር ግን ሐዋርያትና ነቢያት ባሉበት ቤተ ክርስቲያን የቅባቱ መጠን በጣም ከፍተኛ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን እየተበረበረች ትጸዳለች ቅርጽም ያሳጣት ነገር በዚህ ቅባት እየተበረበረ ይወገዳል:: የሰማርያን ቤተ ክርስቲያን ያጸዳ የሐዋርያት ቅባት ዛሬም ለእያንዳንዳችን ባለንበት ቤተ ክርስቲያን ያስፈልገናል:: ባለንበት ዘመን ማመን ያለብን አንድ ነገር ቢኖር የሐዋርያት ቅባት የጎደላት ቤተ ክርስቲያን ገና ተበርብራ ያልጸዳች መሆንዋን ነው::

ሐዋርያት እውነተኛውን እምነት (ዶክትሪን) የሚጠብቁ ናቸው:: በመጀመሪያው ዘመን ሐዋርያቶች ቤተ ክርስቲያን በሐሰተኛ አስተማሪዎች እንዳትበከል ከልዩ ልዩ እውነት ከሚመስል ውሸት ይጠብቋት ነበር:: ሰይጣንም በሲሞን በኩል ሊያደርግ የፈለገው ትልቅ ነገር ይህ ነበር:: ሲሞን እራሱን ለወንጌል እውነት አጋልጦ ከመስጠት ይልቅ ከፊሊጶስ ጋር የሚተባበር መስሎ ስውርና ረቂቅ በሆነው የሰይጣን አሠራር ወንጌልን በገንዘቡ ኃይል ማርኮ በውስጡ በተቀመጠው በመራራ ቅንዓትና በኃጢያተኝነት እስራት የሰማርያን ቤተ ክርስቲያን ለመበከል ነበር ፍላጎቱ:: ነገር ግን ሐዋርያት ጴጥሮስና ዮሐንስ ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያ በገቡ ጊዜ ረቂቅ የሰይጣን ዕቅድና አሳብ ተመታ::

ዛሬስ ለእኛ እውነተኛውን እምነት የሚጠብቁ ሐዋርያቶች ያስፈልጉናል ? ወይስ በድንግዝግዝ መጓዝን ? ስለዚህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን ቅባት ከጌታ የምትቀበል ስለሆነ እንደ ሲሞን የሃይማኖት መልክ ያለው ከአጋንንት የመጣ አመለካከትና ዶክትሪን ቦታ የለውም:: በትክክል በተቀቡና ለመቅደሱም ቅንዓት ያላቸው ሰዎች እንጂ አድራሻው በማይታወቅ ወኔና በኃጢያት ሰንሰለት ትብታብ ተይዘው በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚጨፍሩ ዋጋ የላቸውም:: ስለሆነም ሐዋርያት ያስፈልጉናል !!!

# ነቢያት

ስለ ነቢያት መጽሐፍ ቅዱሳችን በተለይም የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ብዙ ያስተምሩናል:: ስለ ነቢያት አገልግሎት ስናስብ በብሉይ ኪዳን ብቻ እግዚአብሔር የተጠቀመበት በአዲስ ኪዳን እምብዛም የማያስፈልግ ይመስለናል:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ እንዲኖራት ከሰጠው አገልግሎት ሁለተኛው ነው::

" እንዳንዶች ነቢያት . . . እንዲሆኑ ሰጠ:: " (ኤፌ 4÷11)

"...በመጀመሪያ ሐዋርያትን÷ ሁለተኛ ነቢያትን... ሾሞአል"
(1ቆሮ 12÷28)

ነቢያት ያለማቋረጥ የእግዚአብሔርን ድምፅ የሚሰሙበት ልዩ ጸጋ ያላቸው ግልፅና ትርጉም ያለውን ራእይ የሚያዩ የእግዚአብሔር አፍ በመባል የሚታወቁ ናቸው:: ስለ ነቢያት አገልግሎት ብዙ ማለት ቢቻልም ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋናው የነቢያት አገልግሎት ምንድነው የሚለውን እንመለከታለን::

ነቢያት አገልግሎታቸው <u>"ጥቅጥቅ ያለውን ጫካ በመግለጥ አርሶ ጥሩ መሬት አድርጎ ጥሩ ዘር ዘርቶበት የዘሩ ተጠቃሚ የሚሆንን ገበሬ ይመስላሉ"</u> ይህንንም የሚገልጽ በትንቢተ ኤርምያስ እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን :-





" የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ በሆድ ሳልሠራህ አውቄህለሁ ከማኅፀን ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ:: እኔም ወዮ ጌታ እግዚአብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም አልሁ:: እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ ወደምስድድህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና የማዝህንም ሁሉ ትናገራለህና ብላቴና ነኝ አትበል እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ ይላል እግዚአብሔር:: እግዚአብሔርም እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ እግዚአብሔርም እነሆ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ እነሆ ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፣ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፣ ትሠራና ትተክል ዘንድ፣ በአሕዛብና በመንግሥታት ዛሬ አድርጌሃለሁ አለኝ::"
(ኤር1÷4-10)(የቀ.ት)

ከላይ ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መሠረት ነቢያት:-

## *ሀ) በእግዚአብሔር የተጠሩ ናቸው*

*(ኤር 1÷5)*

ነቢያቶች በእግዚአብሔር የተጠሩ÷ የተለዩና የተቀቡ ናቸው :: ነቢያትን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቀብቶ ካልሰጠን በስተቀር እንደ ሌሎች አገልግሎቶች ወይም ስጦታዎች በዘፈቀደ የምናገለግለው አይደለም:: ለምሳሌ የወንጌላዊ ጥሪ ሳይኖራቸው ራሳቸውን ሾመው ወይም በሰው ተሹመው ወንጌላዊ በመባል በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ቆመው የሚያገለግሉ አሉ:: እንዲሁም የመሪነት ጥሪና ቅባት ሳይኖራቸው በሰው ተሹመው ወይም እራሳቸውን ሹመው የሚያገለግሉ ብዙ ናቸው:: እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በእግዚአብሔር ሳይቀቡና ጥሪ ሳይኖራቸው እየተመሳሰሉ ብዙ መቆየት ይችላሉ:: ነቢያትን ግን በሰው መሾም ከቶ የማይቻል ነው:: ራሳቸውንም ነቢይ ያደረጉ ካሉ ወዲያው በፍሬአቸው ይታወቃሉ::

እውነተኛ ነቢያት ግን እግዚአብሔር ቀብቶ የሚያስነሳቸው ስለሆነ ጥርት ባለ መንገድ የእግዚአብሔርን ድምፅ በቀላሉ የሚሰሙበት ጆሮ ያላቸው የሚያዩትን ራእይ እግዚአብሔር በቀላሉ የሚገልጥላቸው በእግዚአብሔር የተጠሩ ናቸው::

## *ለ) እግዚአብሔር የሚያዛቸውን የሚናገሩ ናቸው*

*(ኤር 1፥7)*

ነቢያት እግዚአብሔር የተናገራቸውን ብቻ የሚናገሩ ናቸው:: እግዚአብሔር ለተናገራቸው ነገር ወደ ኋላ የማያፈገፍጉ፥ ወደሚሰዳቸው ሁሉ የሚሄዱ፥ የሰውን ፊት አይተው የማይፈሩ፥ በአካባቢያቸው ያለውን ነገር በመመልከት እግዚአብሔር የተናገራቸውን የማይሸሽጉና፥ ከፊታቸው ያለውን መከራ፥ ስደት፥ ዱላን፥ ግዞትን፥ በመፍራት የእግዚአብሔርን ቃል የማያጥፉ፤ በእግዚአብሔር እጅ አፋቸው የተዳሰሰ፥ ከአፋቸውም የሚወጣ ቃል ኃይልን የተሞላ ሊመጣ ያለውን የሚተነብዩ እግዚአብሔር የሚያዛቸውን ብቻ የሚናገሩ ናቸው::

## *ሐ) የእግዚአብሔርን ቃል በኃይል የሚቀበሉ ናቸው*

*(ኤር 1፥10)*

ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል በኃይል የሚቀበሉ ናቸው ስንል ለየት ባለ መልኩ የእግዚአብሔር ቃል በነቢያት አፍ አለ ያም ቃል በታላቅ ኃይል የተሞላ ነው ማለታችን ነው:: ወንጌል ሰባኪ ወንጌልን እንደሚሰብክበት አስተማሪም እንደሚያስተምርበት የቅባት መጠን ሳይሆን በእነርሱ ውስጥ የሚተላለፈው የእግዚአብሔር ቃል ከቅባታቸው የተነሣ ወደ ሰዎች ሕይወት የሚገባው በታላቅ ኃይል ነው:: እዚህ ላይ መረዳት ያለብን የቅባት መጠን እንዳለ ነው:: ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ይለወጣል ማለት አይደለም ነገር ግን አንድ ወንጌላዊ ባለው ቅባት መጠን የሚያስተላልፈው የእግዚአብሔር ቃልና ነቢያት ባላቸው የቅባት መጠን የሚያስተላልፉት ቃል ከቅባቱ መጠን የተነሣ ኃይሉ ይለያያል::

ከዚህም የተነሣ በእነርሱ ውስጥ የሚተላለፈው የእግዚአብሔር አሳብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነቅል፥ የሚያፈርስ፥ የሚያጠፋና የሚገለብጥ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ወደ ፍፁምነት እንድትደርስ የነቢያት ቅባት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አለው::

ቤተ ክርስቲያንን ዛሬ ስንመለከታት ከላይ ጀምራ እስከ ታች ድረስ ብዙ የተበላሸና ቅርጽ የሌለው እግዚአብሔር ያልተከለው <u>መነቀል</u> ያለበት፤





እግዚአብሔር ያልገነባው <u>መፍረስ</u> ያለበት ብዙ ነገር አለ:: ስለዚህ የነቢያትን አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን እስካልተቀበለች ድረስ እውነተኛውን ተሐድሶ ማግኘት አትችልም::

ራሳቸውን በራሳቸው የተከሉና እንደ ፓርላማ ምርጫ በቅስቀሳ የተቀመጡ ቤተ ክርስቲያንን በመምራት ላይ ያሉ ብዙ ናቸው:: በእግዚአብሔር ያልተቀቡና ጩኸት ብቻ ይዘው የተቀቡ ለመምሰል በሽፍንፍን የውሸት መገለጦች በሰዎች እልልታና ጭብጨባ ታጅበው በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚጨፍሩ በእግዚአብሔር ያልተተከሉ ብዙ ናቸው:: ደግሞም እግዚአብሔር ስለ ታላቅ ምህረቱ ቢታገስም ፃድቅ ፈራጅ ስለሆነ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን ይቀጣል:: "በዚያም ቀን በመድረኩ ላይ የሚዘልሉትን የጌታቸውንም ቤት ዓመፃንና ሽንገላን የሚሞሉትን እቀጣለሁ":: ( ሶፎ 1፥9)(የቀ.ት)

እውነተኛ ጥሩ ዘር የሚዘራበት መሬት ከመገኘቱ በፊት በመሬቱ ላይ ያለው የማይጠቅመውና ፍሬ የሌለው ዛፍ ሁሉ መነቀል አለበት:: ምክንያቱም አብ ያልተከለው ዛፍ ሁሉ ይነቀላል:: (ማቴ 15፥13) ይህ ብቻ አይደለም በእግዚአብሔር ሳይሾሙ የተሾሙ እግዚአብሔር ባልሰጣቸው መገለጥ ከእርሱ ቃል ውጭ በሆነ አንዳንዱም ከአጋንንት በመጣ የአሠራር ሥርዓት (ዶክትሪን) የገነቡት መፍረስ ብቻ ሳይሆን መፈራረስ ያለበት ብዙ ነገር አለ:: እግዚአብሔር መንፈሳዊ ሥርዓትንና አገዛዝን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቀምጧል:: እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሳይሆን በብዙ አብያተ ክርስቲያናት የሚሠራው ሰው ባስቀመጠው መንፈሳዊ አገዛዝና ሥርዓት ነው:: የነቢያት አገልግሎት መገንባት ያለበት ቢሆንም እንኳን እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ነገር በቦታው ለማቆም ከሰውና ከአጋንንት የሆነውን ሁሉ የማፈራረስና የመንቀል ቅባት በላያቸው ላይ አለ:: <u>ስለዚህ ተሐድሶ ስንል መገንባት ብቻ ሳይሆን የማይረባውን ነገር ማፈራረስም ጭምር ነው::</u>

እንዲሁም <u>"ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ "</u> (ኤር1፥10) ሌላው የነቢያት ቅባት ማጥፋት ነው:: መንቀልና የተገነባውን የጠላትን አሠራር ማፍረስ ብቻ ሳይሆን የተነቀለውንና የፈረሰውን ፍርስራሽ ምንም ሳያስቀር ርዝራዥ እንዳይገኝ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠራርጎ የሚያጠፋ ቅባት በላያቸው ላይ አለ::

በተጨማሪም የነቢያት ቅባት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መገለባበጥን ያመጣል ምክንያቱም የነቢያት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ እንድትይዝ ስለሚያደርግ ብዙ አገልጋዮች እንደ ጳውሎስና በርናባስ እውነተኛ የአገልግሎት ቦታቸውን እንዲይዙ ብዙ የሚገለባበጥ ነገር ይኖራል:: ከዚህ የተነሣ አማኞች በተሰጣቸው ጸጋ እውነተኛ ቦታቸውን እንዲይዙ በማድረግ የእግዚአብሔርን ቤት ቅርጽ እንዲይዝ ያደርጋሉ:: መንፈስ ቅዱስ በነቢያት አማካኝነት "እኔ ለመረጥኳቸው ሥራ በርናባስና ሳኦልን ለዩልኝ አለ::" (ሐ.ሥ 13÷2) በነቢያት አገልግሎት ይህ የሚሆነው ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽና እንዲሁም እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋና በጠራቸውም ቦታ በመሆን ምእመኑን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው:: (ኤፌ4÷11-12)

በመጨረሻም የነቢያት አገልግሎት "ትሠራና ትተክል ዘንድ" (ኤር 1÷10) እንግዲህ በሐዋርያትና በነቢያት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን እንደተመሠረተች ሥራው የሚፈፀመው የሐዋርያትና የነቢያት ቅባት በቤተ ክርስቲያን በኃይል መንቀሳቀስ ሲጀመር ነው:: የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ተመሳሳይ ነገር የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን:: እርሱ የነቢያት ቅባት በላዩ ላይ ስለነበረ የእግዚአብሔር ክብር ከመገለጡ በፊት መንገዱን አስተካከለ÷ ሸለቆውን ሞላ÷ ጠማማውን አቀና÷ ተራራውን ዝቅ አደረገ÷ ጠንካራውን መንገድ ለስላሳ አድርጎ ካስተካከለ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ከእርሱ አገልግሎት በመከተል በክብሩ ተገለጠ:: ዛሬም በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ከነሙሉ ክብሩ እንዲገለጥ መንገድን የሚጠርጉ ነቢያት ያስፈልጉናል:: (ሉቃ3÷6) (ኢሳ40÷3-5) በመንቀልና በማፍረስ÷ በመገልበጥና በማጥፋት÷ በመሥራትና በመትከል የነቢያት ቅባት ቤተ ክርስቲያንን ቅርጽ እንዲኖራትና በሁለት እግርዋ እንድትቆም ያደርጋታል:: ስለዚህ ነቢይን ተቀብላ በአገልግሎቱ (በቅባቱ) የተጠቀመች ቤተ ክርስቲያን የነቢይን ዋጋ ታገኛለች:: ዋጋውም ቅርጽ ያላት የምትማርክ÷ የተዋበች÷ የደመቀች÷ ለጌታዋ መምጣት የተዘጋጀች ቤተ ክርስቲያን መሆን ነው::





# ወንጌል ሰባኪዎች (ወንጌላውያን)

እግዚአብሔር ብዙ የተቀቡ ወንጌላውያንን እንዲያስነሳና ወንጌልም ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰበክ የብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ፍላጎት ነው:: በመጨረሻው ዘመን ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ መሰበክ አለበትና:: ነገር ግን በአሁኑ ዘመን ወንጌላዊ ተብሎ መጠራት ጌታ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ለሰዎች ያካፈለው ከጌታ የተገኘ ቅባት ያለበት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ እንዲኖራትና ወደ ሙላት እንድትገባ የሚያደርግ ሳይሆን በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍት የሥራ ቦታና ከንቱ ሹመት የሆነበት ዘመን ነው::

ወንጌላዊ በገጠርና በከተማ ወንጌልን ለመስበክ የተጠራ ብቻ ሳይሆን ከጌታ በተቀበለው የወንጌላዊ ቅባት ምእመናንን ሁሉ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት የተዘጋጁ እንዲሆኑ ከቅባቱ የሚያካፍል ነው:: እውነተኛ ወንጌላዊ ባለበት ቤተ ክርስቲያን ምእመኑ በሄዱበት ስፍራ ሁሉ ወንጌልን ለሌሎች በታላቅ ፍላጎት የሚሰብኩ ይሆናሉ:: ይህንንም የምናየው በጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ነው::

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አራት ላይ ኢየሱስ በሰማርያ ሊያልፍ "ግድ" ሆነበት የሚል ቃል እናገኛለን ኢየሱስ በሰማርያ ሊያልፍ ግድ ሆነበት የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም በጣም ጥልቅና ከፍተኛ የሆነ ውስጣዊ ግፊት÷ ፍላጎትና ውስጣዊ ርሀብ የሚል ነው:: ኢየሱስን በዚያ እንዲያልፍ ያስገደደው አንድ ኃይል ነበር ይህም ኃይል በሉቃስ 4÷19 ላይ " የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል" እንዳለው በጌታ ላይ የነበረው የወንጌላዊ ቅባት በሰማርያ ያልፍ ዘንድ ግድ አለው:: ምክንያቱም በሰማርያ መዳን የሚገባት ነፍስ ነበረችና (ዮሐ 4÷7) እውነተኛ ጥሪ ያላቸው ወንጌላውያን ከቅባቱ የተነሣ በሰማርያ ማለፍ ግድ የሚላቸው ይሆናሉ::

እንደዚሁም እውነተኛ ወንጌላውያን የሰዎችን እንሥራ የሚያስጥሉ ናቸው:: አንዳንድ ወንጌላውያን በመድረክ ላይ ወዲያና ወዲህ እየተንጎራደዱና እየደጋገሙ:-

"ኧ.... ሬ ... ለመሆ.ኑ ! ... ምን ይሆን ችግራችሁ ... ? !!!

ኧረ ለመሆኑ .... ችግራችሁ ምንድን.... ይሆን ? !!!
የኔ እህት ኧ ... ረ .. ለመሆኑ ...ችግርሽ ምን ይሆን ? !!!
አባቶቼ ..ና.. እናቶቼ ... ችግራችሁ ምን ይሆን ? !!!!
ኧረ ችግራችሁ ምን ...ኧ ..ረ ምን ይሆንን ? !!!!

በማለት ምእመኑ ተነስቶ መልስ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ይመስላሉ:: እውነተኛ ወንጌላዊ የሚያገለግለውን ሕዝብ ችግር የማይፈታ ጥያቄ አቅራቢ አይደለም:: ነፍሰንና ቅልጥምን ሁሉ አልፎ በሚገባው በእግዚአብሔር ቃል የሰዎችን እንቆቅልሽና ጥያቄ የተቸገሩበትንም ነገር እየነካ እንሥራቸውን የሚያስጥል ነው:: ይህ ብቻ አይደለም እንሥራቸውን የጣሉትንም እነዚያን ሰዎች የወንጌል ባለ አደራ ሰባኪዎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው:: ጌታ ለሰማርያዋ ሴት የምሥራቹን ወንጌል ሰብኮላት ችግርዋን በሕያው ቃሉ ከነገራትና እንሥራዋን ከጣለች በኃላ ወደ ከተማ ሄዳ ወንጌልን ሰበከች (ዮሐ4÷28-30) ያለ ቅባቱ ቀንበር አይሰበርምና ከጌታ በተካፈለችው የወንጌል ቅባት በሰበከችው ስብከት በሰማርያ ከተማ ብዙዎቹ አመኑ ብዙዎችንም ወደ ጌታ አመጣች::

እንግዲህ እውነተኛ ወንጌላዊያን ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን የተቀበሉትን ቅባት በማካፈል ምእመናን ወንጌል ሰባኪያን እንዲሆኑ የሚያደርግ ቅባት ከጌታ የተቀበሉ ናቸው::

# እረኞች

እረኛ ማለት ጠባቂ÷ ተንከባካቢና መሪ ማለት ነው:: በአዲስ ኪዳን ስለ ጌታ ኢየሱስ እረኝነት በብዙ ቦታ ተጠቅሶ እናያለን:: በዘላለም ኪዳን ደም የበጎች ትልቅ እረኛ ነውና:: ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመስል ታላቅ እረኛ ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ አሳልፎ የሰጠ ማንም የለም:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለው የእረኝነት አገልግሎት ግን በኤፌሶን4÷11 ላይ "... እንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች...እንዲሆኑ ሰጠ" የሚል ቃል እናገኛለን:: በአዲስ ኪዳን በብዙ ቦታ እረኛ ተብሎ ስላልተጠቀሰ እረኛ አያስፈልግም ማለት አይደለም ወይም እረኝነት እንደ ቀላል ስጦታ በፍጹም መታየት የለበትም:: ምክንያቱም መንጋ ያለ እረኛ እረኛም ያለ መንጋ ዋጋ የለውም:: ጌታ ኢየሱስ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ የእረኝነት አገልግሎት ለቤተ





ክርስቲያን ሰጥቶአል:: ይህም አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን ወደ ፍፁም ሙላት ከሚያስገብዋት የአገልግሎት ስጦታዎች አንዱ ነው:: የእረኝነት አገልግሎት የጎደላት ቤተ ክርስቲያን ወዴት እንደምትሄድ አታውቅም ምክንያቱም የሚመራት የለምና:: ከዚህ በታች ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወስደን እረኛ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ስድስት ዋና ዋና ክፍሎችን እንመለከታለን::

> " ሙሴም እንዲህ ሲል ፀለየ የሕይወት ሁሉ ምንጭ የሆንህ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ሕዝቡን መምራትና በጦር ሜዳም ማዘዝ የሚችል አንድ ሰው ምረጥ:: በዚህ ዓይነት ያንተ ጉባኤ እረኛ እንደሌለው በግ ከመሆን ይድናል:: እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው በሁሉ ነገር ብቃት የሚሰጥ መንፈስ ያለውን የነዌን ልጅ ኢያሱን ውሰድና እጆችህን በራሱ ላይ ጫን:: በካህኑ በአልዓዛርና በመላው ማኅበር ፊት እንዲቆም አድርገው በእነርሱም ሁሉ ፊት የአንተ ተተኪ መሆኑን አስታውቅ:: መላው የእስራኤል ማኅበር እርሱን ይታዘዙ ዘንድ የሥልጣንህ ተካፋይ አድርገው:: ካህኑ አልዓዛር ኡሪምና ቱሚም በተባሉ እቃዎች አማካኝነት ፈቃዴን የሚያውቅ ስለሆነ ኢያሱ በአልዓዛር ይደገፋል:: በዚህ ዓይነት አልዓዛር ኢያሱንና መላውን የእስራኤልን ማኅበር በተግባር አፈጻጸማቸው ሁሉ ይመራቸዋል":: ( ዘኁ 27÷15-21)

## )እግዚአብሔር ለአንድ ማኅበር አንድ እረኛ ይፈልጋል
(ዘኁ 27÷16-17)

እግዚአብሔር የቃል ኪዳን አምላክ ስለሆነ ከሰው ልጆች ጋር በቃል ኪዳን መተሳሰር ይፈልጋል:: በተለይም የመረጠውን ሕዝቡን የሚመራለት የዘላለሙን አሳብ በመረዳት ሕዝቡን የሚያሻግርለት እርሱ ወደ አቀደውና ወዳለመው ግብ እንዲያደርስለት ከእነርሱም ጋር በቃል ኪዳን ለመተሳሰር ሰዎችን ይፈልጋል:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ሲፈጥር ብቻ ነው ሰዎችን ያልተጠቀመው:: ከዚያ በኋላ ግን በምድር ላይ ላለው መለኮታዊ ሥራ የግድ እግዚአብሔር ሰዎችን ይፈልጋል:: እግዚአብሔር ሰዎችን የሚፈልገው ለራሳቸው ጥቅምና ክብር እንዲኖሩ

ሳይሆን የእርሱን አሳብ እንዲያገለግሉለት ሰማያዊን ራእይ በዚህ ምድር እንዲገልፁለት ነው:: ከዚህም የተነሣ በየዘመናቱ ሕዝቡን እንዲመሩለት በእርሱና በሕዝቡ መካከል የሚቆሙ ሰዎችን ይፈልጋል::

ሕዝቡን ከግብጽ ከባርነት ቤት በድንቅና በተአምራት አስለቅቆ እየመራ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው ምድር እንዲያደርስ የሕዝቡ ታላቅ መሪ አድርጎ ሙሴን ቢያስነሳውም በዘኁልቁ 27÷12-14 ሕዝቡ በትእዛዙ ላይ ባመፁ ጊዜ የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ኃይል በሕዝቡ ፊት ለመግለፅ እምቢ ባለ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ ተስፋይቱ ምድር አትገባም ትሞታለህ አለው:: ከሞት የከፋ ምንም ነገር እንደሌለ ሙሴ ቢረዳም እንኳን የራሱ ሞት አልታየውም ነበር:: ከራሱ ሞት ይልቅ የታየው ከግብፅ ከባርነት ቤት እየመራ ያወጣውን ሕዝብ ያለ እረኛ የትም መንቀሳቀስና ምንም ማድረግ ስለማይችል በምድረ በዳ ወድቆ የሚቀር ሕዝብ መሆኑን ስለተረዳ እግዚአብሔር ትሞታለህ ሲለው ሙሴ ግን እረኛ ቀብቶ እንዲያስነሳላቸው ለመነ::

ሙሴ ይህንን ጸሎት በጸለየበት ወቅት እርሱን በአገልግሎቱ ይረዱት ዘንድ እግዚአብሔር ከሙሴ መንፈስ ያካፈላቸው ሰባ (70) ሽማግሌዎች ነበሩ:: ነገር ግን ሙሴ ሰባው ሽማግሌዎች እረኞች ሆነው ሕዝቡን መምራት እንደማይችሉ ምናልባትም በሰባ ቦታ ይዘውት እንደሚሄዱ ሰላወቀ ሲጸልይ:-

> "ሕዝቡን መምራትና በጦር ሜዳም ማዘዝ የሚችል
> <u>አንድ ሰው ምረጥ</u>..." አለ:: (ዘኁ 27÷17)

ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲመሩለት በጦር ሜዳም ትእዛዝ እንዲሰጡለት የሕዝቡ እረኛ አድርጎ ቃል ኪዳን የሚገባው <u>ከአንድ ሰው ጋር ነውና</u>:: እግዚአብሔር በየዘመናቱ በቃል ኪዳን በእርሱና በሕዝቡ መካከል የሚቆሙትን ሲያስነሳ በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከሁለት ወይም ከዛ በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር በአንድ ቦታና ጊዜ በአንድነት ቃል ኪዳን ሲገባ አናገኝም:: እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ በአብርሃም በኩል ሲመርጥ በመረጠው ሕዝብና በእርሱ መካከል በቃል ኪዳን የሚቆም በየዘመኑ አንዳንድ ሰው ያስነሳላቸው ነበር:: ከእነዚህም ውስጥ አብርሃም --> ይስሐቅ --> ያዕቆብ --> ዮሴፍ --> ሙሴ --> ኢያሱ:: ከዚያም ወደ መሳፍንት ዘመን ስንገባ የዘመኑን የእግዚአብሔርን ዓላማ ይዘው ሕዝቡን ከጠላት የሚያድኑትን መሳፍንት ሲያስነሳላቸው በየዘመኑ አንዳንድ ሰዎችን





ይቀባላቸው ነበር:: ከእነዚህም ውስጥ ሥራቸው ጎልቶ የሚታየው ጌዲዎንና ሳምሶን ይገኙበታል:: ንጉሥንም እንኳን ቀብቶ የሕዝብ መሪ አድርጎ ሲያስነሳላቸው አንዳንድ ሰዎችን ነበር የሚያነግሥላቸው ሳኦል÷ ዳዊት÷ ሰለሞንን እንደ ምሳሌነት ልንጠቀምባቸው እንችላለን::

አሁን ባለንበትም ዘመን ሕዝቡን እንዲመሩለት ለእርሱ ክብር እንዲቆሙ ራሳቸውን ሳይሆን ክርስቶስን የሚሸቱ ሰማያዊውን ራእይ በዚህ ምድር የሚገልጡ ለአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንድ እረኛ እግዚአብሔር ይፈልጋል:: ይህም ማለት ምክትል እረኞችና ሽማግሌዎች አያስፈልጉም ማለት አይደለም:: ነገር ግን ሙሴ በሰባው ሽማግሌዎች እንዲሁም የቅርብ ረዳቱ በሆነው በኢያሱ እና በእግዚአብሔር መካከል የሚቆም ነበር:: በሌላው አገላለፅ ሰባው ሽማግሌዎችና ኢያሱ ከሙሴ ቅባትና ሥልጣን ሥር ነበሩ:: ከሙሴ እኩል ለመሆን ምኞቱም አልነበራቸውም:: ምክንያቱም ሙሴን ለመርዳት ከሙሴ ቅባት የተካፈሉ መሆናቸውን ያውቁ ነበርና:: ስለዚህ ለአንድ ጉባኤ ወይም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን መምራትና በጦር ሜዳም ማዘዝ የሚችል አንድ ሰው እግዚአብሔር ይፈልጋል:: ሙሴ ሲጸልይ ይህን <u>አንድ ሰው</u> ከሰጠኸን "የአንተ ጉባኤ እረኛ እንደሌለው በግ ከመሆን ይድናል" አለ:: (ዘኁ 27÷17) የሚያስፈልገው እግዚአብሔር የቀባው አንድ ሰው ብቻ ነው:: ይህ አንድ ሰው እራሱ ሊከብርና ሊገን የሁሉም የበላይ ሆኖ እንዲታይ ሳይሆን እርሱ የሁሉም ታናሽ ሆኖ የእግዚአብሔርን በረከት ወደ ሕዝቡ የሚያስተላልፍ አሸንዳ ሊሆን እግዚአብሔር <u>አንድ ሰው</u> ይፈልጋል::

## ለ) በሁሉ ነገር ብቃት የሚሰጥ መንፈስ ያለው ነው

> "እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው <u>በሁሉ ነገር ብቃት የሚሰጥ መንፈስ</u> ያለውን የነዌን ልጅ ኢያሱን ውሰድና እጆችህን በራሱ ላይ ጫን" (ዘኁ 27÷18)

እዚህ ጥቅስ መጀመሪያ ላይ የእግዚአብሔር ቃል በሁሉ ነገር ብቃት ያለው አይደለም የሚለው ምክንያቱም ማንም በእራሱ ኃይልና ብቃት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊመራ አይችልም:: የእግዚአብሔር ቃል የሚለው <u>"ብቃት የሚሰጥ መንፈስ ያለበት"</u> እረኛም ሆነ በእግዚአብሔር ቤት የሚያገለግል ሰው ሁሉ ብቃት የሚያገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ነው:: በቀደመው ትርጉም <u>" መንፈስ ያለበት ሰው "</u> ይላል:: ስለዚህ ኢያሱ

እግዚአብሔር የመረጠውን ሕዝብ ለመምራት የሚያስፈልገውን የእግዚአብሔርን መንፈስ አግኝቶአል ከዚህም መንፈስ ብቃትን ሁሉ አግኝቷል:: አንድ እረኛ በኃይልና በብርታቱ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ብቃትን ማግኘት አለበት:: እረኛ ብቃትን ለማግኘት ምን ማድረግ አለበት ? ለሚለው ጥያቄ ብዙ መልስ ሊኖረን ይችላል:: በዚህ ጽሁፍ ግን የምናየው ያዕቆብ እንዴት ብቃት ያለው እረኛ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ቃል ከዚህ በታች እንመለከታለን:: በተለይ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ላይ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን እረኞች የያዕቆብን አገልግሎት ተምሳሌነት መውሰድና መመልከት አለባቸው::

## *እረኛ ብቃትን ለማግኘት ከቤርሳቤህ ወደ ካራን መውጣት አለበት*

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ያዕቆብ ሲነግረን " በቤት መዋል የሚወድ ጭምት ሰው ነበር " ( ዘፍ 25÷27) ይለናል:: ከዚህ የተነሣ ከርብቃ ጋር በደንብ የጠበቀ መቀራረብ ነበራቸው፤ ርብቃም ትወደውም ትመክረውም ነበር፤ ያዕቆብም የርብቃን ምክር በሥራ ላይ ያውል ነበር::ይህን በማስመልከት በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ " ነገር ግን ርብቃ የኤሳውን ዕቅድ ስለሰማች ያዕቆብን ጠርታ እንዲህ አለችው አድምጠኝ ወንድምህ ኤሳው አንተን በመግደል ሊበቀልህ አስቦአል" (ዘፍ 27÷42) በማለት የኤሳውን የማጥፋት ዕቅድ ለያዕቆብ ስትገልጽለት እናያለን::

ያዕቆብ ገና በእናቱ ማኅፀን እያለ የእግዚአብሔር ዕቅድ በሕይወቱ እንደሚፈፀም የተነገረለት ቢሆንም እንኳን የእግዚአብሔር ዕቅድ በሕይወቱ እንዲፈፀም አንድ ነገር ማድረግ ነበረበት ያም የግድ ቤርሳቤህን ለቆ መውጣት ነበረበት:: ምክንያቱም በቤርሳቤህ ኤሳው በያዕቆብ ሕይወት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማጥፋት ሌላ ዕቅድ አውጥቶ ነበርና:: ቤርሳቤህ የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚያጠፋ የኤሳው ዕቅድ ያለበት ቦታ ነው፤ ቤርሳቤህ ጨለማና ፍርሃት ያለበት÷ ምንም ራእይ የሌለበት÷ ከኤሳው የተነሣ የሥጋት ኑሮ የሚኖርበት÷ ነፃነት የሌለበት ስፍራ ነው:: ብዙ እረኞች በቤርሳቤህ ስለሚኖሩ በሕይወታቸው ያለው የእግዚአብሔር ዕቅድ በኤሳው መንፈስ የተመታ ነው:: ያዕቆብ በቤርሳቤህ ሲኖር ህልምና ራእይ የሌለው÷ ማድረግና መሆን ያለበትን የማያውቅ እንደነበረ ሁሉ አንድ የቤተ ክርስቲያን እረኛም በቤርሳቤህ መሆኑን





የሚያውቀው ምንም ራእይና ህልም የለውም፤ እውነተኛ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ለበጎቹ አይመግብም፤ በጎቹን የሚመራው ከእግዚአብሔር በተቀበለው ምሪት ሳይሆን በኮሚቴ ጭቅጭቅ በተጨመቀ ውሳኔ ነው:: በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል የቆመ ዋና ተጠሪና ተጠያቂ መሆኑን አያውቅም:: እውቀት ቢኖረውም እንኳን እግዚአብሔር ራእይን ሰጥቶኛል ይህም ራእይ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መፈፀም አለበት ብሎ ራእዩን ለማስፈፀም ዋጋን ከፍሎ አይነሳም:: ከሰማይ የተሰጠውን ራእይ በሰዎች ለማስገምገም ጊዜን ይጠብቃል:: ቤተ ክርስቲያን ወደ ምን ዓይነት ክብር እየገሰገሰች እንደሆነና እግዚአብሔር በዘመናችን ምን እያደረገ እንዳለ እንኳን አያውቅም:: እረኛ ማድረግ የሚገባውን እግዚአብሔር ለራሱ የሰጠውን መንፈሳዊ ሥልጣን አይጠቀምም::እንደነዚህ ዓይነት እረኞች የእግዚአብሔርን እውነተኛ ዕቅድ ወደ ቤተ ክርስቲያን አያስተላልፉም:: ምክንያቱም በውስጣቸው ባለው የእግዚአብሔር ዕቅድ ላይ በጠላትነት በሚነሣው በኤሳው የተጠቁ ናቸው::

በቤርሳቤህ ያለ እረኛ በኤሳው የተማረከ በፍርሃት የተያዘ ነው:: ሳኦል ለምን ዐማሌቅን ወደተቀደሰ ስፍራ አስገባህ ተብሎ ሲጠየቅ ይህን ያደረኩት " ወታደሮቼን <u>በመፍራት</u> እነርሱ የፈለጉትን ሁሉ አደረግሁ"አለ:: (1ሳሙ 15÷24) ሳኦል በመጀመሪያ የዐማሌቅ የሰቡ ሠንጋዎች ማርከውት ስለነበር ከዚህ የተነሣ የወታደሮች ፍርሃት ወደ ውስጡ ገባ:: እነርሱንም በመፍራት እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማገልገል አልቻለም:: እንዲሁም የዐማሌቅ መንፈስ ባለበት በቤርሳቤህ የሚኖሩ እረኞች ሰውን በመፍራት የእግዚአብሔርን ዕቅድ ትተው ዐማሌቅ ባወጣው ዕቅድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ነገር ሲሆን ዝም ብለው የሚያዩ ናቸው::

የያዕቆብ አባት <u>ይስሐቅ</u> ከዚህ ምድር የመሄጃው ጊዜ ሲደርስ የመጨረሻውን በረከቱን ነበር በልጁ በያዕቆብ ላይ ያፈሰሰው "... ከመሞቴ በፊት <u>የመጨረሻ ምርቃቴን</u> እሰጥሃለሁ":: (ዘፍ 27÷4) ከዚህ የተነሣ እናቱ ርብቃ ወደ ካራን መሄድ እንዳለበት የመከረችውን ምክር ተቀብሎ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን እንደሄደ እንዲሁም እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ ያለውን የእራሱን ሥራ ጨርሶ ከዚህ ምድር ከመለየቱ በፊት እንደ ይስሐቅ በልጆቹ ላይ የመጨረሻውን በረከት ማፍሰስ ይፈልጋል:: ነገር ግን በረከቱን ተቀብለን በቤርሳቤህ መቀመጥ ስለማይቻል ያዕቆብ ወደ በረከቱ ሙላት ፍፃሜ እንዲደርስ የርብቃን አሳብ ተቀብሎ ወደ ካራን እንደሄደ እንዲሁም

በዘመናችን ያሉ እረኞች የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ በመስማት ሙላት ወደሚገኝበት ወደ ካራን መውጣት አለባቸው:: ስለሆነም :-

" ያዕቆብ ቤርሳቤህን ትቶ ወደ ካራን ለመሄድ ተነሣ "
(ዘፍ 28÷10)

ያዕቆብ ወደ ካራን ለመሄድ ቁርጥ ውሳኔ ባደረገ ጊዜ በመጀመሪያ የተገለጠለት ነገር ቢኖር በቤርሳቤህ አይቶት የማያውቀውን :-

1. እውነተኛ የእግዚአብሔር መገኘት ከሌለበት ስፍራ
   ---> እግዚአብሔር ራሱን ተገልጦ አየው::
2. በነገር ሁሉ ብቃትን እንዲያገኝ
   ---> የሰማይ በሮች ተከፈቱለት::
3. ዓላማ ከሌለው ሕይወት
   ---> እግዚአብሔር በሕይወቱ ያለውን ዓላማ ገለጠለት (ራእይን ተቀበለ) ::
4. የእግዚአብሔር በረከት ከሌለበት ስፍራ ወጥቶ
   ---> ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለልጅ ልጅ የሚተርፍን በረከት እንደተቀበለ በዘፍጥረት 28÷10-19 ይነግረናል::

ከዚህ በኋላ በዘፍጥረት ምዕራፍ 29 መጀመሪያ ላይ እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን "ያዕቆብ ጉዞውን ቀጥሎ በስተ ምሥራቅ ወዳለው አገር ደረሰ" (ዘፍ 29÷1) እዚህ ላይ ያዕቆብ ወደ ካራን ለመሄድ በጉዞ ላይ እንዳለ እግዚአብሔር በልዩ መንገድ ተገናኝቶ ብዙ ነገር ከገለፀለት በኋላ ተነስቶ ጉዞውን ቀጠለ :: የእግዚአብሔር ዓላማ እረኞች ካራን እንዲደርሱ እንጂ በመንገድ እንዲቀሩ አይደለም:: ያዕቆብ ህልምን ቢያይ÷ እግዚአብሔር ቢገለጥለት÷ ተስፋን ቢቀበል÷ ራእይን ቢያገኝም በዚህ ነገር ረክቶ አልተኩራራም ምክንያቱም እናቱ ርብቃ ካራን እንዲደርስ ነውና የነገረችው:: ብዙ እረኞች እግዚአብሔር የገለጠላቸውን ነገር ይዘው በተገለጠላቸው ቦታ ይዘውት ይቆማሉ ጉዞአቸውን አይቀጥሉም፤ወደ አዲስ መገለጥና ራእያቸውም ወደሚፈፀምበት ሙላት ለመድረስ የእግዚአብሔርን ሙሉ ፈቃድ ለማወቅ አይጓዙም:: የያዙትንም ሕዝብ እነርሱ ለዘመናት በቆሙበት ስፍራ ያለውን ነገር ብቻ ነው የሚመግቡት:: ነገር ግን እውነተኛ የበጎች እረኛ ሁል ጊዜ አዲስ ነገር ያለው ነው:: ጌታ ኢየሱስ ሁል ጊዜ አዲስ ነገር እየተቀበለ ወደ ሕዝቡ ያደርስ ነበር ከአፉም በሚወጣው





በአዳዲስ ነገር ይደነቁ ነበር:: እውነተኛ እረኞች አዲስ ነገርን ለማግኘት ሁል ጊዜ ጉዞአቸውን የሚቀጥሉ መሆን አለባቸው:: ያዕቆብ ጉዞውን በመቀጠሉ አንድ ታላቅ ነገርን አየ::

"ያዕቆብ ጉዞውን ቀጥሎ በስተ ምሥራቅ ወዳለው አገር ደረሰ እዚያም በሜዳ ላይ አንድ የውሃ ጉድጓድ አየ በሦስት የተከፈሉ የበግ መንጋዎች በጉድጓዱ ዙሪያ ነበሩ መንጋዎቹ ውሃ የሚጠጡት ከዚህ ጉድጓድ ነበር::" (ዘፍ 29÷1-2)

ከላይ ባለው ጥቅስ ያዕቆብ ያየው ነገር የመጨረሻዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ወደ ሙላቱ የደረሰችውን ቤተ ክርስቲያንን ነበር:: ያዕቆብ በመጀመሪያ አየ (ተመለከተ):: እረኞች ወደ ካራን በመሄድ ጉዞአቸውን ሲቀጥሉ ድንገት እግዚአብሔር የሚገልጥላቸው ነገር ቢኖር ሙላት ያላትና ነውር እድፈትና የፊት መጨማደድ የሌለባት በካራን ያለችዋን ቤተ ክርስቲያን ምን እንደምትመስል ያሳያቸዋል:: ያዕቆብ በመጀመሪያ የተመለከተው " በሜዳ ላይ አንድ የውሃ ጉድጓድ አየ" ይህም ጉድጓድ የሕይወት ውሃ ምንጭ የሆነውን ኢየሱስን የሚያመለክት ነበር:: በቤርሳቤህ የምናየው ነገር ጨለማ÷ ምድረበዳ÷ ሰላም የሌለበት ስፍራ ኤሳው የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለመምታት አሳቡን የዘረጋበት ስፍራ ነው:: በካራን ደግሞ የኤሳው ዕቅድ የተመታበት÷ አንድ የውሃ ጉድጓድ ብቻ የምናይበት ማንም ያልነገሠበት አንዱ የውሃ ጉድጓድ (ኢየሱስ) ብቻ ከፍ ከፍ ብሎ የሚታይበት ጥማት የሌለበት እርካታ የሞላበት ስፍራ ነው::

በማስከተል ያዕቆብ በሦስት የተከፈሉ መንጋዎች ከጉድጓዱ ዙሪያ ተመለከተ:: ጌታ ኢየሱስ የሚፈልጋት ቤተ ክርስቲያን ምንእንደሆነችና እውነተኛ እረኛ ምን ዓይነት እንደሆነ ለጴጥሮስ እንደሚገባው አድርጎ በዮሐንስ ወንጌል ሲገልፅለት :-

"...የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ! እነዚህ ከሚወዱኝ ይበልጥ ትወድደኛለህን ? አለው:: እርሱም አዎ ጌታዬ ሆይ እኔ እንደምወድድህ አንተ ታውቃለህ ሲል መለሰለት:: ኢየሱስም ግልገሎቼን መግብ አለው:: ሁለተኛ ጊዜም የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ! ትወድደኛለህን? አለው:: እርሱም አዎ ጌታዬ ሆይ! እንድምወድድህ ታውቃለህ አለው:: ኢየሱስም ጥቦቶቼን ጠብቅ አለው ሦስተኛ ጊዜ የዮና ልጅ ስምኦን

ሆይ! ትወድደኛለህን? አለው ሦስተኛ ጊዜ ትወድደኛለህን ስላለው ጴጥሮስ አዘነና "ጌታ ሆይ! አንተ ሁሉን ታውቃለህ፥ እኔ እንደምወድህም ታውቃለህ" አለው:: ኢየሱስም እንዲህ አለው በጎቼን አሠማራ፤" (ዮሐ 21፥15-17)

ያዕቆብ ያየው ጌታ የሚፈልጋትን ቤተ ክርስቲያን በሦስት የተከፈሉ የሚመገቡ ግልገሎች፥ የሚጠበቁ ጠቦቶችና የሚሰማሩ በጎች ያሉበትን እውነተኛ የካራን ቤተ ክርስቲያንን ነበር:: የካራን ቤተ ክርስቲያን ስንል ሙላት ያላት ቤተ ክርስቲያን ማለታችን ነው:: የበግ መንጋዎቹም በጉድጓድ ዙሪያ ነበሩ የሚጠጡትም ከአንዱ የውሃ ጉድጓድ ነበር:: በጎቹም ሌላ ጉድጓድ አያውቁም በአካባቢው ሌላ ምንም የለም ሁሉም በጎች ከአንዱ ከኢየሱስ ይጠጡ ነበር:: ብዙ ቤተ ክርስቲያን ከየት እንደመጣ በማይታወቅ ውሃ አንዳንዴ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆነ ለመንጋው ምንም ጥቅም የማይሰጥ፥ የማያረካ ጥምን የማይቆርጥ ውሃ ለበጎች ይቀርባል:: በካራን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን ምንም ሌላ ውሃ የለም ቀጥታ በጎቹ ከአንዱ የውሃ ጉድጓድ (ከኢየሱስ) ይጠጡ ነበር:: ሌላው ያዕቆብ እረኞች የውሃውን መክደኛ <u>ድንጋይ ከጉድጓድ ሲያንከባልሉ ተመለከተ</u> :-

"መንጋዎቹ ሁሉ እዚያ ከተሰበሰቡ በኋላ እረኞች <u>ድንጋዩን አንከባለው ከጉድጓዱ ውሃ ያጠጡአቸው ነበር</u>:: መንጋዎቻቸውን ካጠጡ በኋላ ግን ድንጋዩን መልሰው በጉድጓዱ አፍ ላይ ይከድኑታል::"(ዘፍ29፥3)

እውነተኛ የእረኝነት አገልግሎት እንግዲህ ይህ ነው ድንጋዩን ከጉድጓድ እያንከባለሉ ለበጎች ውሃ ማጠጣት:: በኤፌሶን 4፥11 ላይ "ኢየሱስ ክርስቶስ አንዳንዶችን የምእመናን እረኞች" አድርጎ ከቅባቱ አካፍሎ ሰጥቶአል ነገር ግን እውነተኛ የእረኝነት ጥሪ የሌላቸው ከቅባቱ ያልተካፈሉ አንዳንድ ሰዎች ድንጋዩን ለማንከባለል ይሞክራሉ ነገር ግን ባልተሰጣቸው የቅባት መጠን ድንጋዩን ለማንከባለል መሞከር በፍፁም የማይቻል ነው:: <u>ምክንያቱም የድንጋዩ ማንከባለያ ቁልፍ የቅባቱ ኃይል ነውና::</u> በካራን ግን እውነተኛ የበጎች እረኞች ስላሉ ድንጋዩን ማንከባለል ለእነርሱ በጣም ቀላል ነው:: ስለዚህ እውነተኛ እረኛ ማለት በሕይወት ምንጭ በክርስቶስና በሦስት ቦታ በተከፈሉ የበግ መንጋዎች መካከል ቆመው ድንጋዩን የሚያንከባልሉ ናቸው:: ለዚህም ነበር ሙሴ ስለ እረኛ በዘኍልቁ





27፥15 ላይ ሲጸልይ በመጀመሪያ የጠቀሰው "የሕይወት ሁሉ ምንጭ የሆንክ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ" ያለው ሙሴ ስለ እረኛ ሲጸልይ ይህንን ያለበት ምክንያት የሕይወት ሁሉ ምንጭ በሆነው በእግዚአብሔርና በእረኛ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት እንዳለ በሚገባ ስለተረዳ ነበር::

ያዕቆብ እውነተኛዋን የካራን ቤተ ክርስቲያን ማየት ብቻ ሳይሆን እርሱም ከዚች ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ሆነ::

" ያዕቆብ የአጎቱን የላባን በጎች እየነዳች ስትመጣ ራሔልን <u>አይቶ ወደ ጉድጓዱ ሄደ ጉድጓዱ የተከደነበትንም ድንጋይ አንከባሎ በጎቹን አጠጣቸው"</u> (ዘፍ 29፥10)

ያዕቆብ በነገር ሁሉ ብቃትን አገኘ "ከዚያን በኋላ ራሔልን ሳማት ከደስታውም ብዛት የተነሣ አለቀሰ" (ዘፍ 29፥11) ያዕቆብ ድንጋዩን ካንከባለለ በኋላ ራሔልን ሳማት ምክንያቱም ራሔል የካራን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነበረች:: (ዘፍ 29፥9) ከራሔል ጋር በመሳሳሙ ከካራን ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድነቱን ገለጠ ከዚያም ከደስታውም ብዛት የተነሣ አለቀሰ:: ያዕቆብ ያለቀሰው ብቃትን በሚሰጥ መንፈስ እውነተኛውን አገልግሎት ለማገልገል በመቻሉ ነበር:: ርብቃ ወደ ነገረችው አሳብ በመድረሱ ራእዩ በመፈፀሙ ከዚህ በላይ ለአገልጋይ የሚያስደስተው ነገር ስለሌለ ያዕቆብ ከደስታው ብዛት የተነሳ አለቀሰ::

በዘመናችን ያሉ የቤተ ክርስቲያን እረኞች በነገር ሁሉ ብቃትን አግኝተው ለማገልገል የሚችሉት የማንንም ወደ እግዚአብሔር ክብር የማያደርስ አሳብ ሳይሰሙና ሳይፈሩ የጠራቸውን ጌታ ብቻ በማየት ብዙ ትርምስ ያለበትን ከኤሳው ዕቅድ ጋር የተቀላቀለውን እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልሆነውን የቤተ ክርስቲያን አመራርና ሰው ሠራሽ ሥርዓት (ዶክትሪን) ዋጋ ከፍለው በቤርሳቤህ ጥለው ወደ ካራን ጉዞ ሲጀምሩ የዛን ጊዜ እንደ ኢያሱ በነገር ሁሉ ብቃትን የሚሰጥ መንፈስ ይቀበላሉ:: ኢያሱ ዐማሌቅን አይፈራም እግዚአብሔር ወደ አሳየው ምድር ለመግባት ቁርጥ ውሳኔ ያደረገ ሰው ነበር:: ከዚህም የተነሣ ሕዝቡን ለመምራት ብቃትን የሚሰጥ መንፈስ የተሞላ ነበር::

በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር ብቃትን የሚሰጥ መንፈስ የተሞሉ እረኞችን ይፈልጋል:: ስለዚህ ዐማሌቅን የማይፈሩ የእግዚአብሔርን

የዘመኑን ዕቅድ የተረዱ÷ ዋጋን ከፍለው በቤርሳቤህ ብቃት እንደማይገኝ አውቀው እንደ ያዕቆብ ቤርሳቤህን ትተው እውነተኛውን አገልግሎት ለማገልገል በቅባቱም ኃይል ድንጋዩን ለማንከባለል ወደ ካራን የሚወጡትን፤ በሦስት የተከፈሉ መንጋዎችን ለመመገብ እንደ ኢያሱና እንደ ያዕቆብ በሁሉም ነገር ብቃትን የሚሰጥ መንፈስ የተሞሉ እረኞች በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይነሣሉ::

## *ሐ) እረኛ በሊቀ ካህኑና በማኅበሩ መካከል የሚቆም ነው*

"<u>በካህኑ በአልዓዛርና በመላው ማኅበር ፊት እንዲቆም አድርገው</u>"
(ዘኁ 27÷19)

እረኛ ማለት ከላይ ባለው ጥቅስ መሠረት በካህኑና በማኅበሩ ፊት የሚቆም ነው:: በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ሙሴን በአንተ ፊት ወይም በሰባዎቹ ፊት የሚቆም አላለውም:: እንዲሁም በእግዚአብሔር በእራሱ ፊት እንዲቆም አላዘዘውም ነበር:: እግዚአብሔር የመረጠው ሊቀ ካህኑን አልዓዛርን ብቻ ነበር:: ይህም የአዲስ ኪዳን ጥላ የሆነ የማይሻር ቃል ነው:: ዛሬም ቢሆን እረኛ የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናችን በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መካከል የሚቆም ነው:: ቀደም ሲል በካራን ያሉ እረኞች በምንጩና በበጎቹ መካከል እንደቆሙ ተመልክተን ነበር:: እዚህ ላይ ምእመናን መረዳት ያለባቸው ነገር ቢኖር እረኞች የተለዩ ሰዎች ስለሆኑ አይደለም በክርስቶስና በምእመናን ፊት የሚቆሙት እንደ ማንኛውም አማኝ ከጨለማው ዓለም የወጡ÷ ከሰይጣን መንጋጋ ያመለጡ÷ በእግዚአብሔር ምሕረት በክርስቶስ ደም የነፁ ናቸው:: ልክ ኢያሱ በግብፅ በባርነት ቤት እንደነበረ የነበሩ ናቸው:: ነገር ግን በኤፌሶን 4÷11 ላይ "አንዳንዶችን የምእመናን እረኞች አደረገ" በሚለው ቃል መሠረት ልክ ኢያሱን ለእረኝነት እንደመረጠው ክርስቶስም ምርኮን ማርኮ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ካዳናቸው ከብዙ ቅዱሳን መካከል አንዳንዶችን እረኛ እንዲሆኑ ከእርሱ የእረኝነት ቅባት አካፈላቸው:: ስለዚህ ከራሳቸው የተነሣ ሳይሆን ከተቀበሉት ቅባት የተነሣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ ፊት ለመቆም የበቁ ናቸው:: ስለሆነም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራስ ናቸው::

እረኞች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ መካከል ሆነው የእግዚአብሔርን የልቡን አሳብ ለሕዝቡ የሚያስተላልፉና የእግዚአብሔርን ማንነት በምእመኑ መካከል በመግለፅ ፍቅሩን÷ ቸርነቱን÷ ምሕረቱን÷





የይቅርታውን ብዛትና እንዲሁም እግዚአብሔር የሚባላ እሳት የፍርድም አምላክ እንደሆነና ከሕዝቡም የሚፈልገው ነገር እንዳለ በማሳወቅ ከመንጋው ነውርን÷ ዕድፈትና የፊት መጨማደድን የሚያወጡ ናቸው:: እውነተኛ እረኞች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን አሳብ ወደ ምእመኑ የሚያጓጉዙ ናቸው:: አንድን የመጓጓዣ ዕቃ መጓጓዣ የሚያሰኘው ስለሚያጓጉዝ ነው አለበለዚያ ግን ስም ብቻ ያየዘ ዕቃ ነው የሚሆነው:: እንዲሁም እረኞች እውነተኛውን የእግዚአብሔርን አሳብ ለሕዝቡ መግለፅ ካልቻሉ ስም ብቻ የያዙ ድርጊት የጎደላቸው ናቸው:: በጢሞቴዎስ መልእክት ላይ ምንም እንኳን እረኛው ጢሞቴዎስ የሚል ባናገኝም ወጣቱ ጢሞቴዎስ የእረኝነት አገልግሎት እንደሚያገለግል ሐዋርያው ጳውሎስ በላከለት መልእክቱ ላይ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው::

ጢሞቴዎስ በእረኝነት አገልግሎቱ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የሚቆም ስለሆነ ብዙ ኃላፊነት እንዳለበት ጳውሎስ ያሳስበው ነበር:: በተለይ በአንደኛ ጢሞቴዎስ 6÷13 እና በሁለተኛ ጢሞቴዎስ 4÷1-2 ላይ ጢሞቴዎስ በእግዚአብሔር ፊት የቆመ እረኛ በመሆኑ እራሱን ያለ ዕድፈትና ያለ ነቀፋ እንዲጠብቅ በጊዜውም አለጊዜውም በመፅናት÷ በማስተማር÷ በመምከር÷ በመዝለፍና በመገሰፅ የእግዚአብሔርን አሳብ በትክክል ማስተላለፍ እንዳለበት እንዲሁም የቆመው በማን ፊት እንደሆነ በማሳሰብ የተሰጠውን የወንጌል አደራ እንደሚገባ እንዲወጣ ይመክረዋል:: ስለዚህ እረኞች ከእነርሱ በታች ላሉት ሽማግሌዎች ÷ ዲያቆናትና አገልጋዮች እንዲሁም ለምእመናን የእግዚአብሔርን የልቡን አሳብ በመግለፅ የሚያስተዳድሩ ናቸው::

ዛሬ የአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን እረኞች የስም ባላባት ብቻ ሆነው ነው የሚታዩት:: በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ አንዳንዶቹ እግዚአብሔር ለምን እረኛ እንዳደረጋቸው እንኳ በቅጡ አያውቁም:: አንዳንዶቹ ደግሞ ያሉበት መንፈሳዊ ደረጃ ከምእመኑ እንኳ ተለይቶ አይታይም ወይም አይታወቅም:: አንዳንዶቹ ደግሞ ሰው ባወጣው ሥርዓትና ትብታብ ተይዘው እውነተኛውን የእግዚአብሔር አሳብ ሳያገለግሉ ዓመታትን ይቆጥራሉ:: ያለ እግዚአብሔር አሳብ ወደ ሙላቱ መድረስ ስለማይቻል የሚመሩትንም ሕዝብ ከብዙ የእግዚአብሔር ክብር የጎደሉ ያደርጓቸዋል:: ከዚህ የተነሣ እየጠፋ ላለው ነገር ተጠያቂ የሚሆኑት እረኞች ናቸው:: እንደነዚህ ያሉ የቤተ ክርስቲያን እረኞች ይህ ዘመን የተሐድሶ ዘመን መሆኑን አውቀው መንቃት አለባቸው:: ካልነቁ የእረኝነት በትራቸውን ወይም መቅረዛቸውን

ከእጃቸው የሚወስድ ጌታ በደጅ እንዳለ ጠንቅቀው መረዳት አለባቸው:: ምክንያቱም ይህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ እየያዘች ያለችበት ዘመን ነውና::

## *መ)እረኛ ማኅበሩ ይታዘዙለት ዘንድ የሥልጣን ተካፋይ ነው*

> *"መላው የእሥራኤል ማኅበር እርሱን ይታዘዙት ዘንድ የሥልጣንህ ተካፋይ አድርገው"* (ዘኊ 27÷20)

ይህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ቅርፅ እየያዘች ያለችበት የተሐድሶ ዘመን በመሆኑ በተለይ የመሪዎች አገልግሎትና አቀማመጥ የሥልጣንም አጠቃቀም ትልቅ መታደስ የሚያስፈልገው ስለሆነ በጥቂቱ ሰፋ አድርገን እንመለከተዋለን::

ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ካለማግኘታችን የተነሣ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተብራራ ጉዳይ የለም በማለት ብቻ ለብዙ ዘመን የቤተ ክርስቲያን አመራር እንደ እግዚአብሔር ቃል ባልሆነ ሁኔታ ተመርቶአል:: እግዚአብሔር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ በሆነበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ሥልጣን ወይም አገዛዝን አስቀምጧል:: እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ ነውና:: እግዚአብሔር ለእረኝነት ለመረጠው ለኢያሱ መላው የእስራኤል ማኅበር እንዲታዘዙለት ሥልጣን ሰጥቶት ነበር:: በ1972 ዓ.ም የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት <u>"ሥልጣን"</u> የሚለውን ቃል ፍቺውን ሲያስቀምጠው "በነገር ሁሉ የመምራት÷ የመፍረድ÷ የመግዛትና ማንኛውንም ነገር የማድረግ ሙሉ መብት" ይለዋል::

እግዚአብሔር ለኢያሱ የእረኝነት ሥልጣን ሲሰጠው መላውን የእስራኤል ማኅበር ሊመራ÷ መፍረድ በሚገባው ነገር ላይ ሊፈርድ÷ ሊያስተዳድር በነገር ሁሉ ላይ መብት ያለው አድርጎ ነበር ሥልጣን የሰጠው:: ሙሴ ለኢያሱ ሥልጣኑን ካስተላለፈ በኋላ ሕዝቡን ለመምራት ከኢያሱ በላይ ሥልጣን ያለው አልነበረም:: በማኅበሩ ፊት ሙሴ የመረጣቸው ሽማግሌዎች÷ የሕዝቡ አለቆች÷ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ የተጠሩ ሌዋውያንም ነበሩ ነገር ግን ሁሉም ከኢያሱ ሥልጣን በታች ነበሩ:: ሁሉም ይታዘዙለት ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔር በማኅበሩ ሁሉ ላይ የሾመው እረኛ ነበርና::





ባለንበት ዘመን በተለያዩ ቦታዎች የብዙ አብያተ ክርስቲያናት ትልቅ ችግር ባለሥልጣኑ ማን እንደሆነ ስለማይታወቅ ነው :: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም ባለሥልጣን ከሌላት ብዙ የእግዚአብሔር ሥራ እንደሚበላሽ ግልፅ ነው:: በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንድ የበላይ ባለሥልጣን ወይም ተቆጣጣሪ የግድ ያስፈልጋል ይህም የእግዚአብሔር አሠራር እንጂ የሰው አሠራር አይደለም:: ብዙ ጊዜ የምናመካኘው ነገር ቢኖር እረኛው ሙሉ ሥልጣን መያዝ የለበትም ምክንያቱም ሥጋ የለበሰ ሰው ስለሆነ የግድ ከሽማግሌዎች ጋር በእኩል ሥልጣን መሄድ አለበት የሚል ምንም ቦታ ሊሰጠው የማይገባ አመለካከት አለ:: ኢያሱ በዘኊልቁ 26÷1-63 ለሁለተኛ ጊዜ የተቆጠሩትን ስድስት መቶ ሺህ (600.000) በምድረ በዳ የተወለዱትን አዲሱን ትውልድ እየመራ በሙሉ ሥልጣን ከነዓን ያደረሰው ብረት ለበስ ሰው ወይም ሥጋ የሌለው መንፈስ ብቻ ስለሆነ አልነበረም:: እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲመራለት ስለመረጠውና ስለቀባው ብቻ ነበር::

በሁሉም ነገር እረኛውና ሽማግሌዎች በእኩል ሥልጣን በአንድ ቤተ ክርስቲያን መቀመጥ የእግዚአብሔር ቃል የማይደግፈን ለእግዚአብሔር ሥራ ትልቅ እንቅፋት የሆነ ከእግዚአብሔር ቤት ውስጥ መወገድ ያለበት ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር መሥራት የሚፈልገው እራሱ በሰጠን ሥልጣን አማካኝነት ነው:: እግዚአብሔር ስለ ቤተ መቅደሱ አሠራር ለሙሴ ሲነግረው በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ እንድትሠራው ተጠንቀቅ:: (ዘፀ 25÷40) ሙሴ ከእግዚአብሔር በተቀበለው አሠራር ነበር እንዲሠራ የተነገረው:: ከእግዚአብሔር ባልተቀበልነው አሠራር ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት መሞከር ያዕቆብ እንደሚለን በእውነት ላይ መዋሸት ነው:: በሰማያዊ ጥበብ ሳይሆን በምድራዊ ጥበብ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት መሞከር ነው:: ይህም ምድራዊ ጥበብ ከሥጋ÷ ከዓለም÷ ከሰይጣን እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም:: (ያዕ 3÷14-16)

ቤተ ክርስቲያን በብዙ ሰዎች በምድራዊ ጥበብ በእኩል ሥልጣን ስትመራ ሁሉም የየራሱን ሥልጣን ለማንፀባረቅ ሲል ሁሉም በመራራ ቅናት÷ በአድመኝነትና በራስ ወዳድነት ይያዛሉ:: ምድራዊ ጥበብ ባለበት ሁሉ ሁከትና ክፉ ሥራ ይገኛል:: (ያዕ 3÷14-16) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣን ስታጣ በተለይም ቤተ ክርስቲያንን በመምራት ላይ ባሉ ሰዎች መካከል ሁል ጊዜ ሁከት÷ አድመኝነትና ክርክር ይሆናል:: ነገር ግን ይህ

እንዳይሆን እግዚአብሔር በሽማግሌዎችና በእረኞች መካከል የሥልጣን ልዩነት አስቀምጧል::

ሽማግሌዎች በእረኞች ስለሚመረጡ በሥልጣን ከእረኞች በታች ናቸው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በኤፌሶን ቲቶን በቀርጤስ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያደራጁ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችንም እንዲሾሙ በመልእክቱ ላይ ይገልፅላቸዋል:: (1ጢሞ 3÷1-7) (ቲቶ 1÷5-9) እዚህ ላይ የምንረዳው ትልቅ ነገር አለ ይኸውም ጳውሎስ ሽማግሌዎችን ሾመ ጢሞቴዎስና ቲቶም ጳውሎስ በሰጣቸው መመሪያ መሠረት ከምእመኑ በመምረጥ ሽማግሌዎችን እንዲሾሙ ነገራቸው:: እንዲሁም ሙሴ ሥራው በከበደው ጊዜ ረዳት የሚሆኑትን ሽማግሌዎች ሙሴ የሚያውቃቸውን መርጦ እንዲሾም እራሱ እግዚአብሔር ነው ለሙሴ የመምረጡን ሥልጣን የሰጠው::

> "እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ለሕዝብ አመራር በመስጠት የታወቁ ሰባ ሰዎችን ምረጥ እነርሱንም ሰብስበህ እኔ ወደምመለክበት ድንኳን አምጣቸውና በአጠገብህ ይቁሙ::" (ዘኁ 11÷16)

ሙሴ የማስተዳደር ጸጋ ያላቸውንና የሚያውቃቸውን በታማኝነት ይረዱኛል የእግዚአብሔርንም ሥራ በቅንነት ይሠራሉ የሚላቸውን በተቀበለው ቅባት በኩል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መርጦ ሾመ::

<u>እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን ሽማግሌዎች በተቀቡ ሰዎች አማካኝነት በመንፈስ ቅዱስ ስለሚሾሙ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስተዳድሩበት የሚጠብቁበት ፀጋ ይቀበላሉ:: ነገር ግን እንደ እረኛ ቅባት ፈፅሞ አይሆንም::</u> ሙሴ÷ጳውሎስ÷ ጢሞቴዎስና ቲቶም ሽማግሌዎችን የመሾም ሥልጣን እንደነበራቸው እንዲሁም ባለንበት ዘመን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚያውቃቸውን ለአገልግሎት ይረዱኛል የሚላቸውን የማስተዳደር ጸጋ ያላቸውን እውነተኛ በታቸውን የሚያውቁትን ሽማግሌዎች የመሾም ሥልጣን ያለው እረኛው ነው:: ምናልባት የዘመኑ ፈሪሳውያን ይህ እውነት ሊያስቃቸው ይችላል ነገር ግን የታላቁ የአምላካችን አሠራር ነውና ለእግዚአብሔር አሠራር ራሳችንን አጋልጠን መስጠት አለብን::





ባሁኑ ዘመን በብዙ ቦታዎች የቤተ ክርስቲያን አሠራር እንደ እግዚአብሔር ቃል ሳይሆን በኮሚቴና በእጅ ብልጫ ሆኖ እናገኘዋለን " ግርግር ለሌባ ያመቻል " እንደሚባለው ሁሉ እንዲሁም የኮሚቴና የእጅ ብልጫ አሠራር ለሰይጣን የስርቆት ሥራ አመቺ በር መክፈት ነው:: ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ቃል ካልሆነ አሠራር ቤተ ክርስቲያን ወጥታ ወደ በረከት ሙላት እንድትደርስ እንደ እግዚአብሔር ቃል መራመድ አለባት::

ሌላው በዘኁልቁ 11÷17 ላይ " እኔም ወደዚያ ወርጄ ከአንተ ጋር እነጋገራለሁ ለአንተም ከሰጠሁህ መንፈስ ከፍዬ ለእነርሱ እሰጣቸዋለሁ ከዚያም በኋላ በእነዚህ ሕዝብ ላይ ያለህ ኃላፊነት በመሸከም ይረዱሃል ከእንግዲህ ወዲህ ይህንን ሁሉ ኃላፊነት ብቻህን አትሸከምም":: እዚህ ላይ በሕዝቡ ላይ ያለህን ኃላፊነት <u>በመሸከም ይረዱሃል</u> እንጂ <u>የሥልጣንህ</u> ተካፋይ ይሆናሉ አላለውም:: <u>"ይረዱሃል"</u> የሚለው ቃል ራሱ ከእርሱ በታች መሆናቸውን ያስረዳል ስለዚህ የእስራኤል ሽማግሌዎች ከተመረጡ በኋላ ከሙሴ ሥልጣን እኩል እንመራለን ያሉበት ጊዜ አልነበረም ፤ በኢያሱም ዘመን እንዲሁ ፤ በሐዋርያትም ዘመን ሽማግሌዎች ከተሾሙ በኋላ ከሐዋርያት እኩል ለመሆን አልሞከሩም:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲመክረው በነገር ሁሉ የመምራት÷ የመፍረድ÷ የመሾም÷ ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት እንድትራመድ ለማድረግ ሙሉ መብት እንዳለው ነግሮታል:: ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያንን የመጠበቅ÷ የማስተዳደር÷ የማስተማር ችሎታ ያላቸው በመሆን ለመንጋው ምሳሌ ሆነው የመመላለስ ኃላፊነት አለባቸው:: የተሰጣቸውንም ኃላፊነት በትክክል መወጣት አለባቸው:: ሆኖም የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እረኛ መንጋውን ለመምራት <u>ሙሉ ሥልጣን</u> የተቀበለ ስለሆነ ሽማግሌዎች በእርሱ ሥልጣን ሥር ሆነው የእርሱ ረዳት መሆናቸውን በሚገባ ማወቅ አለባቸው:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከእረኛ ሥልጣን ሥር ሆነው እራሳቸውን አስገዝተው መመላለስ ሞታቸው ነው:: እንዲያውም ባልተሰጣቸው ሥልጣን እረኛውን በቁጥጥር ሥር ለማድረግ በሥጋዊ ምኞት በከንቱ ይጥራሉ::

በአንደኛ ጢሞቴዎስ 3÷6 ላይ በትዕቢት ተነፍቶ ዲያብሎስ እንደተፈረደበት እንዳይፈረድበት አዲስ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን መሪ አይሁን ይላል:: እዚህ ላይ የምንማረው ትልቅ ነገር ዲያብሎስ የተፈረደበት በአንድ ነገር ነው ይኸውም እራሱን ከእግዚአብሔር ሥልጣን በላይ አደርጋለሁ በልዑልም እመስላለሁ ብሎ ባልተሰጠው ሥልጣን በትዕቢት

ተነፍቶ እራሱን ከፍ ከፍ ሲያደርግ በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ ወደቀ:: እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ባልተሰጣቸው ሥልጣን እራሳቸውን ከፍ ከፍ ሲያደርጉ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለን ዲያብሎስ እንደተፈረደበት በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ መውደቃቸው የማይቀር ነው:: ምናልባት ለአዲስ ክርስቲያን ነው የተፃፈው ልንል እንችላለን አዲስ ክርስቲያን ማለት ብዙ የቃሉ እውቀት የሌለው ማለት ነው:: የዓመታት ብዛት መብሰላችንን አያመለክትም:: ማንም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በእግዚአብሔር ቃል ተሞልቶ ትክክለኛ ቦታውን ካላወቀ የሁሉ በላይ ሆኖ ለመታየት የሚወድ ሽማግሌ ከአዲስ አማኝ የተሻለ ሕይወት አይኖረውም::

ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ቀብቶ በሰጣቸው እረኛ በኩል ለሚመጣው የእግዚአብሔር አሳብ÷ ራእይና ዕቅድ ታዛዥ መሆን አለባቸው እንጂ ተቃዋሚ እንዲሆኑ እግዚአብሔር አላስቀመጣቸውም:: ሽማግሌዎች የእረኞች ሥልጣን ተቃዋሚ ከሆኑ ቀደም ብለን እንዳየነው የእግዚአብሔርን ሥራ ለማበላሸት በወጣው የዐማሌቅ መንፈስ አሠራር እእምሮአቸው የተያዘ ነው:: ስለሆነም ኤሳው የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማበላሸት ያዕቆብን ሲያስጨንቀው እንደነበረ እንደነዚህ ዓይነት ሽማግሌዎች ሁል ጊዜ የእረኞችን ሥልጣን በመቃወም የእረኞች ቅባት በትክክል እንዳይሠራ ዕንቅፋት ይሆናሉ:: እረኞች በእንደነዚህ ዓይነት ሽማግሌዎች ላይ ዋጋ ከፍለው ቁርጥ እርምጃ ካልወሰዱ በቀር ሁሌ ከኤሳው ጋር የቤርሳቤህ ኑሮ ስለሚኖሩ ቀስ በቀስ እረኞች በአገልግሎታቸው ተስፋ መቁረጥ÷ ግድ የለሽ መሆን እየታየባቸው በመጨረሻም በሕይወታቸው ያለው የእግዚአብሔር ዕቅድ ፈፅሞ የተበላሸ ይሆናል:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን እረኞች ከውጭ ባለው የጠላት ተቃውሞ ሳይሆን ከውስጥ ባለው ተቃውሞ ነው ብዙ የሚቸገሩትና ዝለውም የሚወድቁት::

በካይሮ ከተማ ውስጥ ለአርባ አምስት ዓመታት በእረኝነት ያገለገሉ አንድ ግብፃዊ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ በአንድ አጋጣሚ ተገናኝተን ስላላቸው የእረኝነት አገልግሎት እየተጫወትን ሳለ በዓለም ዙሪያና በግብፅ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ በእረኞችና በሽማግሌዎች ስላለው የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን አጠቃቀም ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ትልቅ ዕንቅፋት እንደሆነ አጫወቱኝ:: በእርስዎ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ችግር አለ ወይ ብዬ ጠየኳቸው አሳቸውም በፍፁም የለም አሉኝ፤ እንዴት በማለት ጠየኳቸው፤ ሲመልሱልኝም ባለሁበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በእረኝነት ሥልጣን ሥር በትክክል የማይሄድና ከተሰጠው ሥልጣን





በላይ ለመሆን የሚሞክር ከሆነ በሮሜ 12÷3-8 ያለውን ቃል በማንበብ ሁሉም የተሰጠው የአገልግሎት ስጦታ እንዳለው ከተሰጠው የአገልግሎት ሥልጣን በላይ በትዕቢት እንዳያስብ በተሰጠው ሥልጣን ብቻ እንዲንቀሳቀስ ከቃሉ ላይ በደንብ አስረግጬ እነግረዋለሁ:: ከዚህ የተነሣ እኔ ባለሁበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ ዓይነቱ ችግር የለም አሉኝ :: በተጨማሪም ሲገልፁልኝ ይህን ሁሉ የማደርገው እኔ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመጀመሪያው ሰው ሆኜ ለመታየትና ለእራሴ ክብር ለመኖር ሳይሆን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ቃሉ መመራት ስላለባት ነው አሉኝ :: እዚህ ላይ ትልቅ ጥያቄ መጠየቅ የምፈልገው ሥልጣኑን አውቆ ቤተ ክርስቲያን በሥርዓት እንድትመራ የሚያደርግ እረኛ ማነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰው ሽማግሌዎች ሊኖራቸው ስለሚገባ ባህርያት መካከል የማይጨቃጨቅ÷ የማይከራከር÷ ስለ አለመታዘዝ የማይከሰስ የሚል ይገኝበታል:: በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ግን ባለሥልጣኑ ስለማይታወቅ በሚኖረው የመሪዎች ስብሰባ ላይ ሽማግሌዎች ተከራካሪዎችና ተጨቃጫቂዎች ለእረኛውና ለምእመኑ ባለመታዘዝ የተያዙ ናቸው:: እውነተኛ የእረኝነት ቅባትና ፀጋ እንዳላቸው እያወቁ እግዚአብሔር ቀብቶ የሰጣቸውን እረኛ ሥልጣን የማይቀበሉ ሽማግሌዎች አገልጋዮችና ምእመናን ቀብቶ የላካቸውን እግዚአብሔርን እንጂ የሚቃወሙት ሰውን አለመቃወማቸውን መረዳት አለባቸው:: (ሉቃ 10÷16)

በተለይ በተለያዩ ሀገር ስላሉት እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለማይታዘዙ ሽማግሌዎችና መሪዎች ብዙ ማለት ይቻላል ነገር ግን በአንድ ዐረፍተ ነገር ጠቅለል አድርጌ እገልጻዋለሁ “ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ መያዝ ስላለባት የዘመናችን የሽማግሌና የመሪዎች አገልግሎት ተሐድሶ ያስፈልገዋል” ይህን ስል ሽማግሌዎች አያስፈልጉም የሽማግሌዎች አገልግሎት ጥቅምም የለውም ማለቴ እንዳይደለ ግልፅ መሆን አለበት ሽማግሌዎች በጣም ያስፈልጋሉ:: እግዚአብሔር በቀባው እረኛ በኩል የሚተላለፈውን አሜን ብለው በሥራ ላይ በማዋል ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ ያስገዙ ሽማግሌዎች አጥፍ ክብር ይገባቸዋል::

እረኞች ሥልጣን አላቸው ስንል የእግዚአብሔር ቃል የማይደግፉቸውን የራሳቸውን ምኞት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይፈፅማሉ ማለት አይደለም:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተቀበሉትንና ያመኑበትን

ማንም ሳይከለክላቸው ወደ ማኅበሩ በማስተላለፍ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲባረክ መንግሥቱም እንድትሰፋ የማድረግ ሥልጣን አላቸው ማለታችን ነው:: ስለሆነም በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እረኞች እረኛ በሆኑበት ቤተ ክርስቲያን በመላው ማኅበሩ ላይ  ሙሉ ሥልጣን ያላቸው ናቸው::

## ሠ) እረኛ በሊቀ ካህኑ የሚደገፍ ነው

> "ካህኑ አልዓዛር ኡሪምና ቱሚም በተባሉ ዕቃዎች አማካይነት ፈቃዴን  የሚያውቅ ስለሆነ <u>ኢያሱ በአልዓዛር ይደገፋል</u>::" (ዘኍ 27÷21)

ቀደም ብለን እንዳየነው እረኞች በመላው ማኅበርና በሊቀ ካህኑ ፊት የሚቆሙና መላውን ማኅበር በሥልጣን የሚያዙ ስለሆኑ ትልቅ ኃላፊነት የተቀበሉ መሆናቸውን መዘንጋት የለባቸውም:: ከዚህም  የተነሣ ከላይ ባለው ጥቅስ መሠረት ፈጽመው በሊቀ ካህኑ መደገፍ አለባቸው:: ሊቀ ካህኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ  የሚያውቅበት ኡሪምና ቱሚም ስላለው ኢያሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያወቀ ለሕዝቡ መናገር እንዲችል ፈፅሞ በሊቀ ካህኑ መደገፍ ነበረበት:: እንዲሁም በዘመናችን ያሉ እረኞች እግዚአብሔር እረኛ አድርጎናል ብለው በራሳቸው ፈቃድና አስተሳሰብ ሕዝቡን መምራት አይችሉም:: ጊዜአቸውን ሰውተው የአዲስ ኪዳን ታላቅ ሊቀ ካህን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በመደገፍ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አለባቸው:: በፀሎት ከመትጋትና ቃሉን ከማንበብ ችላ ማለት የለባቸውም:: እረኞች በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከሊቀ ካህኑ ከኢየሱስ ጋር በፀሎትና  በቃሉ ፈፅሞ መጣበቅ አለባቸው ይህም የእረኞች ከባድ ኃላፊነት ነው::

በአንድ ወቅት ከአንድ የቤተ ክርስቲያን እረኛ ጋር በአንድ አጋጣሚ ተገናኝተን ስለ አገልግሎቱ ሲያጫውተኝ በሳምንት አንድ ቀን ብቻ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነብበት ጊዜ እንዳለው ነገረኝ:: እኔም በጣም አዘንኩ:: ይህ እረኛ ሳምንቱን በሙሉ ሲባዝን ከርሞ በሳምንት አንድ ቀን የእግዚአብሔርን ቃል አንብቦ ለሕዝቡ ምን እንደሚያስተላልፍ ለሁላችን የታወቀ ነገር ነው:: እግዚአብሔር ግን ለኢያሱ ሲነግረው ይህንን ሕዝብ ታወርሳለህና ፅና አይዞህ እጅግም በርታ ካለው በኋላ ሕዝቡን እንዲያወርስ





በነገር ሁሉ መከናወን እንዲያገኝ የሚያደርገውን ታላቅ ምስጢር ሲነግረው:-

> "አንተ ብቻ አይዞህ በርታ አገልጋዬ ሙሴ ለሰጠህም ሕግ ሁሉ እውነተኛ ታዛዥ ሁን በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ ማንኛውም ነገር እንዲከናወንልህ ከዚህ ህግ ከቶ ዝንፍ አትበል  <u>ይህን የሕግ መጽሐፍ ምን ጊዜም ከማንበብ አትቆጠብ በእርሱ የተፃፈውን  ሁሉ መፈፀም ትችል ዘንድ እርሱን ሌሊትና ቀን አሰላስለው ይህን ብታደርግ ሁሉ ነገር በተቃና ሁኔታ ይከናወንልሃል::</u>"(ኢያሱ 1÷7-8)

የብዙ እረኞች ወድቆ መቅረት ምክንያት  በፀሎት ስለማይተጉና ከእግዚአብሔር  ቃል  ጋር እንደሚገባ በየቀኑ ጊዜ ስለማይወስዱ ለሕዝቡም የሚያፈሱት ነገር ስለሌለ ነው::  በክርስቶስ ላይ ስለማይደገፉ ሕይወታቸው ይደርቅና አገልግሎታቸውም የወሬ ዙሪያ ጥምጥም ብቻ ይሆናል::  ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት ስለማይችሉ የሚመሩት ምእመን ሌላ እረኛ መፈለግ ይጀምራል:: በቤተ ክርስቲያን መከፋፈልን ከሚፈጥረው ከብዙ ምክንያቶች አንዱ የእረኛው ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ  ላይ አለመደገፍና ከጌታ ጋር ጊዜን አለመውሰድ ነው:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ይፈልጋል:: ያንን ካገኙ ማር ባለበት ንብ ይሰበሰባልና ከእግዚአብሔር የሆነውን ካጡ ደግሞ ማር ወደሚገኝበት ቦታ ይሄዳሉ ወይም የቤተ ክርስቲያን እረኛውን መቃወም ይጀምራሉ::

እዚህ ላይ ከእረኞቻችሁ የሚበላን ነገር ያጣችሁ አገልጋዮችና ምእመናን ብትኖሩ አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ:: ይህም በመጀመሪያ ማድረግ ያለባችሁ ነገር ስለ እረኞቻችሁ አገልግሎት በፀሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብና ከዛም አልፎ ስለ አገልግሎታቸው ቀረብ ብሎ አሳብ÷ አስተያየትና  መስተካከል የሚገባውን ነገር ሁሉ በፍቅርና በንፁህ ሕሊና በግልፅነት መንገሩ ፍሬያማ ሊያደርጋቸው ይችላል:: ካለበለዚያ ግን እረኞችን መቃወም የእግዚአብሔር ቃል ስለማይደግፈን መፍትሔው ማር ወዳለበት ስፍራ መሄድ ብቻ ነው::

እረኞች በሊቀ ካህኑ በክርስቶስ ላይ በፀሎትና ቃሉን በማንበብ መደገፍ ሲያቆሙ እግዚአብሔር እረኛ አድርጎ እንዳስቀመጣቸው

እስኪጠራጠሩ ድረስ በራሳቸው የእረኝነት አገልግሎት አይተማመኑም:: ከዚህ የተነሣ በታላቅ ፍርሃት ውስጥ በመውደቅ የሽማግሌዎችን፥ የአገልጋዮችንና የምእመኑን አካሄድ ሁሉ ከራሳቸው የሥልጣን ወንበር ጋር በማያያዝ መልካም ሕሊና እስከማይኖራቸው ድረስ ያሉበት ወንበር እንዳይነካ በእራሳቸው አሳብ ብዙ ሥጋዊ የሆኑ አጥሮችን ማቆም ይጀምራሉ:: እሁንም የዚህ የመጨረሻ ውጤት ቤተ ክርስቲያንን እስከ መከፋፈል ያደርሳል::

ስለዚህ እረኞች በሕዝቡና በሊቀ ካህኑ ፊት በመቆም ለሕዝቡ የሚሆንን ሰማያዊ ነገር ለመመገብ፤ እንዲሁም ሞገስ አግኝተው ሙሉ ሥልጣናቸውን ለመጠቀምና የተሰጣቸውን የመሪነት ኃላፊነት እንደሚገባው ለመወጣት ኢያሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚነግረው በሊቀ ካህኑ በእልዓዛር ላይ እንደተደገፈ እንዲሁም ሁሉ በሁሉ በሆነው በክርስቶስ ላይ በቃሉና በፀሎት መደገፍ አለባቸው::

## *ረ) እረኛ በተግባር አፈጻጸም መላውን ማኅበር የሚመራ ነው*

> "…. በዚህ ዓይነት እልዓዛር ኢያሱንና መላውን የእስራኤል ማኅበር በተግባር አፈጻጸማቸው ሁሉ ይመራቸዋል" (ዘኍ 27÷21)

እዚህ ላይ "በተግባር አፈጻጸማቸው ሁሉ ይመራቸዋል" የሚለው ቃል በቀድሞው ትርጉም "የእስራኤል ልጆች በቃሉ ይግቡ በቃሉ ይውጡ" የሚል ቃል እናገኛለን:: ከላይ ባለው ጥቅስ መሠረት እልዓዛር ኢያሱንና መላውን የእስራኤልን ማኅበር በተግባር አፈጻጸማቸው ሁሉ ይመራቸዋል የሚለው አሳብ ግልፅ ሆኖ ሲብራራ ሊቀ ካህኑ እልዓዛር የሕዝቡ መሪ አይደለም ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቅበት ኡሪምና ቱሚም አለው:: ኢያሱ ግን የሕዝቡ መሪ ነው ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቅበት ኡሪምና ቱሚም የለውም ነበር:: ስለዚህ ኢያሱ ሕዝቡን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመምራት የግድ ኡሪምና ቱሚም ባለው በእልዓዛር ላይ መደገፍ አለበት:: በእልዓዛር ላይ ሲደገፍ ለሕዝቡ ምን እንደሚያስፈልጋቸው ጠንቅቆ ያውቃል አለበለዚያ ግን ሕዝቡን እንዴት መምራት እንደሚገባው አያውቅም:: ስለዚህ ካህኑ እልዓዛር በመጀመሪያ ኢያሱን ከዛ በኋላ በኢያሱ አማካኝነት ሕዝቡን በተግባር አፈጻጸመማቸው ይመራቸው ነበር::





እዚህ ላይ የምንረዳው ነገር ቢኖር እረኛ በክርስቶስ ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍ እንዳለበት ነው:: በክርስቶስ ላይ የተደገፉ እረኞች ወደ ሕዝቡ የሚያፈሱት የክርስቶስን አሳብ ብቻ ነው:: የክርስቶስ አሳብ ከሆነ ወደ ሕዝቡ የሚያፈሱት ሕዝቡን የሚመራው ክርስቶስ ይሆናል ማለት ነው:: እረኞች የእግዚአብሔር አሳብ ማስተላለፊያ አሸንዳዎች ናቸው:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ሲነግረን ካህኑ እልዓዛር ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት የእግዚአብሔርን አሳብ ለኢያሱ ይነግረዋል ኢያሱም ደግሞ በሊቀ ካህኑ ላይ ስለሚደገፍ የእግዚአብሔርን አሳብ በመስማት ለሕዝቡ ያስተላልፍ ነበር:: ዛሬም ቢሆን እንደ ኢያሱ ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ያዳነው ሕዝብ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚገልፀው የቤተ ክርስቲያን እረኞች አድርጎ ለቀባቸው ሰዎች ነው:: እረኞች ደግሞ ለሚመሩት ሕዝብ የተቀበሉትን የእግዚአብሔርን የዘላለም አሳብ ያስተላልፋሉ::

"እልዓዛር ኢያሱንና መላውን የእስራኤልን ማኅበር በተግባር አፈጻጸማቸው ሁሉ ይመራቸዋል" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በኢያሱና በሙሴ ሕይወት በሚገባ ተፈፅሞ እናገኛለን::

> "እግዚአብሔር ትእዛዙን ለአገልጋዩ ለሙሴ ሰጠ፤ ሙሴም ለኢያሱ ሰጠ፤ ኢያሱም ትእዛዛቱን ፈፀመ፤ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ኢያሱ ሁሉን ነገር አደረገ፤ አንዳችም ነገር አላስቀረም:: " (ኢያ 11÷15)

ከላይ ባለው ጥቅስ መሠረት እግዚአብሔር ሙሴን በሙሴም አማካይነት ኢያሱን ይመራው እንደነበር፤ ኢያሱም በሙሴ አማካኝነት የተገለጠለትን የእግዚአብሔርን አሳብ አንድም ሳይቀር ይፈጽመው እንደነበር ያስረዳል::

ስለዚህ እረኞች ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ምሪት ለሕዝቡ በሚያስተላልፉበት ጊዜ ሕዝቡ ማወቅ ያለበት ትልቅ ነገር እግዚአብሔር በእነርሱ አማካኝነት እየመራቸው እንደሆነ ነው:: ብዙ ጊዜ ከእረኞች የሚወጣውን አሳብ እንደ ቀላል ነገር በመቁጠር ከእግዚአብሔር አሳብ በጣም እንርቃለን:: ብዙ በወቅቱ መፈፀም ያለበት የእግዚአብሔር ሥራ ሳይፈፀም ይቀራል:: ለምሳሌ በእረኛው በኩል ለሚመጣው ራእይ ኃላፊነቱ የእራሱ የእረኛው ወይም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ብቻ ይመስለናል::

የእረኛ ትልቅ አገልግሎት ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ምሪት ለሕዝቡ ማስታወቅና ቀዳሚም በመሆን ከሕዝቡ ጋር አብሮ በመሰለፍ ከግብ ማድረስ ነው:: ሕዝቡ ግን ካልታዘዙለት ምንም ማድረግ አይችልም:: እግዚአብሔር ውጡ ይላችኋል ሲላቸው ሕዝቡ የሚገቡ ከሆነ የእግዚአብሔር አሳብ አይፈጸምም::

እረኞች መንጋውን የመምራት ሥልጣን ቢኖራቸውም እጅ እየጠመዘዙ በግድ የእግዚአብሔር አሳብ እንዲፈጸም አያደርጉም:: ባላቸው የአገልግሎት ሥልጣን በእግዚአብሔር ዕቅድ ላይ የሚነሱትን ይቃወማሉ፥ ይገስጻሉ፥ ይመክራሉም፥ መወገድ ያለበትን እንዲወገድ ያደርጋሉ:: ነገር ግን መንጋውን በኃይል መግዛት ስለማይችሉ ሽማግሌዎች አገልጋዮችና ምእመኑ በፍቅር ለእረኞች በጣም ታዛዥ መሆን አለባቸው:: በእረኛው በኩል ለሚመጣው የእግዚአብሔር አሳብ ሕዝቡ እንደ አንድ አካል ሆኖ መነሣት አለበት::

እግዚአብሔር ኢያሱን በእረኝነት ሲቀባው ሕዝቡ በቃሉ እንዲገቡ በቃሉ እንዲወጡ ሥልጣን ሰጥቶት ነበር:: ይህም ማለት አታድርጉ ያላቸውን አያደርጉም፤ አድርጉ ያላቸውን ያደርጋሉ፤ ውረሱ ያላቸውን ይወርሳሉ፤ ተዋጉ ሲላቸው ይዋጋሉ፤ ተሻገሩ ሲላቸው ይሻገራሉ ምክንያቱም በአፉ ላይ የተቀመጠው ለሕዝቡ የሚናገረው ቃል የተገኘው የክርስቶስ ምሳሌ ከሆነው ከሊቀ ካህኑ ከአልዓዛር ነበር:: ስለዚህ ኢያሱ ከአፉ በሚወጣው ቃል መላው የእስራኤል ሕዝብ ይታዘዙለት ነበር:: ይህንንም መጽሐፍ ቅዱሳችን ሲያረጋግጥልን እግዚአብሔር ለኢያሱ መንገር የሚገባውን ከነገረው በኋላ "ከዚህ በኋላ ኢያሱ የሕዝቡን አለቆች እንዲህ ብሎ አዘዘ ወደ ሰፈር ገብታችሁ ሕዝቡን ስንቃችሁን አዘጋጁ ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላካችሁ የሚሰጣችሁን ምድር ለመውረስ በሦስት ቀን ውስጥ የዮርዳኖስን ወንዝ ትሻገራላችሁ ብላችሁ ንገሩ":: (ኢያሱ 1÷10) ለሕዝቡ በዚሁ ምዕራፍ ላይ ከቁጥር 12 እስከ 15 ድረስ ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ ነገራቸው ሕዝቡም በአንድ ልብና በአንድ አሳብ ከኢያሱ ጋር ቃል ኪዳን ገቡ::

" እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ብለው መለሱለት የነገርከንን ሁሉ እንፈፅማለን፤ ወደምትልከንም ስፍራ ሁሉ እንሄዳለን፤ ለሙሴ ሁል ጊዜ ስንታዘዝለት እንደነበረው ሁሉ፥ ለአንተም እንታዛዛለን፤ እግዚአብሔር አምላክህ





ከሙሴ ጋር እንደነበረ ከአንተ ጋር ይሁን ! የአንተን ሥልጣን የሚቃወምና ትእዛዝህን ሁሉ የማይፈጽም ቢኖር በሞት ይቀጣ፤ ብቻ አንተ አይዞህ ! በርታ !"

(ኢያሱ 1÷16-18)

ከላይ ባለው ጥቅስ ላይ <u>ሕዝቡ የገባቸው ቃል ኪዳኖች</u>

1. የነገርከንን ሁሉ እንፈጽማለን
   —> ወደ ከነዓን ለመድረስ::
2. ወደምትልከን ስፍራ ሁሉ እንሄዳለን
   —> በጦርነት ጠላትን ድል ለማድረግ::
3. ለሙሴ እንታዘዝ እንደነበር ሁሉ ለአንተም እንታዘዛለን
   —> መታዘዝ ከመስዋዕት ስለሚበልጥ::
4. እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደነበረ ከአንተ ጋር ይሁን
   —> እግዚአብሔር የቀባቸውን በመባረክ በረከት እንደሚገኝ ስለሚያውቁ::
5. የአንተን <u>ሥልጣን የሚቃወም ትእዛዝህንም የማይፈፅም</u> ቢኖር በሞት ይቀጣ
   —> በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል የቆመ፥ ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ሥልጣንን እንደተቀበለና የሚያዛቸውም ትእዛዝ ከእግዚአብሔር እየተቀበለ እንደሆነ ስላወቁ የማይቀበለውን በሞት እንደሚቀጣ በመግለጽ ቃል ኪዳን ገቡ:

ዛሬም ቢሆን በቤቱ ላስቀመጣቸው እረኞች ምእመኑ ታዛዥ እንዲሆኑ እግዚአብሔር ይፈልጋል:: ከእረኛው ጋር በአንድ ልብ የሚሠራ፥ በእረኛው ቃል የሚወጣና የሚገባ፥ የእግዚአብሔር አሠራርን የተረዳ ሕዝብ እግዚአብሔር ይፈልጋል:: ቤተ ክርስቲያን በእረኞች በኩል ለሚመጣው ለእግዚአብሔር አሳብ መታዘዝን ካላወቀች ለውጥን አታይም:: ለምሳሌ መውረስ ያለብን አንድ ነገር ሲኖር እረኛው እግዚአብሔር ውረሱ ይለናል የምንወርሰውም በእንዲህና በእንዲህ ዓይነት መንገድ ነው ብሎ ለሕዝቡ ሲያስታውቅ ሕዝቡ እግዚአብሔር ተናግሮናልና እንውጣና እንውረስ ብሎ ዋጋን ከፍሎ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ነገር ለመውረስ ካልተነሣ ለውጥን የማያይ ጉባኤ ይሆናል፤ ከቃዴስ ወደ ቃዴስ የሚሽከረከር የለመለመችውን ወተትና ማር የምታፈሰውን ከነዓንን ሳያይ በምድረ በዳ የሚቀር ሕዝብ ይሆናል:: እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው ትልቅ ነገር ቢኖር የሕዝቡ

አለመታዘዝ ነው:: እንዲሁም እረኞች በጣም የሚያዝኑበት ነገር ቢኖር የሚመሩት ሕዝብ ባለመታዘዝ ኃጢያት ሲያዝ ነው:: ስለዚህ የእስራኤል ሕዝብ ኢያሱን ለመታዘዝ ቃል ኪዳን ከኢያሱ ጋር እንዳደረጉ ዛሬም ለሚመሩን የቤተ ክርስቲያን እረኞች ለመታዘዝ እያንዳንዳችን የቃል ኪዳን ሰዎች መሆን አለብን::

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፍፁምነት እንድትደርስ የእረኞች ቅባት ለቤተ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ነው:: ስለሆነም ስም ብቻ ይዘው የተቀመጡትን እረኞች እግዚአብሔር ወደሚፈልገው አገልግሎት በመታደስ እንዲገቡለት ይፈልጋል:: የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እረኞች ከቤርሳቤህ ወደ ካራን የወጡ፤ በቅባቱ ኃይል ድንጋዩን በማንከባለል እውነተኛውን አገልግሎት የሚያገለግሉ፤ በሰው ሥርዓትና ትብታብ ያልተያዙ፤ በሊቀ ካህናቸው ብቻ የሚደገፉና በተሰጣቸውም ሥልጣን የሚጠቀሙ ናቸው:: እንዲሁም ደግሞ የሚመሩት ሕዝብ እነርሱን ለመታዘዝ ከእረኞች ጋር በቃል ኪዳን የተሳሰሩ ናቸው::

# አስተማሪዎች

የማስተማር ቅባት ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊና በጣም ታላቅ ለውጥ የሚያመጣ ነው:: ነገር ግን ክርስቶስ ምርኮን ማርኮ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ የሰጠው የማስተማር ቅባት ከልምድ ከምናገኘው የማስተማር <u>ችሎታ</u> በጣም የተለየ ነው:: በችሎታና በቅባት መካከል ልዩነት አለ:: ሰው በልምድ፥ በትምህርትና በዕድሜ ብዛት ችሎታን ሊያገኝ ይችላል ወይም በተፈጥሮ ስጦታ በአንድ ነገር ችሎታ ሊኖረው ይችላል ቅባት ግን ከዚህ ሁሉ በጣም የተለየ ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ጻፎችና የሕግ መምህራን የማስተማር ችሎታ ነበራቸው:: እዚህ ላይ ሰዎች የማስተማር ችሎታ አላቸው ማለት ከአምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች ውስጥ ከክርስቶስ የአስተማሪነት ቅባት ተቀበሉ ወይም ተካፋይ ሆኑ ማለት አይደለም:: አንድ ሰው ከዕድሜ ብዛት ካገኘው ልምድ ቅዱሳን መጽሐፍትን አንብቦ በመረዳት ሰዎችን ሊያርም፥ ሊገስፅ፥ ሊመክር፥ እንዲሁም የተፃፉትን የእግዚአብሔር





ቃል በመጥቀስ ሰዎችን ሊያስተምር ይችላል:: ይሁን እንጂ የማስተማር ቅባት ከዚህ የተለየ ነው:: ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የማስተማር ችሎታና የማስተማር ቅባት ያላቸው ሰዎች ተለይተው መታወቅ አለባቸው:: የማስተማር ችሎታ ባላቸው ሰዎችና ጌታ ባካፈለው የማስተማር ቅባት ባላቸው ሰዎች መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ:: ይህንን ለመረዳት የጌታ ኢየሱስን አገልግሎት መመልከቱ ይጠቅመናል::

ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በትምህርቱ ሰዎች እጅግ ይደነቁ ነበር:: ምክንያቱም እርሱ ያስተምር የነበረው በቅባቱ ነበርና መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጥልን "...ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ እንደ ጻፎች ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና":: (ማቴ7÷28-29) እዚህ ላይ ክርስቶስ በነበረበት ጊዜ ጻፎችና የሕግ መምህራንም ማስተማር ሕዝቡን ያስተምሩ ነበር:: ጌታ ግን እንደ ጻፎችና የሕግ መምህራን በችሎታ ሳይሆን በሥልጣን በቅባቱ ኃይል ያስተምራቸው ነበር የሰሙትም እጅግ ይደነቁ ነበር:: "በበዓሉም እኩሌታ ላይ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ ያስተምር ጀመር ፤ አይሁዳውያን ባለሥልጣኖችን ይህ ሰው ሳይማር እንዴት ይህን ሁሉ ሊያውቅ ቻለ ? እያሉ ይደነቁ ነበር::" (ዮሐ 7÷14-15)

ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው የእኔ ትምህርት ከላከኝ ከአብ የተገኘ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም:: የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ የሚፈልግ ቢኖር ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር የተገኘ ወይም እኔ የተናገርኩት መሆኑን ያውቃል:: (ዮሐ7÷16-17) በዚህ ጥቅስ ላይ በቤተ መቅደስ ውስጥ ያሉ አይሁድ ባለሥልጣኖች የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ፊደል በማጥናት ብቻ የሚታወቅ ነው ብለው ስለሚያምኑ ኢየሱስ እንደ ፊደል መጽሐፍን ሳይቆጥር የእግዚአብሔርን ቃል ከሰማይ እየተቀበለ በሥልጣን ሲያስተምራቸው ተደነቁ::

እውነተኛ የማስተማር ቅባት ያለው አስተማሪ ትምህርቱ ከሰማይ የተገኘ ሕዝቡን የሚያስደንቅና ሰማያዊውን የእግዚአብሔርን ምስጢር በመግለጥ ወደ ሕዝቡ የሚያስተላልፍ ነው:: ለተቀቡ አስተማሪዎች በቀላሉ የእግዚአብሔር የቃሉ ፍቺ (መገለጥ) ይፈስላቸዋል:: የተሰወረውን በቅዱሳት መጽሐፍ የተፃፈውን የእግዚአብሔርን ቃል በመተርተር ምእመናን ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ጋር በደንብ የሚያጣብቁ ናቸው:: እንዲሁም እግዚአብሔር በየዘመናቱ የሚያደርገውን አስደናቂ ሥራ ከእግዚአብሔር

ቃል በመግለጥ የእግዚአብሔርን የዘመኑን ዕቅድ ለዘመኑ ሰዎች የሚገልጡ ናቸው::

ከዚህ የተነሣ ሁል ጊዜ የተቀቡ አስተማሪዎች አዳዲስን ነገር ከቃሉ እየቆፈሩ ስለሚያወጡ መለወጥን በማይፈልጉ በፈሪሳውያንና በሕግ መምህራን ብዙ ሊባሉ ይችላሉ:: ጌታ በሚያገለግልበት ጊዜ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቀው የሚያውቁ ነበሩ:: ነገር ግን ከሚያውቁት ከብሉይ ኪዳን ውስጥ የተሰወረውን ምስጢር በመግለጽ መልሶ ለራሳቸው ሲያስተምራቸው እንደ ዘመናችን ፈሪሳውያን እነሱም "ይህ አዲስ ትምህርት አይደለምን" ይሉ ነበር:: (ማር 1÷27)

እግዚአብሔር ምን ጊዜም በሕዝቡ መካከል አዳዲስ ነገሮችን ማድረግ ይፈልጋል:: እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን አዲስ ነገር ሕዝቡ በእምነት እንዲቀበል በመጀመሪያ በአስተማሪዎች በኩል ከቃሉ እውነት እየገለጠ አዲስ ነገር እንዳለ በማሳየት ሕዝቡ እንዲወርሱ ያስተምራቸዋል:: ቤተ ክርስቲያን ወደ ሙላት እንድትገባ የአስተማሪዎች ቅባት ትልቅ ስፍራ አለው:: የእግዚአብሔር ቃል በሆሴዕ 4÷6 ላይ "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል" ይላል:: በኤፌሶን 4÷11-16 ላይ ደግሞ ስናይ ቤተ ክርስቲያን ፍፁምና ሙሉ ሰው ወደ መሆን የሚያደርሳትን በቁጥር 12 ላይ ሲገልፀው "ሁላችን የእግዚአብሔር ልጅን በማመንና በማወቅ" እንደሆነ ይነግረናል:: የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ደግሞ በዮሐንስ 1÷1-5 ላይ "ቃል" እንደሆነ ይህም ቃል ደግሞ እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ ወልድም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ይነግረናል:: ቃሉንም ካላወቅን በቃሉ መታመን አንችልም:: እውቀት ከሌለን ደግሞ ሆሴዕ እንዳለው ከእግዚአብሔር ተለይተን መጥፋታችን ነው::

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፍፁምና ሙሉ ሰው በእምነትም ወደሚገኝ አንድነት እንድትመጣ ከተፈለገ እውነተኛ አስተማሪዎችን የግድ መቀበል አለብን:: ያለ አስተማሪዎች ቅባት የእግዚአብሔርን ልጅ ክርስቶስን (ቃሉን) ማወቅ አንችልም:: ቃሉን የሚያሳውቁን አስተማሪዎች ከሌሉን ደግሞ በኤፌሶን 5÷26-27 ላይ ባለው መሠረት ገና አልተቀደስንም እስከ አሁንም ድረስ በፊት መጨማደድና በነውር እንዲሁም በዕድፈት ውስጥ ነን ማለት ነው:: ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ሁሉ ነፅታ ክርስቶስን ወደ መምሰል የምትደርሰው እንደ ውኃ አጥቦ የሚያነጻው ቃሉን በተቀቡ አስተማሪዎች አማካኝነት ስታገኝ ነው::





ታዲያ አዳዲስ ነገሮችን የማስተማር ቅባት ያላቸው የእግዚአብሔር ሰዎች ለምን በየስፍራው መወገዝ ይደርስባቸዋል ? እግዚአብሔር ቀብቶ የሚሰጠንን አስተማሪዎችን ከመቀበል ይልቅ ሐሰተኞች ናቸው የምንልበት ምክንያት ምንድነው? እንግዲህ ለዚህ መልስ የሚሆነንን ከዚህ በታች እንመለከተዋለን::

## ሀ) ትምህርቱ አዲስ ስለሚሆንባቸው

በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 1÷21-27 ላይ ጌታ ኢየሱስ ወደ ቅፍረናሆም በገባ ጊዜ ወዲያው በሰንበት ወደ ምኩራብ ገብቶ ከወትሮው ለየት ያለ ከጻፎች ትምህርት በጣም የተለየ እንግዳ የሆነ ነገር ያውም በሥልጣን አስተማራቸው ከዚህ የተነሣ መገረም ሞልቶባቸው " ይህ አዲስ ትምህርት አይደለምን እያሉ እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ" ኢየሱስ የሚሠራው ነገር አዲስ የሚያስተምራቸው ነገር አዲስ ሆነባቸው:: ይህ የኢየሱስ ትምህርት ምንም አዲስ ቢሆን የብሉይ ኪዳንን የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን አልነበረም:: ነገር ግን ሕዝቡም ሆኑ የሃይማኖት መሪዎቻቸው የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍ ከሰው ሠራሽ ሥርዓትና ወግ ጋር ስለደባለቁት ኢየሱስ የሚያስተምረውን የነጠረ ቃል መቀበል ተሳናቸው:: ስለዚህ የራሳቸውን ወግና ሥርዓት መጣል ስላልፈለጉ የተቀባውን ኢየሱስን ሐሰተኛ አስተማሪና ነቢይ ማለት በጣም ቀለላቸው:: የዚህም የመጨረሻ ውጤት ኢየሱስን እያወገዙ እስከ ሞት ድረስ ገፉት::

ቤተ ክርስቲያን አዳዲስ መገለጥና የቃሉን እውነት ይዘው የሚነሱትን ሁሉ ሐሰተኛ ከማለት የሚያስተምሩት ትምህርት እንደ እግዚአብሔር ቃል ነው ወይ? በማለት መመርመሩ እጅግ ያዋጣል:: ነገር ግን ከእኛ ወግና ሥርዓት ጋር ያልሄደውን ሁሉ ሐሰተኛ ነው ማለት በፍፁም አንችልም:: እግዚአብሔር ተሐድሶን ሲያመጣ ወደድንም ጠላንም ወግና ሃይማኖታዊ ሥርዓታችን መነካቱ አይቀርም:: ስለዚህ እንደ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ልጅ (ቃሉን) መግፋት ይሻለናል ወይስ በቃሉ የእኛን ኮተት መጣል ? የቱ ይሻለናል?

## ለ) ለአዲስ ወይን ጠጅ አዲስ አቁማዳ ያስፈልጋል

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5÷27-39 ላይ ጌታ ሌዊ የተባለውን ቀራጭ በቀረጥ መቀበያ ስፍራ ተቀምጦ አየውና ተከተለኝ ብሎ ከጠራው በኋላ ሁሉን ነገር ትቶ ተከተለው:: ከዚህ በኋላ ሌዊ ለኢየሱስ ክብር በቤቱ ታላቅ ግብዣ አዘጋጀ:: በግብዣው ላይ የነበሩ ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህራን አሮጌ የሆነ የጾምና የጸሎት አመለካከት ነበራቸው:: ይኸውም አንጀታቸውን አጥፈው ሳይበሉ በመዋላቸው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙና ለእግዚአብሔር የመጀመሪያ ተጠሪዎች አድርገው እራሳቸውን ይቆጥሩ ነበር:: ይህም አሮጌ አመለካከታቸው ግብዞችና ትምክህተኞች እንዲሆኑ ስላደረጋቸው ያላቸውን አሮጌ አመለካከት ይዘው ለኢየሱስ በጥያቄ መልክ አቀረቡለት:: ኢየሱስም ደግሞ ስለ ጾምና ጸሎት ያለው አመለካከት አዲስ ስለነበረ በምሳሌ ይመልስላቸው ጀመር "በአረጀው የወይን ጠጅ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር ማንም የለም ይህን የሚያደርግ ቢኖር ግን አዲሱ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳዋል .......ስለዚህ አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገባል" አላቸው:: (ሉቃ 5÷37-38)

ጌታ ኢየሱስ የተናገረው ምሳሌ ከጾምና ከፀሎት ጋር ምንም የተያያዘ አልነበረም:: የተናገረው ግን አሮጌ አመለካከት ይዘው አዲሱን አመለካከት ለመቀበል የማይሞክር እንደሆነ ጉዳት እንዳለው በምሳሌ ያስረዳቸው ነበር:: ችግሩ ያለው የወይን ጠጁ ላይ ሳይሆን አቁማዳው ላይ ነው:: ዛሬም ቢሆን ብዙ የተቀቡ አስተማሪዎች አዳዲስ እውነቶችን ይዘው ሲመጡ የሚገፉት ከሚያስተምሩት ትምህርት ሳይሆን ችግሩ ያለው የሰሚዎቹ አቁማዳ ላይ ነው:: በአሮጌ አመለካከት ከዛሬ ሃያና ሠላሣ ዓመት በፊት በያዙት የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ከራሳቸው ወግና ሥርዓት ጋር ደባልቀው ከዚያ በላይ መሄድ ስለማይችሉ ያላቸውም አሮጌ አቁማዳ ስለሆነ አዲሱን መቀበል በፍፁም አይችሉም:: አዲስ ነገር ከሰሙ ሁል ጊዜ የአሮጌው አመለካከታቸው አቁማዳ ይፈነዳል፤ የፍንዳታውም ድምፅ ደግሞ ከአንደበታቸው ሲወጣ ሁሌ ተቃውሞን የሚያሰማ ይሆናል::

ስለዚህ በእነርሱ አሮጌ አቁማዳ አዲሱን የወይን ጠጅ ሲያስቀምጡ ሁል ጊዜ ጥፋት የሚያመጣ ፍንዳታን የሚያስከትል ስለሆነ ሁሉን "የስህተት ትምህርት ነው" በማለት እንደፈሪሳውያን ማውገዝ ብቻ ነው





የሚያውቁት:: ስለ እነኚህ ፈሪሳውያን በቁጥር ሠላሳ ዘጠኝ ላይ ጌታ ሲገልጽልን :-

> "ብዙ ጊዜ የቆየ ደረቅ የወይን ጠጅ የጠጣ አዲሱን በተሐ የወይን ጠጅ መጠጣት አይፈልግም ምክንያቱም የቆየው ደረቅ የወይን ጠጅ የተሻለ ነው ይላል::" (ሉቃ 5÷39)

በዚህ ጥቅስ ላይ አሮጌው የወይን ጠጅ መጠጣት የለመዱ ሰዎች አዲሱን መጠጣት በፍፁም አይፈልጉም:: መጠጣት የማይፈልጉበትን ምክንያት ጌታ ሲገልፀው "የቆየው ደረቅ የወይን ጠጅ የተሻለ ነው ይላሉ" እዚህ ላይ በደንብ እንመልከት የተመኙት የወይን ጠጅ "ደረቅ" ነው ምንም ልስላሴ የሌለው ደረቅ÷ ልምላሜን የማያሳይ ደረቅ÷ ጥቅም የሌለው ደረቅ ቃል÷ ደረቅ አገልግሎት÷ ደረቅ ሕይወት÷ ደረቅ ኑሮን፤ እነዚህ ሰዎች በሁሉ አቅጣጫ ምርጫቸው ደረቅ የወይን ጠጅ ነው:: እነኚህ ሰዎች ምርጫቸውን እስካላስተካከሉ ድረስ አዲሱን የወይን ጠጅ በፍፁም መጠጣት አይችሉም:: አዲሱ የወይን ጠጅ ግን የሚያደርቅ ሳይሆን የሚያረጥብ÷ ጊዜና ወቅቱ ያላለፈበት÷ ከሰማይ የመጣ ትኩስ ምንም ክፉ ነገር የሌለበት ጌታ ራሱ እንዲጠጡት የመረጠው አዲሱን የወይን ጠጅ ነበር:: በፈሪሳውያን አመለካከት ግን ደረቁ የወይን ጠጅ የተሻለ ነው ብለው አንዴ ስለተቀበሉት አመለካከታቸው እስካልተለወጠ ድረስ የአዲሱ የወይን ጠጅ ውበትና ጣዕም በፍፁም አይታያቸውም::

ስለዚህ አዲስን ነገር የሚያስተምሩንን አስተማሪዎች ትምህርታቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል ስንመረምር ምንም ስሕተት ላይኖረው ይችላል:: ስለሆነም ትምህርቱ ሳይሆን መቀየር ያለበት አቁማዳው ነው መለወጥ ያለበት:: በአሮጌው አቁማዳ አዲሱን የወይን ጠጅ በፍፁም መቀበል አንችልምና:: አዲሱን የወይን ጠጅ÷ አዲሱን የእግዚአብሔርን ዕቅድ÷ አዲሱን የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ከእግዚአብሔር ለመቀበል አዲሱን አቁማዳ መያዝ ይገባናል::

## ሐ) የተቀቡትን መናቅ

በሉቃስ 4÷16 እስከ 30 በምንመለከትበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በዲያብሎስ ከተፈተነ በኋላ ወደ አደገበት አገር ወደ ናዝሬት ሄደ:: እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገብቶ የነቢዩ ኢሳያስን መጽሐፍ

ገልጦ አነበበላቸውና ይህ ቃል ዛሬ ተፈፀመ ብሎ መጽሐፉን ዘጋው:: ጌታ ያነበበው እግዚአብሔር እንደቀባው የሚገልፀውን ክፍል ነበር:: ይህም ያነበበው ቃል እውነት እንደሆነ "ሁሉም ይመሰክሩለት ነበር ከአፉም ከሚወጣው ከጸጋው ቃል የተነሣ እየተደነቁ ..." :: (ሉቃ 4÷22)(የቀ.ት) ነገር ግን ኢየሱስ ምንም የተቀባና ከአንደበቱም የሚወጣው ግሩም የሆነ የጸጋ ቃል እንደሆነ ቢመሰክሩለትም የእርሱን ቅባትና የጸጋውን ቃል እንዳይቀበሉ ያደረጋቸው ነገር ኢየሱስ የናዝሬት ሰውና እናቱም ማርያም እንደሆነች ስላወቁ ብቻ የናዝሬት ሕዝብ ጌታ ኢየሱስን በመናቅ የአናጢው የዮሴፍ ልጅ ብለው ኢየሱስን ገፉት:: አብሮአቸው በናዝሬት በማደጉ አብሮአቸው መብላት መጠጣቱ ወ.ዘ.ተ የተቀባውን ኢየሱስን እንዳይቀበሉት አደረጋቸው::

ዛሬም ቢሆን በአንድ ቤተ ክርስቲያን አብሮ ማደግ ምናልባትም እየመከርን ያሳደግናቸው ልጆች በጌታ ጥቂት ዓመታትም የቆጠሩትን ድንገት በእግዚአብሔር ቅባት ተቀብተው ከአፋቸው የሚወጣው የጸጋ ቃል እጅግ የሚያስደንቅ ሲሆንብን የምንሰጣቸው ምላሽ ምን ይሆን? ነገር ግን በውስጣችን የምንንቃቸው ከሆነ ኢየሱስን ከገፉት ከናዝሬት ሰዎች በምንም አንለይም:: የተቀቡ መሆናቸውን ውስጣችን እየመሰከረልን ከአፋቸው በሚወጣው የጸጋ ቃል ውስጣችን መበርበር ሲጀምር ገና ለገና የእራሳችን ክብር÷ ወግና ሥርዓታችን እንዳይነካ በማለት እግዚአብሔር የቀባቸውን በመናቅ ሐሰተኞች ናቸው ብንል ፈራጅ ቆሟልና የተቀቡትን ከመናቅ እንጠንቀቅ::

እንግዲህ ባለንበት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ እየያዘች ስለሆነ የማስተማር ችሎታ ባላቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ወደ ፍፁም ሙላት መድረስ አትችልም:: ምክንያቱም የማስተማር ችሎታ ያላቸው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ላይ ላዩን ብቻ ነው የሚጠቁሙን:: ነገር ግን ማንንም ሳይፈሩ የተሰወረውን የእግዚአብሔርን እውነት በመግለጥ የተበላሸው የእግዚአብሔር ዕቅድ ይህ ነው እያሉ ትክክለኛውን መንገድ የሚያሳዩ ከክርስቶስ ቅባት ተካፋይ የሆኑ አስተማሪዎች ያስፈልጉናል:: ካለ አስተማሪዎች ቅባት ቤተ ክርስቲያን በእውነት ላይ መራመድ አትችልም::





# የመንፈስ ቅዱስ የክትትል ሥራ

በአስቴር ምዕራፍ 2÷9 ላይ በመታሽት ቅርጽ እንድትይዝና ወደ መታሻ ምርጥ ክፍል እንድትወሰድ እንዲሁም ቅርጽ መያዝ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ቅርጽም እንዲኖራት የሚያደርጓት አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች እንደሆኑ አንድ በአንድ ተመልክተናል::

በአስቴር ምዕራፍ 2÷11 ላይ ቅርጽ እንድትይዝ ወደ መታሻ ክፍል የገባችውን አስቴርን አስመልክቶ ስለመርዶክዮስ የክትትል ሥራ ሲያብራራ "መርዶክዮስም አስቴር በምን ዓይነት ሁኔታ እንዳለችና ወደፊት የሚገጥ ማት ዕድል ምን እንደሆነ ለማወቅ በየቀኑ በምርጥ ሴቶች መኖሪያ ቤት አደባባይ ፊት ለፊት ወዲያና ወዲህ ይመላለስ ነበር"ይለናል:: (አስቴ 2÷11)

ስለዚህ ቅርጽ መያዝ በወሰነችና ጉዞዋን በጀመረች እንደ አስቴር ባለች ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት መርዶክዮስ (መንፈስ ቅዱስ) ሁል ጊዜ ይገኛል:: በጉዳይዋ ሊገኝ÷ በጸሎት ቦታዋ÷ በአገልግሎት ስፍራዋ ሁል ጊዜ ሊረዳትና ሊመራት ቅርጽ በመያዝ ላይ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት መንፈስ ቅዱስ ይቆማል:: እንዲሁም "ወደ ፊት የሚገጥማት ዕድል ምን እንደሆነ ለማወቅ" በፊት ለፊትዋ ሁል ቀን ይገኝ ነበር:: ምክንያቱም እንደ ንግሥት አስጢን የእምቢታን ድምጽ እንዳታሰማ ያለችበትን ሁኔታ በየቀኑ ይቆጣጠር ነበር:: ዛሬም ቢሆን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ በየቀኑ እንደሚቆጣጠር ማወቅ ይኖርብናል:: ለዘመኑ የእግዚአብሔር ዕቅድ ያለንን የልባችንን ምላሽ÷ እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥሪና ለንጉሡ የዘውድ መጫን ጥሪ የምንሰጠውን ምላሽ ለማወቅ ከፊት ለፊታችን ቆሟል:: ስለዚህ ያለን ምላሽ የእሺታ÷ የትህትናና የመታዘዝ ነው ወይስ የመኩራት÷ የትዕቢትና የእምቢተኝነት ? የቤተ ክርስቲያን መሪዎች÷ አገልጋዮችና ምእመናን እዚህ ላይ በደንብ አስተውሉ ባለንበት ዘመን መንፈስ ቅዱስ አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች በደንብ ቦታቸውን ይዘው በመሥራት ቤተ ክርስቲያን የተዋበች እንድትሆን የተሐድሶን ሥራ ለመሥራት ለእያንዳንዳችን የፍቅር ድምፁን እያሰማን ነው ታዲያ ለዚህ ድምፅ ምላሻችን ምን ይሆን? የእሺታን ድምፅ እንድናወጣ ጌታ ይርዳን:: ነገር ግን መታደስን የማትፈልግ ቤተ ክርስቲያን ካለች ባልዋ ፍቅሩን ሲገልፅላት ምላሹን የማትሰጥ ቤትዋን በገዛ እጅዋ የምታፈርስን ሴት ትመስላለች:: ስለዚህ እንጠንቀቅ !!